www.zeyeneta.com

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን እምነት ፤ ሥርዓተ አምልኮትና የውጪ ግንኙነት



ይህ የእምነትና ሥርዓት መጽሐፍ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ቀዳማዊ ፣ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ የቤተ ክርስቲያንን ዕድገት ለማፋጠን ባላቸው ጽኑ ምኞት ፤ ባሳዩት ጥረትና በሰጡት መመሪያ መሠረት ተዘጋጅቶ ፣ ለሁለተኛ ጊዜ ታተመ ።

አሳታሚ፡– ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት
PUBLISHER:– TENSAE PUBLIHSING HOUSE

አዲስ አበባ ሐምሌ 1988 ዓ·ም·
ADDIS ABABA, JULY 1996

www.zeyeneta.com



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ቀዳማዊ ፡
ፓትርያርክ፣ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ
His Holiness Abune Paulos I
Patriarch of the Ethiopian Orthodox Tewahedo Church.

www.zeyeneta.com

አዘጋጅዎች

1· ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ የአክሱምና የመላዋ ትግራይ
ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ..... ሰብሳቢ

2· ብፁዕ አቡነ አብርሃም ሊቀ ጳጳስ የስብከተ ወንጌልና
ሐዋርያዊ ተልእኮ መምሪያ የበላይ ኃላፊ ..... አባል

3· ብፁዕ አቡነ ናትናኤል የአርሲ ሀገረ ስብከት
ሊቀ ጳጳስ ..... »

4· ብፁዕ አቡነ በርተሎሜዎስ የሲዳሞና
የቦረና አህጉረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ..... »

5· ብፁዕ አቡነ ሳሙኤል የጂማ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ .. »

6· ብፁዕ አቡነ ገብርኤል የውጭ ጉዳይና የሕዝብ
ግንኙነት የበላይ ኃላፊ እና የምዕራብ ሸዋ
ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ..... »

7· ብፁዕ አቡነ ገሪማ ሊቀ ጳጳስ የቅ/ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ
የጠቅላይ ቤተክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅና
የቅ/ሥላሴ/መ/ኮሌጅ ዲን ..... »

8· መልአከ ታቦር ተሾመ ዘሪሁን በአውስትራሊያ
የኢ·ኦ·ተ· ቤተ ክርስቲያን ኃላፊ ..... »

9· ሊቀ ካህናት ክንፈ ገብርኤል አልታየ የቅ/ጳውሎስ
ከ/መንፈሳዊ ት/ቤት ም/ዲን ..... »

10· መልአከ ሰላም ዳኛቸው ካሣሁን የስብከተ ወንጌልና
ሐዋርያዊ ተልእኮ መምሪያ ኃላፊ ..... »

11· መጋቤ ብሉይ ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ የቅ/ጳውሎስ
ከ/መንፈሳዊ ት/ቤት መምህር ..... »

12· ሊቀ ካህናት ብርሃኑ ገብረ አማኑኤል የትንሣኤ
ማሳተሚያ ደርጅት ኃላፊ ..... »

13· መጋቤ ብርሃናት ጎሐጽባሕ ጥሩነህ በቅ/ሥላሴ
መንፈሳዊ ኮሌጅ የሐዲሳት ትርጓሜ መምህር ..... »

14· መረጌታ ደጉ ዓለም የመንበረ ፓትርያርክ ቅ/ቅ/ማርያም
ቤ/ክ/ የመጻሕፍተ ሐዲሳት መምህር..... »

www.zeyeneta.com

15· መጋቤ ምሥጢር ወልደ ሩፋኤል ፊታሒ
የዜና ቤተክርስቲያን ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ..... »
16· መሪጌታ ጽጌ ዘሪሁን ከትምህርትና
ማሠልጠኛ መምሪያ ..... »
17· ሊቀ ሥዩማን ራደ አስረስ ከሊቃውንት ጉባኤ ..... »
18· መመህር ሀ/ማርያም ተድላ » » ..... »

ከላይ በተገለጹት አባላት ከተዘጋጀ በኋላ፣

1· መምህር ገብረ ሕይወት የደብረ ጽጌ ቅ/ማርያም ገዳም የሐዲሳት ትርጓሜ መምህር
2· መልአከ ገነት ገብረ ሥላሴ አወቀ በሰዋስወ ብርሃን ቅ/ጳውሎስ ከ/መንፈሳዊ ት/ቤት የብሉያት ትርጓሜ መምህር
3· መምህር ስብሐት ገብረ እግዚአብሔር በሰዋስወ ብርሃን ቅ/ጳውሎስ ከ/መንፈሳዊ ት/ቤት የመጽሐፍተ ሐዲሳት ትርጓሜ መምህር
4· መጋቤ ብሉይ መዘምር ታየ በቅ/ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ የብሉያት መምህር ባሉበት ታይቷል ።

www.zeyeneta.com

ማውጫ

አርእስት **ገጽ**

የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ መልእክት ..... ፩

መቅድም ..... ፫

መግቢያ ..... ፲፭

ክፍል ፩
እምነት

ምዕራፍ ፩ ሀልዎተ እግዚአብሔር ..... ፲፯

ምዕራፍ ፪ ሥነ ፍጥረት ..... ፳፩

ምዕራፍ ፫ አምስቱ አዕማደ ምሥጢር ..... ፳፬

ሀ) ምሥጢረ ሥላሴ

ለ) ምሥጢረ ሥጋዌ

ሐ) ምሥጢረ ጥምቀት

መ) ምሥጢረ ቁርባን

ሠ) ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን

ምዕራፍ ፬ ሰባቱ ምሥጢራተ ቤተክርስቲያን ..... ፴፫

ሀ) ምሥጢረ ጥምቀት

ለ) ምሥጢረ ሜሮን

ሐ) ምሥጢረ ቁርባን

መ) ምሥጢረ ክህነት

ሠ) ምሥጢረ ተክሊል

ረ) ምሥጢረ ንስሓ

ሰ) ምሥጢረ ቀንዲል

ምዕራፍ ፭ ቅዱሳት መጻሕፍት ..... ፵፩

ምዕራፍ ፮ ትውፊት ..... ፵፯

ምዕራፍ ፯ ክብረ ቅድስት ድንግል ማርያም ..... ፶፱

www.zeyeneta.com

ምዕራፍ ፭ ክብረ ቅዱሳን ..... ፶፫
ሀ) ክብረ መላእክት ቅዱሳን
ለ) ቅዱሳን ነቢያት
ሐ) ቅዱሳን ሐዋርያት
መ) ቅዱሳን ሰማዕታት
ሠ) ጻድቃን
ረ) ክብረ ዐጽመ ቅዱሳን
ምዕራፍ ፮ ቤተክርስቲያን ..... ፶፱
ምዕራፍ ፯ ታቦት ..... ፷፭
ምዕራፍ ፰ ሃይማኖትና ምግባር ..... ፷፱

ክፍል ፪

ሥርዓተ አምልኮት ...
ምዕራፍ ፱ ሥርዓተ ጸም ..... ፸፯
ምዕራፍ ፲ ሥርዓተ ጸሎት ..... ፹፮
ምዕራፍ ፲፩ ሥርዓተ ምጽዋት ..... ፹፱
ምዕራፍ ፲፪ ሥርዓተ ስግደት ..... ፺፭
ምዕራፍ ፲፫ ሥርዓተ በዓላት ..... ፺፮
ምዕራፍ ፲፬ ሥዕል ..... ፺፰
ምዕራፍ ፲፭ መስቀል ..... ፺፰
ምዕራፍ ፲፮ ንዋያተ ቅድሳት ..... ፻

ክፍል ፫
የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የውጭ ግንኙነት

ምዕራፍ ፲፯ የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት
ቅድመ ክርስትና ..... ፻፫
ምዕራፍ ፲፰ የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት
በዘመነ ክርስትና ..... ፻፮

www.zeyeneta.com

ምዕራፍ ፳፪ የኢትዮጵያን መንበረ ጵጵስና
ለመመሥረት የተደረገ
የውጭ ግንኙነት ..... ፻፱

ምዕራፍ ፳፫ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
ቤተክርስቲያን የምትቀበላቸው
ዓለም አቀፍ ጉባዔያት ..... ፻፲፫

ምዕራፍ ፳፬ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
ቤተክርስቲያን የውጭ ግንኙነት
ከኬልቄዶን ጉባዔ በኋላ ..... ፻፳፪

ምዕራፍ ፳፭ ከኬልቄዶን ጉባኤ በኋላ በክርስትና
እምነት ጥንካሬ የተገኘ ዓለም አቀፍ
ዕውቅና/ገነና/ ..... ፻፳፬

ምዕራፍ ፳፮ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
ቤተክርስቲያን የውጭ ግንኙነት
በአሁኑ ጊዜ ..... ፻፴፩

ምዕራፍ ፳፯ በኦርየንታል ኦርቶዶክስ አብያተ
ክርስቲያናትና በምሥራቅ ኦርቶዶክስ
ቤተክርስቲያን መካከል ምሥጢረ
ሥጋዌን በተመለከተ የተደረገ
ውይይት ..... ፻፴፬

www.zeyeneta.com

የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ መልእክት

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን

የተወደዳችሁ ምእመናን!

ቀደምት ቀዱሳን አበው ልባቸው በእግዚአብሔር ፍቅር የነደደ ስለነበር እንደ መላእክት ዘወትር ፈጣሪያቸውን ቅዱስ ፣ ቅዱስ ፣ ቅዱስ ፣ እያሉ ያመሰግኑ ነበር ። ከአምላክ በተሰጣቸው ጸጋ መጻሕፍትን ሲያመሠጥሩ ፣ ብሉያት ሐዲሳትን ሲተረጉሙና ሲያስተምሩ ኖረዋል ። ከተውንም አግዚአብሔር አምላካቸውን በሰቂለ ኅሊና ፣ በነቂሀ ልቡና ጥዋት ማታ ማመስገን የዘወትር ተግባራቸው ነበር ። በፍጹም ልብ ፣ በፍጹም ሀሳብ ፣ በፍጹም ነፍስ ቅዱስ ኃያል ፈጣሪያቸውን በጽኑ ከማመናቸውና ከመውደዳቸው የተነሣ ሀብታተ መሥጢራት እየተሰጧቸው ቅዱሳት መጻሕፍትን በጥልቀት አብራርተዋል ፣ ተርጉመዋል ፣ በምሥጢር ተራቀቀዋል ፣ አያሌ ትሩፋትንም ፈጽመዋል ። ከአባቶች ሐዋርያትና ከቅዱሳን ጻድቃን ሰማዕታት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ነቅ ሳያስገቡ ትክክለኛውን እምነት፣ ሥርዓትና ትውፊት ጠብቀው አቆይተውናል ። በዚህም ሳይወሰኑ ፣ ጥንታዊት ፣ ሐዋርያዊት፣ ታሪካዊትና ብሔራዊት የሆነችውን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በመንፈሳዊ ተጋድሎና በበጎ ምግባር ይበልጥ አጠናክረውና አክብረው ለአሁኑ ኢትዮጵያዊ ትውልድና ለመላው ዓለም አውርሰዋል ። ልበ አምላክ ቅዱስ ዳዊት «በምድር እንደተፈተነ ሰባት ጊዜ እንደተጣራ ብር የእግዚአብሔር ቃላት የነጽ ቃላት ናቸው" (መዝ· 11፡16) እንዳለው ሁሉ የዚህች ቤተክርስቲያን አባል ለመሆን የታደለው ኢትዮጵያዊ ሁሉ በቅድስት ቤተክርስቲያኑ ሊኮራ ይገባል ። ከርስዋ መንጭቶ ፣ አምሮና ደምቆ በዓለሙ ሁሉ ገንኖ የነበረውን ታላቁን የኢትዮጵያ ሥልጣኔ ወደ አንድ

www.zeyeneta.com

ቢሊዮን የሚጠጋው መላው የምድራችን ጥቁር ሕዝብ ሊመራመርና ሊያውቅ ፣ ሊመካና ሊኮራም ይገባል ።

ይህም መመራመር የዕውቀት ጥማትን ለማርካት የሚደረግ ጥረት ብቻ ሳይሆን የትውልድ ግዴታና መንፈሳዊ ተልእኮም ጭምር ነው ። ይልቁንም ምእመኑ ፣ መላው ሕዝባችን እምነቱን ጠንቅቆ የማወቅ ፣ ሃይማኖቱን ከቢጽ ሐሳውያን የመከላከልና ለልጆቹም የማስተማር ኃላፊነት አለበት ። ይህ በልዩ የሊቃውንት ጉባኤ ተዘጋጅቶ በቅዱስ ሲኖዶስ ታይቶና ጸድቆ የቀረበው መጽሐፍ ዓላማው ይህ ነው ።

«ካልጠየቁ አያውቁ ፣ ካላወቁ አይጸድቁ» ነውና ምእመናን ሃይማኖታቸውን ፣ ሥርዓቱንና ትውፊቱን ሊረዱ ይገባል ። ስለ እምነታችን ሊያውቁ ለሚሹም የውጭ ሰዎች መጽሐፉ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ተተርጉሞ ስለቀረበ ለማንበብ ያመቻቸዋል ። የሃይማኖታችንን ምንነት ከስረ መሠረቱ ጠንቅቀው ካለማወቅ የተነሣ የተዛባ አመለካከት ፣ ፈር የሳተ አስተያየት የሚሠነዝሩት ሁሉ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ትክክለኛውን እምነት ከምንጩ ሊያገኙ ይቻላቸዋል ። በማወቅም ሆነ ባለማወቅ በስሕተትም ሆነ በድፍረት ለሚናገሩት ሰዎች አስተዋይ ለአምሮ እንዲሰጣቸው እንመኛለን ።

ከዚህም ሌላ በኦሪየንታል ኦርቶዶክስና በምሥራቅ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ፣ በኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናትና በምዕራብ አብያተ ክርስቲያናት መካከል ባለው የትምህርተ ሃይማኖት ፣ ቀኖናና ሥርዓተ አምልኮት ልዩነት ላይ ውይይት ሊደረግ ይገባዋል የሚሉ ወገኖች ሁሉ የቤተ ክርስቲያናችን ጥንታዊ ትክክለኛና የማይዛባ እምነትና ሥርዓት በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተገለጸ መሆኑን እንዲያውቁልን እንሻለን ። «... ሁሉም አንድ ይሆኑ ዘንድ ...» ብሎ ጌታ እንደተናገረው ቤተክርስቲያናችን የክርስቲያኖቸን ኅብረትና አንድነት በመሠረቱ የማትቃወም ብትሆንም ለዚህ ሲባል እምነትና ሥርዓተ አምልኮት እንዳይፋለስ ብርቱ ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት ታምናለች ።

መጽሐፉ የቤተክርስቲያኒቱን እምነት ፣ ሥርዓተ አምልኮትና የውጭ ግንኙነት በሚገባ እንዲገልጽ ታስቦ በጥንቃቄና በጥራት የተዘጋጀ ስለሆነ ጠቀሚታው ከፍ ያለ ነው ። ይህ መጽሐፍ የእምነታችንን አዕማድ ዋና ዋና ነጥቦችን ጠቅሎ አስፍሯል ። በረጋ አእምሮ

www.zeyeneta.com

በተሰበሰበ ኀሊና እግዚአብሔርን ለጋዥ ለድርጎ ላነበበው የሃይማኖትን ሐዋርያዊ መሠረት ቁልጭ ለድርጎ ያሳያል ። መንፈሳዊ በረከትንም ያድላል ። እያንዳንዱም ምእመን እምነቱን በሚገባ ተረድቶ ፣ ሃይማኖቱን እንዲጠብቅና እንዲከላከልም ታላቅ መዛሪያ ይሆነዋል ። ቸርነቱ የማያልቅበት ፣ በዓለሙ ምሉዕ የሆነውን የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ጸጋና በረከት ይሳተፍ ዘንድ ንጹሕ ልቡናንና ቅን መንፈስን ያሳድርበታል። በመጪረሻም ምእመናንን ደጋግሚ አደራ የምለው ፣ እምነታችን ሥርዓታችን ፣ ትውፊታችን እንግዳ ደራሽ ሳይሆን ጥንታዊና ሐዋርያዊ ፣ በጠንካራ ለለት ላይ እንደተገነባው ቤተ ጽኑ መሠረት ያለው ስለሆነ ይህን መጽሐፍ በማንበብ ሃይማኖታችሁን በሚገባ እንድትረዱና እንድትጠብቁ ነው ።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር
እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ

ለባ ጳውሎስ
፫ትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ
ታኅሣሥ 29 ቀን 1988 ዓ.ም.
አዲስ አበባ ፣ ኢትዮጵያ

www.zeyeneta.com

መቅድም

ኢትዮጵያ በመጽሐፍ ቅዱስም ሆነ በዓለም ሥነ ጽሑፍ የታወቀች ቢሆንም በበለጠ የምትታወቀውና በሁሉም ዓይን ጎልታ የምትታየው «የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው» ከሚለው የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ጋር ተያይዞ በተመሠረተው የአምልኮተ እግዚአብሔር ታሪኳ ነው ። (መዝ·110፡10 ፣ ምሳ·1፡7)።

ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን በቅዱሳት መጻሕፍት ፣ በጥንታውያን የታሪክ ሠነዶችና በሥነ ጥንት ጥናት በቀይ ባሕር አካባቢና በዓባይ ሸለቆ ዙሪያ ከታወቁት አህጉር ሕዝብ ጐን ተገቢ ቦታዎችን ይዘው የሚገኙ ናቸው ።

በጥንታዊ ታሪክ መነሻነት ኢትዮጵያ የሚለው ቃል በመልክዐ ምድር አቀማመጥ ከግብፅ በስተደቡብ የሚገኝ በዘርና ቀለሙ እስከ ሕንድ ውቅያኖስ የሚደርስ ቀለምንና ዘርዐ ትውልድን የሚያመለክት የአካባቢ መጠሪያ መሆኑ ይታወቃል ።

ኢትዮጵያ የሚለው ስም ከሁለት የፅርዕ ቃላት መልከ–ጠይም የሚለው ተወስዶ በዚህ አካባቢ ለሚኖረው ሕዝብ መጠሪያ ስሙ ነው ። ሀገሪቱንም ኢትዮጵያ ያሰኘው የኗሪዎቹ ደም ግባት ነው ።

ኢትዮጵያ የሚለው ክልልም በየጊዜው የመስፋትና የመጥበብ ታሪክ ያጋጠመው ቢሆንም የምድረ ኢትዮጵያ ማዕከሉ የጥቁር ዓባይ መፍለቂያ (መነሻ) መሆኑ ግልፅ ነው ።

መጽሐፍ ቅዱስ የሁሉንም ነገር አጀማመር የሚነግረን ልዩ መጽሐፍ በመሆኑ በአሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ 2፡13 ላይ «የሁለተኛው ወንዝ ስም ግዮን ነው ፣ እርሱም የኢትዮጵያን ምድር ሁሉ ይከባል» ይላል። ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊትም «ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአ ብሔር ትዘረጋለች» ብሏል ። (መዝ· 67፡31)።

ኢትዮጵያ የሚለው ስመ ተጸውዖ በመጽሐፍ ቅድሱ በብዙ ቦታ ይገኛል። የብሉይ ኪዳን ነቢያትም ወደ ዝርዝር ጉዳይ ሳይገቡ የኢትዮጵያን ስም ይጠራሉ ።

ከልደተ ክርስቶስ በፊት በ800 ዓመት አካባቢ የነበረው ግዋም ገጣሚው ግሪካዊው ሆሜር በግሪክኛ ሥነ ጽሑፍ ስለ ኢትዮጵያውያንና ስለሚኖሩበትም አካባቢ ገልጾአል ።

www.zeyeneta.com

ከሆሜር በኋላ ከልደተ ክርስቶስ በፊት ከ400–300 ዓመት የነበረው የታወቀው ታሪክ ጸሐፊ ሄሮዶቱስም በመጽሐፉ ኢትዮጵያውያን የሚኖሩበት ከግብፅ ደቡብ መለስ የሚገኝና ቀይ ባሕርንም ተከትሎ እስከ ሕንድ ውቅያኖስ የሚደርስ አካባቢ እንደነበርና የእነዚህንም ኢትዮጵያውያን የኑሮ ሁኔታ ሲገልጽ «የዕድሜ ባለጸጋዎች» እንደነበሩ ያመለክታል ።

እንግዲህ በዚህ ሁሉ ገጽታ ኢትዮጵያ በአፍሪካ ክፍለ ዓለም በሰሜን ምሥራቅ አፍሪካ የምትገኝ የረዥም ዘመን ታሪክ ያላት ሀገር ናት ።

ኢትዮጵያ እግዚአብሔርን ሳታውቅ የኖረችበት ጊዜ እንደሌለ ቢታወቅም ንግሥተ ሳባ በታሪክ የሰማችውን የሰሎሞንን ጥበብ ለማየትና በዘመኑ የነበረውን የሀገራችንን ሥልጣኔ ለማስተዋወቅ የብሉይ ኪዳንንም እምነትና ትምህርት ጥበብንም ከመሠረቱ ለመረዳት ወደ ኢየሩሳሌም ባደረገችው ጉዞና በተፈጠረው ግንኙነት ምክንያት የብሉይ ኪዳን እምነትና ጽላተ ሙሴ ወደ አገራችን ገብተዋል ።

ከዚያ ዘመን ጀምሮ ሀገራችን ኢትዮጵያ የብሉይ ኪዳን እምነት ትምህርትና ሥርዓት የሚፈጸምባት የጽላተ ሙሴ መንበር ሆና ትኖራለች። (1ነገሥ· 10፡1–9)

በዚህ የታሪክ የሥልጣኔና የእምነት ግንኙነት ምክንያት ኢትዮጵያውያን ረዥሙንና አድካሚውን የበረሃ ጉዞ በእግርና በእንስሳ ጀርባ እየተጓዙ በዳዊት ከተማ በኢየሩሳሌምና በአካባቢዋ የቦታ ባለ ይዞታ ሆነዋል ። ይህም ለኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆን ለመላው ጥቁር ሕዝብ የታሪክ ኩራትና የሥልጣኔ ምልክት ሆኗል ። የክርስትናውም እምነት በዚሁ የታሪክና የሃይማኖት ግንኙነት መሠረት አምልኮተ እግዚአብሔርን ለመፈጸም ወደ ኢየሩሳሌም በሄደው ኢትዮጵያዊ ጃንደረባ አማካኝነት በ1ኛው ምእት ዓመት ወደ ሀገራችን እንደገባ በማያሻማ ሁኔታ በቅዱስ መጽሐፍ የተገለጠ ነው ። (የሐዋ· 8፡26–39)።

ነገር ግን የቤተክርስቲያኒቱ ሀልውና በኤጲስ ቆጶስ ተባርኮና ተቀድሶ ምሥጢራተ ቤተክርስቲያንን መፈጸም የተጀመረው በ4ኛው መቶ ዓመት ከእስክንድርያው ሊቀ ጳጳሳት ከቅዱስ አትናቴዎስ በተሾመው በቅዱስ ፍሬምናጦስ ነው ። ከእስክንድርያም ጋር የተመሠረተው መንፈሳዊ ግንኙነት በዚሁ ሃይማኖታዊ ታሪክ መነሻነት ነው ።

ኢትዮጵያ ከልደተ ክርስቶስ በፊት በሙሴ ሕግ ከጊዜ በኋላም ሐዲስ

www.zeyeneta.com

ኪዳኑን በመማር በማስተማር በእነዚህ ሁለት ዓበይት ሕግጋት በቅደም ተከተል ስመ እግዚአብሔርን በመጥራት ፣ ሕገ እግዚአብሔርን በመጠበቅ አምልኮቱንም በመፈጸም ስትመራ የቆየች የሃይማኖት ሀገር ስትሆን የዕድገቷም ዓላማና አቋም በዚሁ ዓይነትና መጠን የተገነባ ሆኖ ከአንዱ ትውልድ ወደ ተከታዩ ሲወርድና ሲወራረስ መጥቶ አሁን ከአለበት ደረጃ ላይ ደርሶ ይታያል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የኬልቄዶንን ጉባኤ ከማይቀበሉት የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት አንዷ ናት ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ፣

ሀ) ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሠራውን ፣

ለ) ሐዋርያት ያስተማሩትን ፣

ሐ) በሦስቱ ጉባኤያት የተወሰኑትን ማለት በመንፈስ ቅዱስ አጋዥነት እየተመሩ

318 ቅዱሳን አበው በ325 ዓ·ም· በኒቅያ ፣ 150 ቅዱሳን አበው በ381 ዓ·ም· በቍስጥንጥንያ ፣

200 ቅዱሳን አበው በ431 ዓ·ም· በኤፌሶን ያስተማሩትንና የወሰኑትን ፣

ከእነዚህም ቅዱሳን አበው ትምህርትና ውሳኔ ጋር የሚተባበሩ በየጊዜው የተነሡ ቅዱሳን አበው ያስተማሩትንና የእነርሱንም የተቀደሰ ሥርዓታቸውን አምናና ተቀብላ ታስተምራለች ።

ከ4ኛው መቶ ዓመት እስከ 7ኛው መቶ ዓመት የነበረው ጊዜ አርኪ የቤተክርስቲያን ታሪክ የተፈጸመበት አንድ ወቅት ነበር።

ይህም ጊዜ ቅዱሳት መጻሕፍት ከፅርዕና ከመላለሉት ጥንታውያን የሥልጣኔ ቋንቋዎች ወደ ግዕዙ ብሔራዊ ቋንቋ የተተረጐሙበት ፣ ገዳማዊ ሕይወት ፣ የተመሠረተበት ፣ የቤተክርስቲያናችን የውዳሴ ፣ የቅዳሴ ፣ የዝማሬ ፣ የዜማ ስልቶች በፈቃደ እግዚአብሔር በኢትዮጵያዊው አባት በቅዱስ ያሬድ የተደረሱበት የሥነ ጽሑፍ ውበት የታየበት ወቅት ነበር ።

በ7ኛው መቶ ዓመት ሰሜን አፍሪካና በከፊል መካከለኛው ምሥራቅ በሰለሙ ዓረቦች በመወረሩና ይህም ሁኔታ ከጊዜ በኋላ በቀይ ባሕር

www.zeyeneta.com

አካባቢ ቀይ ባሕርን ተከትሎ እስከ ሕንድ ውቅያኖስ እየሰፋ በመምጣቱ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ከክርስትናው ዓለም ጋር የነበራት ግንኙነት ተቋረጠ ።

በ9ኛው መቶ ዓመት በኢትዮጵያ የክርስትናው ታሪክ ተቃዋሚ ሆና በተነሣችው በዮዲት (በጉዲት) ቤተክርስቲያናችን ብዙ ቅርሶችን አጥታለች ። የብዙ ሰዎችም ሕይወት ጠፍቷል ።

ከ10ኛው እስከ 15ኛው ክፍለ ዘመን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በ9ኛው መቶ ዓመት የተደመሰሰውን ታሪኳን መልሳ በማደስና በአሠራራቸውም በዓለም ተወዳዳሪ የሌላቸው አብያተ ክርስቲያናት የታነጹበት ስብከተ ወንጌል በመላ ሀገሪቱ የተስፋፋበት ገዳማዊ ሕይወት በበለጠ የታደሰበት ሥነጽሑፍ የዳበረበት አምልኮተ ባዕድ የጠፋበት ቅዱሳት መጻሕፍት ከዓረብኛ ወደ ግዕዝ ቋንቋ በብዛት የተተረጐሙበት ጊዜ ነበር ።

16ኛው ክፍለ ዘመን በኦቶማን ኢምፓየር ደጋፊነት በሀገሩ ላይ ያመፀው የውስጥ ጠላት የሆነው ግራኝ መሐመድ በቤተክርስቲያናችንና በሀገራችን ህልውና ላይ ከባድ ጉዳትን ያደረሰበት ወቅት ነበር ። ይህም ዘመን በኢትዮጵያ ታሪክ የጨለማው ዘመን በመባል የታወቀ ነው ። በዚያን ጊዜ ግራኝ መሐመድ ከምሥራቅ ኢትዮጵያ ተነሥቶ ወደ መሐል ኢትዮጵያ በመምጣት ከዚያም ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ በማምራት በሀገሪቱ የነበረውን የክርስትና ታሪክ ደምስሶ የድጋፍ ሰጭውን የኦቶማን ኢምፓየር አገዛዝን ለመተካት ነበር ፣ ግን በጊዜው የነበረው ኢትዮጵያዊ ትውልድ በሃይማኖቱ የጸና ፣ በሥነ ምግባሩ የተዋበ ፣ በሀገር ፍቅር የነደደ በመሆኑ ያን የውስጥ ጠላት ኢብራሂም ግራኝ መሐመድን ከነሠራዊቱ በእግዚአብሔር ኃይል በመደምሰስ ድልን ተቀዳጅቷል ።

በ16ኛው ክፍለ ዘመን ግራኝ መሐመድ ያደረሰው ጥፋትና እልቂት የ15 ዓመታት የመከራ ዘመን ቢሆንም በኢትዮጵያ ታሪክ በአጥፊነቱ ተወዳዳሪ የማይገኝለት ዘመነ ሰማዕታት ነበር ።

በግራኝ መሐመድ ወረራም ወቅት በርዳታ መልክ ከመጡት የፖርቱጋል ወታደሮች ጋር ተሰባጥረው የመጡ ጀሱዊት መነኮሳትም እንደነበሩ ታሪክ ያስታውሰናል ። በነዚህም መነኮሳት ምክንያት በሀገራችን ብዙ ደም ፈሷል ።

www.zeyeneta.com

ከ18ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ እስከ 19ኛው መቶ ዓመት አጋማሽ ድረስ ለአንድ መቶ ዓመት ያህል በተራዘመው ዘመን መሳፍንት ቤተክርስቲያናችን ያጋጠማትን ፈተና ሁሉ አልፋ ፣

ሀ) የቅኔና የሰዋስው ሥነ ጽሑፍ ማእከላት የሆኑ ትምህርት ቤቶችን ፣

ለ) የትርጓሜ መጻሕፍት ጉባኤያትን ፣

ሐ) የጸዋትወ ዜማ ትምህርት ቤቶችን በማስፋፋትና በማጠናከር ርምጃዋ ሳይታጠፍ እንደገና በ19ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ላይ በአፄ ቴዎድሮስ አነሣስ የሀገሪቱ አንድነት ተጠብቆ ወደሚቀጥለው ዐረፍተ ዘመን ለመሸጋገር በቅታለች ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በማንም ሰው ዓይን መታየት ያለባት በታሪካዊነቷ ብቻ ሳይሆን በአፍሪካ ቀንድ ለእግዚአ ብሔር መንግሥት ጽናት የራሷ የሆነ የክርስትና ታሪክ በማቈየቷና ለሀገር አንድነትና ነጻነት በአደረገችውም መሥዋዕትነት ጭምር መሆን አለበት።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በዚህ ረጅም የታሪክ ዘመን ለሃይማኖቷ ለነጻነቷ ፣ ለሀገር ዕድገት ፣ ለጎብረተሰብ አንድነት ከፍተኛ መሥዋዕትነትን የከፈለች መሆኑ ግልጽ ነው ። ይህን ሁሉ ታሪክ ሁሉም ሰው እንዲያውቀው ማድረግም ተገቢ ነው ።

በየጊዜው የኢትዮጵያን ገጽታ ለማጥፋትም ሆነ ኢትዮጵያን ለመውረር የፈለጉና የሚፈልጉ ክፉዎች ኃይላት ሁሉ ለዓላማቸው መሳካት በመጀመሪያ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያንን መደምሰስ ወይንም በተለያየ ምክንያት ማዳከም ነበር ።

በ19ኛው ክፍለ ዘመን የአውሮፓውያንን ሥልጣኔ ወደ ኢትዮጵያ ለማስገባት ከፍተኛ ጥረት ተደርጎ ነበር ።

የአውሮፓ ኃያላን መንግሥታት ኢትዮጵያ የአፍሪካ የሥልጣኔ ማእከል እንዳትሆን በስውር ተስማምተው ተባብረው በ19ኛው ክፍለ ዘመን ፍጻሜ አካባቢ የኢጣሊያ ወረራ በኢትዮጵያ ላይ እንዲፈጸም ሆነ ። በሃያኛው ክፍለ ዘመንም ሞሶሎኒ ኢትዮጵያን በቅኝ ገዥነት ለመያዝ በተነሣ ጊዜ ለዓላማው መሳካት በኢትዮጵያ በመጀመሪያ መደምሰስ ከአለባቸው አንዷ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን

www.zeyeneta.com

እንደነበረች ታሪክ ያስረዳናል ። ይህም ከ1928 እስከ 1933 ዓ·ም· ድረስ በተደረገው ወረራ በተግባር የታየ ነው ። ይሁን እንጂ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የደረሰባትን ጥፋትና ጥቃት ተቋቁማና እንደገና አንሠራርታ የኢትዮጵያን ታሪክ አደራጅታ ወደ ነበረበት መልሳ ሕዝብ በማገልገል ላይ ትገኛለች ።

ሃያኛው ክፍለ ዘመን እንደ 5ኛው ፣ 11ኛውና 16ኛው ክፍለ ዘመን የመለያያ ፣ የመወጋገዣና የግጭት ሳይሆን የራስን ዓላማ ሳይለቁ ተቀራርቦ በመወያየት ለችግሩ መፍትሔ የሚሰጥበት ነው ።

በ5ኛው መቶ ዓመት «ከሁሉ በላይ የምትሆን ሐዋርያት የሰበሰቧት አንዲት ቅድስት ቤተክርስቲያን» ከሁለት መከፈል በቤተክርስቲያን ታሪክ እጅግ በጣም የሚያሳዝን ነበር ።

በመሠረቱ የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን አንዲት ናት ። ሰዎችም እንደየፍላጐታቸው በየጊዜው ሊከፋፍሏት አይችሉም ። ይሁንና ቤተክርስቲያናችን በኢኩሚኒዝም መንፈስ የምትሳተፍባቸው ዓለም አቀፍ የክርስትና መድረኮች አሏት ።

የኬልቄዶንን ጉባኤ ከማይቀበሉት የኦሪየንታል ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት አንዷ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን መሆንዋን ከላይ ገልጸናል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ከኦሪየንታል ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ጋር ያላትን የሃይማኖት አንድነት አጽንታና አክብራ የያዘች ስትሆን የምትመራውና የምትተዳደረውም ከሐዋርያት በተገኘው ትውፊት መሠረት በቅዱስ ሲኖዶስ ነው ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከቀደምት ነቢያት ጀምሮ ለሃይማኖት አባቶችና ለቤተክርስቲያን መሪዎች በነበራት ፍቅርና መንፈሳዊ አክብሮት የእስክንድርያ ቤተክርስቲያን «የኒቅያ ጉባኤ ውሳኔ ነው» ብላ በጻፈችው የተንኮል ድንጋጌ ለአንድ ሺህ ስድስት መቶ ዓመታት ከራስዋ ልጆች ሳትሾም ከእስክንድርያ ጳጳሳትን እየተቀበለች ስታስተናግድ ኖራለች ።

ቤተክርስቲያኒቱ ለ1600 ዓመታት በእስክንድርያ ቤተክርስቲያን ሥር በኖረችበት ጊዜ ከግብጽ የሚመጡት ጳጳሳት የእኛን ቋንቋ ካለማወ

www.zeyeneta.com

ቃቸው እኛም የእነርሱን ቋንቋ ካለማወቃችን የተነሣ ባለመግባባት ብዙ ድክመት ታይቷል ።

የክርስትና እምነት እስከ ጕረቤት የመላው አፍሪካ አህጉር ሊዳረስ ሲችል በሀገር ውስጥ እንኳ እንደሚገባ አልተስፋፋም ። ቀድሞ ከነበሩት ት/ቤቶች በቀር ትምህርት ቤቶች በከፍተኛ ደረጃ አልተቋቋሙም ያን ጊዜ በነበረው የግብጻውያኑ ተጽዕኖም ምክንያት የውጭ ግንኙነታችን በሰፊው አልተዘረጋም ።

ከዚህም ከባድ የአስተዳደር ተጽዕኖ ለመላቀቅ የሰው ኃይል ፣ የጊዜና የብዙ ሀብት መሥዋዕትነት ተከፍሎአል ።

ከሺህ ስድስት መቶ ዓመታት በኋላም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በብዙ ትግልና ፈሊጥ ከራስዋ ልጆች መርጣ ለመሾም የምትችልበትን መንፈሳዊ መብትና ነጻነት በማስገኘትና የራስዋ ባለቤት ለመሆን በማብቃት ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ታሪክና ትውልድ የማይረሳው ገድል ፈጽመዋል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ለመንበረ ማርቆስ ያላት አክብሮት የተጠበቀ ቢሆንም በግብጽ ቤተክርስቲያን መሪዎች በየጊዜው የሚፈጠረው የበላይነት ስሜት በሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት መካከል ያለውን ግንኙነት እያሻከረ ነው ።

ተፈላጊ ያልሆነ ይህ አይነቱ ቅራኔ እንዲቀር በየጊዜው ቢሞከርም በኢየሩሳሌም የሚገኘውን የቦታ ይዞታችንን ለማሳጣት የሚደረገው ሴራ ቤተክርስቲያናችንን እያሳዘነ ነው ።

ይሁን እንጂ ቤተክርስቲያን በክርስቶስ ደም የተመሠረተች አሐቲ እንደ መሆንዋ መጠን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በተሠማራችበት አቅዋምዋ ጸንታ እምነትዋንና ሥርዓትዋን ከማስፋፋት የሚያግዳት አይኖርም ።

የሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት ግንኙነትም በመንፈሳዊ አመለካከት እየተመረመረ ወደፊት የተሻለ መልክ እንደሚኖረው ተስፋ ታደርጋለች ፣ ምኞትዋም ጸሎትዋም ነው ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በሀገር ውስጥ 32 አህጉረ ስብከት ያሏት ሲሆን ፣ በውጭ ሀገርም በኢየሩሳሌም ፣ በካሪቢያን


www.zeyeneta.com

ደሴቶችና በላቲን አሜሪካ ፣ በአሜሪካ ፣ በአውሮፓ ፣ በአፍሪካ ፣ በካናዳና በአውስትራሊያ አህጉረ ስብከት አሏት ።

የኢየሩሳሌሙ ይዞታ ከልደተ ክርስቶስ በፊት ጀምሮ ከብሉይ ኪዳኑ እምነት ጋር በነበረው ግንኙነት ተያይዞ የመጣ የታሪክ ይዞታ ነው ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን 40,000,000 (ዐርባ ሚልዮን) ምእመናን 400,000 (ዐራት መቶ ሺህ) ካህናት ፣ 30,000 (ሠላሳ ሺህ) የሰበካ አብያተ ክርስቲያናት አሏት ።

በዚህም ሁሉ ከመንበረ ፓትርያርክ እስከ አጥቢያ ቤተክርስቲያን በዘረጋችው የአስተዳደር መዋቅር በቃለ ዓዋዲው ደንብ መሠረት መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎትዋን በስፋት ታበረክታለች ።

www.zeyeneta.com



www.zeyeneta.com

መግቢያ

በነቢያትና በሐዋርያት መሠረትነት ላይ የታነጸችው ጥንታዊት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ከአበው የተቀበለችውን እምነት ፣ ትምህርትና ትውፊት ጠብቃ በቃልና በጽሑፍ እያስፋፋች ከትውልድ ወደ ትውልድ ስታስተላልፍ ቆይታለች ።

እምነትዋን ፣ ትምህርትዋንና ሥርዓትዋን ፣ ታሪኳንና ትውፊትዋን የሚገልጹ መጻሕፍትን በየጊዜው እያዘጋጀች ለሕዝብ ታቀርባለች ። በመላ አገሪቱ የሚገኙ መምህራንና ሊቃውንትም የቤተክርስቲያኒቱ እምነትና ሥርዓት የሚጠበቁበትን መንፈሳዊ አገልግሎት በቃልም በጽሑፍም ሲያበረክቱ ኖረዋል ፣ በማበርከትም ላይ ናቸው ።

በክርስቶስ ደም ለተዋጀችው ለዚች ቤተክርስቲያን ህልውና የበላይ ጠባቂ የሆነው ቅዱስ ሲኖዶስም አደራውንና ኃላፊነቱን በተግባር ለመወጣት የሚያደርገው ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተጠናከረ በመምጣት ላይ ነው ። ይህንኑ በተመለከተ በቅርቡ ተዘጋጅተው ለሕዝበ ክርስቲያኑ የተሠራጩ የሕግና የሥርዓት የሃይማኖትም መጻሕፍት ከሁሉም ጊዜ በበለጠ ለሚያረገው እንቅስቃሴ በጥሩ ምሳሌነት ሊጠቀሱ የሚችሉ የሥራ ውጤቶች ናቸው ። የቤተክርስቲያኒቱን እምነትና ትምህርት ፣ ታሪክና ትውፊት የሚመለከቱ ለምእመናን ጠቃሚ የሆኑ መጻሕፍትን አሁንም በብዛትና በስፋት እያዘጋጀ የማሠራጨት ዕቅዱ ቀጥሎአል ። በዚህም መሠረት ይህ በመጠኑ አነስተኛ የሆነ በይዘቱ ግን ጥልቅ መልእክት ያለውና የቤተክርስቲያኒቱን እምነት ፣ ትምህርትና ሥርዓተ አምልኮት ጠቅለል ባለ መልኩ የያዘ መጽሐፍ ተዘጋጅቷል ።

መጽሐፉ ከትምህርተ ሃይማኖቱና ሥርዓተ አምልኮቱ ጋር ቤተክርስቲያኒቱ ከጐረቤትና ከውጭው ዓለም ጋር ያላትን የቆየ የወዳጅነት ፣ የተራድኦና የሰላም ግንኙነት በሰፊው ይገልጣል ።

በአሁኑ ጊዜ ስለ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን መንፈሳዊ አቅዋም ፣ ይዘትና እንቅስቃሴ ለማወቅ የሚሹ ብዙዎች ናቸው። ይልቁንም ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ በአሁኑ ጊዜ የቤተክርስቲያኒቷን ዕድገት ለማጠናከር ከአኃት አብያተ ክርስቲያናት ጋር የበለጠ መቀራረብና መገናኘት ፣

www.zeyeneta.com

ከምሥራቅ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንም ጋር የተራድኦ ግንኙነት እንዲኖር በሚያደርጉት ከፍተኛ ጥረት የቤተክርስቲያኒቱን እምነትና ትምህርት ፣ ትውፊትና ታሪክ አጠር ባለ ዝግጅት ፣ ጥርት ባለ አጻጻፍ አዘጋጅቶ ማቅረብና ማሳወቅ እጅግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ቅዱስነ ታቸው በሰጡት መመሪያ መሠረት ይህ የእምነትና ሥርዓተ አምልኮት መጽሐፍ በቅዱስ ሲኖዶስ አባላትና በቤተክርስቲያኒቱ ምሁራን ቅንጅት ተዘጋጅቶ በቅዱስ ሲኖዶስ ተመርምሮ እንዲታተም ተደርጓል ።

www.zeyeneta.com

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን

ክፍል ፩

እምነት

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ትምህርት ከሁሉም ቅድሚያ የሚሰጠው ሃይማኖት ነው ፡ ቤተክርስቲያኒቱ ያለ ሃይማኖት እግዚአብሔርን ማገልገል እንደማይቻል ታምናለች ። የእግዚአብሔርም መንግሥት የሚወረሰው በሃይማኖት መሆኑን ለምእመናን ታስተምራለች ።

ምዕራፍ ፩

ሀልዎተ እግዚአብሔር (የእግዚአብሔር መኖር)

እግዚአብሔር የሚለው ስም የባሕርይ ስም ነው ። ትርጉሙም ዓለምን ፈጥሮ የሚገዛ ማለት ነው ።

የማይታይና የማይመረመር ሁሉን ማድረግ የሚችል ሁሉንም የፈጠረ መጀመሪያና መጨረሻ የሌለው ዘለዓለማዊ አምላክ መኖሩና ራሱን ለሰው ልጆች እንደገለጠ በቅዱሳት መጻሕፍት ተረጋግጧል ። (ዘጸአ·3፡6)

የዚህን ዘለዓለማዊ አምላክ መኖር ከሚያስረዱን የአእምሮ ማስረጃዎች ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው ።

ፍጥረት፡-የሰው ልጅ የእግዚአብሔርን መኖር ለመረዳት ብዙ ተመራምሮአል። በምርምሩም የእግዚአብሔርን መኖር ወደማወቅ የሚያደርሱ መንገዶችን አግኝቶአል ። ለማንኛውም ነገር ምክንያት አለው ። ለሥዕል ሠዓሊ ፡ ለመጽሐፍ ጸሐፊ ፡ ለወንበር ጠራቢ አለው ።

www.zeyeneta.com

ለሚንቀሳቀስ ነገር ሁሉ አንቀሳቃሽ አለው ። በዚህ መሠረት ፥ "ፍጥረት ያለፈጣሪ የተገኘ አይደለም" ወደሚለው እምነት ተደርሶአል ። ፍጥረት ሁሉ ከታናሹ ጀምሮ እስከ ታላቁ ፥ አእምሮ ከሌለው ጀምሮ ከፍተኛ አእምሮ እስካለው ድረስ የእግዚአብሔርን መኖር ወደማወቅ ይመራል ፥ ስለዚህም ሰሎሞን "እግዚአብሔርን የማወቅ ጉድለት በልባቸው ያለባቸው ሰዎች ሁሉ በእውነት ከንቱ ናቸውና በእነዚህ በሚታዩ ፍጥረቶቹ በዚህ ዓለም የሚኖር እርሱን ያውቁ ዘንድ ተሳናቸው ፥ ሥራውንም እያዩ ፈጣሪያቸውን አላወቁም ፥ ..... ፀሐይና ጨረቃን አይተው የፈጠራቸውን ይወቁ..." (ጥበብ 13፡1–10) ይላል ። ኢዮብም "እንስሶችን ጠይቅ ያስተምሩሃልና ። የሰማይንም ወፎች ጠይቅ ይነግሩሃልና ። ወይም ለምድር ተናገር እርስዋም ታስተምርሀለች ፥ የባሕርም ዓሣዎች ይነግሩሀል ፥ የእግዚአብሔር እጅ ይህን እንዳደረገ ፥ ከእነዚህ ሁሉ ይህን የማያውቅ ማን ነው?" ብሏል (ኢዮብ 12፡7–9) ። ቅዱስ ዳዊትም በመዝሙር 18፡1–2 "ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ የሰማይ ጠፈርም የእጆቹን ሥራ ያወራል" በማለት ተናግሮአል ።

ታላቁ ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስም ከዚህ ግልጥ በሆነ ሁኔታ እግዚአብሔር በፍጥረቱ ለፍጥረቱ እንደሚታወቅ ሲያስረዳ እንዲህ ይላል። "ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ታይቶ የማይታወቅ እግዚአብሔር ለፍጥረቱ በሥነ ፍጥረት ይታወቃል ።" (ሮሜ 1፡19–20)።

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ይህን የሐዋርያውን መልእክት በተረጐመበት ድርሳኑ እንዲህ ይላል "እግዚአብሔር ገናናነቱ በሥራው ይታወቅ ዘንድ ሁሉን ካለመኖር ወደ መኖር አመጣ ። ነፍስ በሰው ውስጥ እንደማትታይ ግን በሰውነት እንቅስቃሴ እንደምትታወቅ እግዚአብሔርም በሥጋዊ ዐይን አይታይም ግን በፈቃዱና በሥራው ይገለጣል ፥ ይታወቃልም ። በባሕር ላይ ተንሳፍፉ ወደፊት የምትጓዝ መርከብን የሚመለከት ሰው በውስጥዋ የሚመራት ነጂ እንዳለ ማወቅ አለበት እንደዚሁም ምንም በዓይነ ሥጋ ባይታይ ሁሉንም የሚመራ እግዚአብሔር እንደሆነ ማስተዋል ይገባዋል ። (የዮሐንስ አፈወርቅ ትርጓሜ ፥ ሮሜ 1፡19–20) ።

<u>ልቡና</u>፡– "ሕግ የሌላቸው አሕዛብ ከባሕርያቸው የሕግን ትእዛዝ ሲያደርጉ እነዚያ ሕግ ባይኖራቸው እንኳ ለራሳቸው ሕግ ናቸውና

www.zeyeneta.com

እነርሱም ልቡናቸው ሲመሰክርላቸው አሳባቸውም እርስ በርሱ ሲካሰስ ወይም ሲያመካኝ በልባቸው የተጻፈውን የሕግ ሥራ ያሳያሉ።'' (ሮሜ 2፡ 14–15)። ሰው በልቡናው ውስጥ ባለው መንፈሳዊ ሕግ አነሳሽነት መልካም ይሠራል ከክፉም ይርቃል ። ተላልፎ ክፉ ቢሠራም እንኳ ሕሊናው ይወቅሰዋል ። መልካም የሚሠራ ዋጋ እንደሚያገኝ ክፉ የሚሠራም እንደሚቀጣ ይኸው ሕሊናው ይመሰክርበታል ። ይህ ዓይነቱ ሕሊና ለደግም ሆነ ለክፉ እንደሥራው ዋጋ የሚከፍል አንድ አምላክ መኖሩን ወደ ማወቅ ይመራል ።

ታሪክ፡– በዚህ ዓለም አምልኮት የሌለው ሕዝብ እንዳልኖረ የሰው ልጅ ታሪክ ያስረዳል ። ከጥንት ጀምሮ እስከ አለንበት ዘመን ድረስ የአልምኮቱ ዓይነት ይለያይ እንጂ ሁሉም በየወገኑ ባዕድ አምላክ ወይም ብዙዎች አማልክትን ያመልካል ። ይህም ሁሉ የሚያሳየው የእንድ እውነተኛ አምላክ መኖርን ነው ። እግዚአብሔር ባይኖር ሰው ይህን የአምልኮት ጠባይ ከየት ሊያገኝ ቻለ? (የሐዋ·14፡11–16 ፣ 17፡26–29) ።

በቅዱሳት መጻሕፍት ስለ እግዚአብሔር መኖር በሰፊው ከመነገሩም በላይ ስለ እርሱ የተሰጡ መግለጫዎች አሉ ። እነርሱም የሚከተሉት ናቸው ።

ቅድስና፡– እግዚአብሔር ቅዱስ ነው ፣ ከክፉ ወይም ከርኩስ ነገር ጋር ምንም ግንኙነት የለውም ። እርሱ ራሱ ''እኔ ቅዱስ እንደሆንሁ እናንተም ቅዱሳን ሁኑ'' ሲል ተናግሮአል ። (ዘሌዋ 19፡2 ። 1ጴጥ·1፡16) ። ሁልጊዜ በመላእክት ቅዱስ ፣ ቅዱስ ፣ ቅዱስ ፣ እየተባለ ሲመሰገን ይኖራል (ኢሳ·6፡3) ።

ፍቅር፡– እግዚአብሔር ፍቅር በመሆኑ ፍጥረቱን ይወዳል መልካም የሆነውን ነገር ሁሉ ለፍጥረቱ ይሰጣል ።

እግዚአብሔር ፍቅር መሆኑ በወንጌላዊው ዮሐንስ ወንጌልና መልእክታት ተደጋግሞ ተገልጦአል ። (1 ዮሐ· 4፡8) በኋላም ሰው መሆኑ ፍቅሩን ያመለክታል ። (ዮሐ·3፡16 ። ሮሜ 5፡5)።

ጽድቅ፡– እግዚአብሔር በሁሉ እውነተኛ ነው ፣ በእውነተኛነቱ ለሁሉ በትክክል ይፈርዳል ፣ (1 ሳሙ 2፡2፣2 ጢሞ 4፡8) ዮሐንስ በራእዩ 16፡7 ''አዎ ጌታዬ ሁሉን የምትገዛ ፍርድህ እውነተኛና የሚገባ ነው'' ይላል ።

www.zeyeneta.com

ጥበብ፡– ፍጥረትንና የፍጥረቱን ሥነ ሥርዓት ክንውን ስንመለከት የእግዚአብሔርን ፍጹም ጥበብ እንረዳለን ። ነቢዩ ዳዊት እግዚአብሔር በጥበብ የሠራውን ሁሉ በማድነቅ እንዲህ ይላል ። "አቤቱ ሥራህ እጅግ ብዙ ነው ሁሉን በጥበብ አደረግህ" (መዝ፡ 103፡24)።

ከአንድ እስከ አራት ክተመለከትናቸው የባሕርዩ መግለጫዎች የተለዩ ሌሎች የግዚአብሔር የባሕርዩ መግለጫዎች አሉ ።

ሁሉን ቻይነት (ከሃሌ ኩሉ) ፡– ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር ፈጽሞ የለም ፡ ሁሉን ማድረግ ይችላል ፡ እግዚአብሔር ራሱ ለአብርሃም "ሁሉን ቻይ ነኝ" ብሎ ገልጦለታል ። (ዘፍ· 17፡1። 18፡14 ። ሉቃ 1፡37)

ሁሉን ማወቅ፡– እግዚአብሔር ሁሉን ነገር ከመሆኑ በፊት ያውቀዋል። ነገሮችን ሁሉ ከመታሰባቸውና ከመሠራታቸው በፊት ያውቃቸዋል ። (መዝ 138፡2፡ ዮሐ·2፡25) ።

ምሉዕነት፡– እግዚአብሔር በቦታና በጊዜ አይወሰንም በየትም ቦታ አለ ፡ ምንም እንኳን ስለ ልዕልናው በሰማይ እንደሚኖር ቢነገርም በሰማይ ብቻ አይወሰንም ። ቅዱስ ዳዊት እንዲህ ይላል "ከመንፈስህ ወዴት እሄዳለሁ? ከፊትህስ ወዴት እሸሻለሁ? ወደሰማይ ብወጣ አንተ በዚያ አለህ ወደ ሲኦልም ብወርድ በዚያ አለህ…" (መዝ 138፡7–10 ። ኤር 23፡23 ሠለስቱ ምእት ቅዳሴ)

ዘለዓለማዊነት፡– እግዚአብሔር በዘመናት አይወሰንም ፡ ከዘመን በፊት ነበረ ፡ ዘመናትንም አሳልፎ ይኖራል ። (መዝ 89፡ 1–2) በጠቅላላ አነጋገር እግዚአብሔር መጀመሪያና መጨረሻ የለውም ራሱ መጀመሪያና መጨረሻ ነው በእርሱ ዘንድ ለውጥ የለም ። (ኢሳ 44፡6 ። ያዕ 1፡17)

www.zeyeneta.com

ምዕራፍ ፪

ሥነ ፍጥረት ፥

ቅዱስ መጽሐፍ የእግዚአብሔርን መኖር በማረጋገጥ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ በማለት ይጀምራል ። (ዘፍ·1፡1) ቅዱስ ጳውሎስም በዕብራውያን መልእክቱ 3፡4 ላይ "ሁሉን የፈጠረ እግዚአ ብሔር ነው" ይላል ።

እግዚአብሔር ሁሉን አስገኘ ፣ ለሁሉ ነገር መገኛ ጥንትና መሠረት ነው ። ለእርሱ ግን ለህላዌው ምክንያት የለውም ። (የሐዋርያት ጸሎተ ሃይማኖት) እግዚአብሔር ይህን የሚታየውንና የማይታየውን ዓለም በውስጣቸውም ያሉትን ሁሉ ከቸርነቱ ብዛት የተነሣ ፈጠረ ። (ኢሳ·42፡5) ።

እግዚአብሔር ይህን ዓለም ካለመኖር ወደ መኖር ያስገኘው "ለይኩን" ባለው ቃሉ ብቻ ነው ። ይህ ዓለም ከመፈጠሩ በፊት ምንም ነገር አልነበረምና (ጥበበ ሰሎሞን 11፡17 ። 1 መቃብ 27፡1 ቅዱስ ጳውሎስም "ዓለሞች ሁሉ በእግዚአብሔር ቃል እንደተፈጠሩ ስለዚህም የሚታየው ነገር ከሚታዩት እንዳልሆነ በእምነት እናስተውላለን" (ዕብ 11፡3) በማለት እግዚአብሔር ፍጥረትን ካለመኖር ወደ መኖር አምጥቶ መፍጠሩን አስረድቷል ።

ፈጣሪ ፍጥረታት እግዚአብሔር ሥነ ፍጥረትን በየመልኩና በየወገኑ መፍጠሩ ክብሩ ይገለጥበትና ስሙ ይቀደስበት ዘንድ ነው ። ይህንም ነቢዩ ኢሳይያስ "ፍጥረታትን ሁሉ ለክብሬ ፈጠርኋቸው አለ እግዚአብሔር" ብሎ ተናግሮአል ። (ኢሳ·43፡7)

ፍጥረታት ሁሉ በየወገናቸው ከዕለተ እሑድ እስከ ዕለተ ዓርብ ባሉት ስድስት ቀናት በቅደም ተከተል መፈጠራቸውን ቅዱስ መጽሐፍ ይናገራል ።

እነዚህም በስድስቱ ዕለታት የተፈጠሩ ፍጥረታት በየወገን በየወገ ናቸው ተቆጥረው ሃያ ሁለት መሆናቸውን መጽሐፈ ኩፋሌ ይናገራል ።

www.zeyeneta.com

(ዘፍ 1፡1–31) ኩፋሌ ፡ 3 ፡9) በየዕለቱ የተፈጠሩት ፍጥረታትም በሚከተለው ሁኔታ የተገለጡት ናቸው ።

ሀ) <u>የእሑድ ፍጥረታት</u>

1· እሳት

2· ነፋስ

3· ውሃ

4· መሬት (ዐራቱ ባሕርያት)

5· ጨለማ

6· ሰባቱ ሰማያት

7· መላእክት

8· ብርሃን ናቸው (ኩፋሌ 2፡5–8 ዘፍ· 1፡1–5) ።

ለ) <u>የሰኞ ፍጥረት</u>

በምድር ላይ ሞልቶ የነበረው ውሃ ተከፍሎ ጠፈር ተገለጠ (ዘፍ 1፡6–8 ። ኩፋሌ 2፡9 ። ዘፍ 1 ፡9)

ሐ) <u>የማክሰኞ ፍጥረት</u>

1· በጣት የሚለቀሙ አትክልት

2· በማጭድ የሚታጨዱ አዝርዕት ።

3· በምሣር የሚቆረጡ ዕፀዋት ናቸው ። (ዘፍ 1፡11–13 ።)

መ) <u>የረቡዕ ፍጥረታት</u>

1· ዐሐይ

2· ጨረቃ

3· ከዋክብት ናቸው (ዘፍ·1፡14–16)

ሠ) <u>የሐሙስ ፍጥረታት</u>

በደመ ነፍስ የሚንቀሳቀሱ ከባሕር ውስጥ ፡

1· በደረት የሚሳቡ

2· በእግር የሚያኮበኩቡ

3· በክንፍ የሚበሩ እንስሳት ፡አራዊትና አዕዋፍ ናቸው ፡ (ዘፍ 1፡20–22)።

www.zeyeneta.com

ረ) <u>የዐርብ ፍጥረታት</u>

በደመ ነፍስ ሕይወት የሚንቀሳቀሱ በየብስ የሚኖሩ ፡

1· ዘመደ እንስሳ ፡

2· ዘመደ አዕዋፍ ፡

3· ዘመደ አራዊት ፡

4· በነባቢት ነፍስ የሚንቀሳቀስ ሰው ናቸው (ዘፍ 1፡24–28)።

እነዚህን ሁሉ ፍጥረታት በየወገኑ ከፈጠራቸው በኋላ መልካም እንደሆኑ አይቶ እግዚአብሔር በሥራው ደስ አለው እንዲበዙም ባረካቸው። (ዘፍ 1፡21 ። መዝ 103፡31)።

የሰው ተፈጥሮ

እግዚአብሔር ከዕለተ እሑድ እስከ ዕለተ ዐርብ ያሉ ፍጥረታትን በየዓይነታቸው ከፈጠረ በኋላ ሰውን የእነዚህ ሁሉ የበላይ ገዢ አድርጎ በመልኩና በአርአያው ፈጠረው ፡ በደመ ነፍስ ሕይወት ከሚኖሩ ፍጥረታት የምትለየውን ነባቢት ፡ ለባዊትና ሕያውት ነፍስን በውስጡ አሳደረበት ። ወንድና ሴትም አደረጋቸው "ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሉአት ግዙአትም" ብሎ ባረካቸው ። (ዘፍ 1፡26–28) ። በእግዚአብሔር አርአያና ምሳሌ የተፈጠረው ሰው ባለ አእምሮ ፍጡር ነው ።

<u>7ኛ ቀን</u>፡– እግዚአብሔር በሰባተኛው ቀን ከመፍጠር ሥራው ዐረፈ። ስለዚህም ሰባተኛይቱን ቀን የዕረፍት ቀን እንድትሆን ባረካት ቀደሳትም" ተብሎ ተጻፈ ። (ዘፍ2፡3) ።

ስለዚህ እግዚአብሔር የፍጥረታት ሁሉ አስገኝና ባለቤት ነው ። እግዚአብሔር ዓለምን በሥልጣኑ ማስገኘት ብቻ ሳይሆን መጋቢው ፡ መሪውና ጠባቂውም ነው ። (መዝ 103፡27–31 ። 1ቆሮ· 3፡22። 15፡28። የሐዋ· 14፡17) ።

www.zeyeneta.com

ምዕራፍ ፫

አምስቱ አዕማደ ምሥጢር

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን መሠረተ እምነ ትዋን የምትገልጥባቸውና የምታስተምርባቸው አምስት አዕማደ ምሥጢር አሏት ። አዕማድ ማለትም ምሰሶዎች ማለት ነው ። የምሥጢር ምሰሶዎችም የተባሉበት ምክንያት ቤት በምሰሶ ተደግፎ እንደሚጸና ምእመናንን በትምህርተ ሃይማኖት ያግፈው የሚያጸኑ ስለሆነ ነው ። እነዚህም አምስቱ አዕማደ ምሥጢር መጽሐፋዊ መሠረት ያላቸው ናቸው (1 ቆሮ·14፡19።)

በዚህም መሠረት አምስቱ አዕማደ ምሥጢር የእምነታችን መግለጫ በሆነው በጸሎተ ሃይማኖት ተዘርዝረው ይተረጐማሉ ።

1· ምሥጢረ ሥላሴ

ይህ ክፍል የሥላሴ አንድነትና ሦስትነት የሚገለጥበት የምሥጢር ዓምድ ነው ። ሥላሴ በስም በግብር ፣ በአካል ሦስት ሲሆኑ በባሕርይ ፣ በመለኮት ፣ በህልውና በፈቃድ አንድ ናቸው ።

የስም ሦስትነት ፡ አብ ፣ ወልድ ፣ መንፈስ ቅዱስ ፣

የግብር ሦስትነት፡ አብ ወላዲ ፣ ወልድ ተወላዲ መንፈስ ቅዱስ ሠራጺ ነው ።

የአካል ሦስትነት ፡ ለአብ ፍጹም አካል አለው ፣ ለወልድ ፍጹም አካል አለው ፣ ለመንፈስ ቅዱስም ፍጹም አካል አለው ።

አብ ልብ ነው ፣ ወልድ ቃል ነው ፣ መንፈስ ቅዱስ እስትንፋስ ነው ። አብ ለራሱ ለባዊ ሆኖ ለወልድና ለመንፈስ ቅዱስ ልባቸው ነው ። ወልድ ለራሱ ቃል ሆኖ ለአብና ለመንፈስ ቅዱስ ቃላቸው ነው ። መንፈስ ቅዱስ ለራሱ እስትንፋስ (ሕይወት) ሆኖ ለአብና ለወልድ እስትንፋስ (ሕይወት) ነው ።

ሥላሴ በስም ፣ በግብር ፣ በአካል ሦስት ናቸው ብንልም በባሕርይ በመለኮት በህልውና በፈቃድ አንድ ስለሆኑ አንድ አምላክ እንጂ ሦስት አማልክት አይባሉም ። አብ ወልድ ፣ መንፈስ ቅዱስ ፣ በየአካላቸው ሲኖሩ ህልውናቸው አንዲት ናት ። (አቡ ሊዲስ ሃይ·አ/ምዕ 40 ክፍ 4 ቁ 6።)

www.zeyeneta.com

የሥላሴ የሦስትነት ስማቸው የአንዱ ወደ አንዱ አይፋለስም ። ይህም ማለት የአብ ስም ተለውጦ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ፣ የወልድ ስም ተለውጦ አብ መንፈስ ቅዱስ ፣ የመንፈስ ቅዱስ ስም ተለውጦ አብ ወልድ ተብሎ አይጠራም ። አብ ፡ አብ ነው ። ወልድ ወልድ ነው ፡ መንፈስ ቅዱስም መንፈስ ቅዱስ ነው ። ሦስቱም በየስማቸውና በየአካላቸው ፣ ጸንተው ይኖራሉ (አግናጢዎስ ሰማዕት ሃይ·አበ) ምዕ·11 ክፍ 1 ቁ 7–8።)

በአንድነት ስማቸው ግን ፡– እግዚአብሔር ፣ አምላክ በመባል ሦስቱም ይጠሩበታል ። እግዚአብሔር አብ ፣ እግዚአብሔር ወልድ ፣ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ አንድ እግዚአብሔር ። አብ ፡ አምላክ ወልድ አምላክ ፣ መንፈስ ቅዱስ አምላክ ፣ አንድ አምላክ ፡ ይባላል ። ይህንም ሦስት መቶ አሥራ ስምንቱ ሊቃውንት በሃይማኖት አበው ሲያስረዱ «በእግዚአብሔር አብ ፣ በእግዚአብሔር ወልድ ፣ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ እናምናለን» ብለዋል (ሃይ አበ ዘሠለስቱ ምእት/ምዕ19 ፡ ክፍል 1 ቁጥር 30።)

የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳሳት ቅዱስ ሐዋርያዊ አትናቴዎስም «አብ አምላክ ነው ፣ ወልድ አምላክ ነው ፣ መንፈስ ቅዱስ አምላክ ነው ፣ ግን አንድ አምላክ እንጂ ሦስት አማልክት አይባሉም» በማለት ገልጾአል (ሐዋርያዊ አትናቴዎስ ሃይ·አበ· ። ምዕ 24 ክፍል 4 ቁጥር 4)

ስለ ሥላሴ አንድነትና ሦስትነት በብሉይና በሐዲስ ኪዳናት በብዙ ቦታ· ተገልጾአል ።

በብሉይ ኪዳን

ዘፍ· 1፡26።2፡18።3፡22።11፡7።18፡1–3። መዝ· 33፡6።146፡5። ኢሳ6፡3፡8።

በሐዲስ ኪዳን

ማቴ· 3፡16–17። 28፡19። ዮሐ·14፡26። 2 ቆሮ· 14፡13። 1 ጴጥ· 1፡2። 1 ዮሐ· 5፡7–8።

2· ምሥጢረ ሥጋዌ

ምሥጢረ ሥጋዌ ከሦስቱ አካላት አንዱ፡– እግዚአብሔር ወልድ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ፣ ከነፍስዋም ነፍስ ነሥቶ በሥጋ የመገለጹ ፣ አምላክ ሰው ፣ ሰው አምላክ ፣ የመሆኑ ምሥጢር ነው ። «ቃል ሥጋ ሆነ በእኛም አደረ» (ዮሐ 1፡14)።

www.zeyeneta.com

እግዚአብሔር ወልድ ሰው የሆነበት ምክንያት

እግዚአብሔር የመጀመሪያዎቹን ሰዎች አዳምንና ሔዋንን በንጹሕ ባሕርይ ያለሞት ፈጥሮአቸዋል ። «እግዚአብሔር ሞትን አልፈጠረምና»። (መጽ· ጥበብ 1፡13)።

ይሁን እንጂ የሰው ልጅ የተሰጠውን ትእዛዝ በማፍረስ ስለበደለ ሞተ ሥጋ ሞተ ነፍስ ፡ ርደተ መቃብርና ርደተ ገሃነም ተፈረደበት(ዘፍ 3፡19–24 እግዚአብሔር ሞትን አልፈጠረምና ነዋሪ ይሆን ዘንድ ፍጥረትን ፈጥሮዋል እንጂ የሰዎች ጥፋት ደስ አያሰኘውም ፡ በእጃችሁ ሥራ ሞትን አታምጡ ። የሰውም መፈጠር ፡ ለደኅንነት ነውና ። በእነርሱ ዘንድ ሁሉን የሚያጠፋ የሞት መርገዝ ፡ኃጢአት አልነበረምና ። ሕይወት የማታልፍ ስለሆነች ለመቃብርም በዚህ ዓለም ግዛት አልነበረውምና እግዚአብሔርን የዘነጉ ሰዎች ግን በቃል ጠሩት ። ባልንጀራም አደረጉት በዚሁም ጠፉ· (ጥበብ 1፡13–17። ሮሜ 6፡23። እግዚአብሔር ለሞት አልሠራንምና ለሕይወት እንጂ» 1 ተሰ· 5፡9)።

አዳምና ሔዋን በበደላቸው ከክብራቸው ተዋረዱ ፡ ከጸጋቸው ተራቆቱ ፡ ከተድላ ገነት ወጡ ፡ ተባረሩ ፡ በሥራቸው በራሳቸው ላይ ብዙ መከራን አመጡ ። ተጨነቁ ፡ ተቸገሩ ፡ ለአጋንንትም ተገገሮች ሆኑ ። በኃጢአት ምክንያት ወደ ዓለም የገባው ሞት በሰው ላይ ሠለጠነ ፡ ከአዳም እስከ ክርስቶስ የነበሩትን ሁሉ ሞት አንድ አድርጎ ገዛቸው ። (ሮሜ 5፡12–14) ይህ ሁሉ መከራ የመጣባቸው ሕገ እግዚአብሔርን በመተላለፋቸው መሆኑን አውቀው ተጸጸቱ ፡ አዘኑ ፡ አለቀሱ ፡ ንስሐ ገቡተው ፡ ፈጣሪያቸውን ለመኑት ። እግዚአብሔርም በፈታሒነቱ አንጻር መሐሪነቱ አለና የአዳምንና የሔዋንን ንስሐቸውን ተቀብሎ ኀዘናቸውንና ለቅሶአቸውን ተመልክቶ ሊያድናቸው ወደደ ፡ ተስፋም ሰጣቸው ፡ (ኢሳ 63፡8 ዕብ· 2፡14–16።)

ይህም የተሰጠው ተስፋ የሚፈጸምበት ዘመን በደረሰ ጊዜ በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘለዓለም ሕይወት እንዲያገኝ ፡ ልዑል እግዚአብሔር ተቀዳሚ ተከታይ የሌለውን አንድ የባሕርይ ልጁን ወደ ዓለም ላከው ፡ እግዚአብሔር ወልድም ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ንጽሕት ከምትሆን ከቅድስት ድንግል ማርያም ሰው ሆኖ ተወለደ ። ሰው ሆነ ማለትም በተለየ

www.zeyeneta.com

አካሉ ነፍስና ሥጋን ተዋሐደ ማለት ነው ። በዚህም የነቢያት ቃል ሁሉ ተፈጸመ (ኢሳ· 7፡14፡ 9፡6፡ ሚክ· 5፡2፡ ገላ· 4፡4)።

መለኮት ከሥጋ ፡ ሥጋ ከመለኮት ጋር ያለ መለወጥ ፡ ያለመቀላቀል ፡ ያለ መለያየትና ያለ መከፈል በተዋሕዶ አንድ አካል አንድ ባሕርይ ሆነ ። ሰው ከመሆኑ አስቀድሞ ፡ ሰውም ከሆነ በኋላ አንድ ወልድ ፡ አንድ ክርስቶስ ነው ። (ቂርሎስ ሃይ· አበ· ምዕ· 78 ክፍ· 48 ቁ 9–18)። ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙም ፦ «በተዋሕዶ ሰው የሆነ አምላክ ፡ አምላክም የሆነ ሰው እርሱ ብቻ ነው» ብሎአል ሃ·አ·ምዕ·61·ክፍል·4·ቁጥር·23· ሥጋም በተዋሕዶተ ቃል እንደከበረ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ «በሥጋ የነበረ ንዴት በተዋሕዶተ ቃል ጠፋ ፡ የቃል ክብር ለሥጋ በተዋሕዶ ገንዘቡ ሆነ» ብሎአል ። (ዮሐ አፈ· ሃይ/አ/ምዕ· 66· ክፍ· 9· ቁጥ· 18–19)። ከተወለደም በኋላ ከኃጢአት በቀር ሰው የሚሠራውን ሥራ ሁሉ እየሠራ አደገ ፡ በዚህም ዓለም· 33· ዓመት ከሦስት ወር ኑሮና አስተምሮ ስለእኛ የሞት ፍርድን ተቀበለ በመስቀል ተሰቅሎ ሞተ ፡ በሞቱም ሞትን አጠፋ ፡ ዓለምን አዳነ ፡ ሦስት መዓልት ሦስት ሌሊት በከርሠ መቃብር አድሮ ተነሣ ። ከተነሣም በኋላ ለደቀ መዛሙርቱ እየታየ ጉባኤ ሠርቶም መጽሐፈ ኪዳንን እያስተማረ በምድር ላይ አርባ ቀን ቆየ ። በአርባኛውም ቀን ደቀ መዛሙርቱ እያዩት በመላእክት ምስጋናና በክብር ወደ ሰማይ ዐረገ ። በአባቱም ቀኝ (ዕሪና) ተቀመጠ ፡ ዳግመኛም በሕያዋንና በሙታን ላይ ሊፈርድና ለሁሉም እንደሥራው ዋጋውን ይከፍል ዘንድ ይመጣል ። (ዮሐ3፡13። 1ጴጥ 3፡22። ማቴ 25፡31። ኤፌ·4፡8–10። የሐዋ·2፡30። 2ቆሮ 5፡14 ።

ስለዚህ በምሥጢረ ሥጋዌ የሚገለጠው ትምህርተ ክርስቶስን ቃለ አብ ወመንፈስ ቅዱስ ፡ ድንግል ማርያምን በአማን ወላዲተ አምላክ ወላዲተ ቃል ፡ ብሎ ማመን ነው ። ቂርሎስ ሃይ/አ) ።

3· ምሥጢረ ጥምቀት፡

ጥምቀት በምሥጢረ ሥላሴና በምሥጢረ ሥጋዌ ለሚያምን ሰው ሁሉ የሚሰጥ የኃጢአት መደምሰሻ ፡ ከእግዚአብሔር የልጅነትን ጸጋ መቀበያ ፡ የመንግሥተ ሰማያትም መውረሻ ነው ። ምሥጢር መባሉም ካህኑ ለጥምቀት የተመደበውን ጸሎት አድርሶ ሲባርከው ውሃው ተለውጦ ማየ ገቦ ስለሚሆንና ከእግዚአብሔር ዘንድ የጸጋ ልጅነትን ስለሚያሰጥ ነው ። (ዮሐ· 19፡34–35)።

www.zeyeneta.com

አምኖ የሚጠመቅ ሁሉ የኃጢአት ሥርየትን ያገኛል ፤ «ወነአምን በአሐቲ ጥምቀት ለሥርየተ ኃጢአት ፡— ኃጢአትን ለማስተሥረይ በአንዲት ጥምቀት እናምናለን» (ጸሎተ ሃይማኖት)

ማንም ሰው በጥምቀት ከእግዚአብሔር ይወለዳል ፤ ከፍዳ ይድናል ። "ያመነ የተጠመቀም ይድናል ፤ ያላመነና ያልተጠመቀ ግን ይፈረድ በታል" (ማር·16፡16 ፤ የሐዋ·2፡28)። ከሥላሴ መወለድም የእግዚአብ ሔርን ርስት መንግሥተ ሰማያትን ለመውረስ ነው ። መንግሥተ ሰማያትም በጥምቀት እንጂ ያለ ጥምቀት ልንገባባት እንደማንችል ጌታችን አስተምሮአል ። «እውነት እውነት እልሀለሁ ማንም ከውሃና ከመንፈስ ቅዱስ ያልተወለደ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት አይችልም» (ዮሐ· 3፡5። ቲቶ 3፡4–7)።

ስለ ጥምቀት በሕግና በነቢያት የተነገሩ ትንቢቶችና የተገለጡ ምሳሌዎች አሉ ።

ሀ) ትንቢት፡— «የጠራ ውሃ እረጫችሁአለሁ ትጠሩማላችሁ» ከርኵሰታችሁም ከጣኦቶቻችሁም ሁሉ አነጻችሁአለሁ ። (ሕዝ· 36፡25። ሚክ· 7፡19) ።

ለ) ምሳሌ፡— 1· ግዝረት

ግዝረት የጥምቀት ምሳሌ ሆኖ በብሉይ ኪዳን ሲሠራበት ኖሮአል ። ግዝረት ለአብርሃም የቃል ኪዳን ምልክት ሆኖ በመሰጠቱ በስምን ተኛው ቀን ያልተገረዘ ሁሉ ከአብርሃም ቤተሰብ አይቈጠርም ምድረ ርስትንም አይወርስም ፤ ከተስፋው አይካፈልም ። የእግዚአብሔርም ወገን አይባልም ነበር ። (ዘፍ· 17፡7)።

በሐዲስ ኪዳን በግዝረት ፈንታ ጥምቀት ተተክቶአል ። ያልተጠመቀ ሁሉ የእግዚአብሔር ልጅ አይባልም ፤ መንግሥተ ሰማያትን አይወ ርስም ። (ቆላስይስ 2፡11)

በብሉይ ኪዳን መፈጸሚያ ፤ በሐዲስ ኪዳን መጀመሪያ የነበረው መጥምቁ ዮሐንስም በውሃ ያጠምቅ ነበር ። (ማር· 1፡4–8)

2· የኖኅ መርከብና የእስራኤል ቀይ ባሕርን መሻገር የጥምቀት ምሳሌዎች ነበሩ ፤ (1ኛ ጴጥ· 3፡19 ፤ 1 ቆሮ· 10፡2)።

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ትንቢቱን ለመፈጸም ፤ ምሳሌውን አማናዊ ለማድረግ በማየ ዮርዳኖስ (ወንዝ) በዮሐንስ እጅ

www.zeyeneta.com

ተጠምቆአል ። (ማቴ 3፡16። ማር 1፡9። ሉቃ 3፡21 ። ዮሐ 1፡31)።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ምሥጢረ ጥምቀትን ለወንዶች በ40 ቀን ፣ ለሴቶች በ80 ቀን ትፈጽማለች ። ይህም ዕድሜ የመጀመሪያዎቹ ሰዎች ከእግዚአብሔር ልጅነትን የተቀበሉበት ነው ። (ኩፋሌ 4፡2–15)።

4· ምሥጢረ /ቁርባን

ቁርባን ወደ እግዚአብሔር የምንቀርብበት ፣ ከእግዚአብሔር ጋር አንድ የምንሆንበት ምሥጢር ነው ። «እውነት እውነት እላችኋለሁ የወልደ እጓለ እመሕያው ክርስቶስን ሥጋውን ካልበላችሁ ደሙን ካልጠጣችሁ የዘለዓለም ሕይወት የላችሁም ። ሥጋዬን የበላ ደሜን የጠጣ የዘለዓለም ሕይወት አለው ። ሥጋዬና ደሜ ሕይወትነት ያለው እውነተኛ ምግብ ነውና ። ሥጋዬን የበላ ደሜን የጠጣ ከእኔ ጋር ይኖራል ። እኔም ከእርሱ ጋር እኖራለሁ» (ዮሐ· 6፡53–57)። ተብሎ ተጽፎአልና ።

ስለ ምሥጢረ ቁርባን አስቀድሞ የተነገሩ ትንቢቶችና የተገለጡ ምሳሌዎች አሉ ።

ትንቢት

«ከስንዴ ፍሬና ከወይን ፣ ከዘይትም ይልቅ በዛ» (መዝ 4፡7)። ጥበብ ቤትዋን ሠራች ፣ ሰባቱንም ምሰሶዎችዋን አቆመች ፣ ፍሪዳዋን አረደች ፣ የወይን ጠጅዋንም ደባለቀች ፣ ማዕዷንም አዘጋጀች (ምሳሌ· 9፡1–9)።

የሰው የሕይወቱ መጀመሪያ እህልና ውሃ ወይንና ስንዴ ነው ። (ሲራ 39፡26)።

እነዚህም ትንቢቶች በመስቀል ላይ የተሠዋው በግዐ ፋሲካ ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋውን ደሙን በስንዴ ኅብስትና በወይን እንደሚሰጥ የተነገሩ ናቸው ።

ምሳሌ

የእስራኤል ልጆች ከግብጽ የባርነት አገዛዝ በወጡበት ጊዜ አርደው ሥጋውን እንዲበሉት ደሙንም የቤታቸውን መቃን ጉበንና መድረኩን ረጭተው ከመቅሠፍትና ከሞተ በኩር እንዲድኑ የተሰጠው የፋሲካቸው

www.zeyeneta.com

በግ በመስቀል ላይ የተሠዋውና ሥጋውንና ደሙን ለሰው ልጆች ሕይወት ቤዛ አድርጎ የሰጠው የወልደ እግዚአብሔር የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ነው ። ይህም «እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ» (ዮሐ· 1፡29) ተብሎ በተጻፈው ታውቋል ።

ለወልደ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ የሆነው ካህን መልከ ጼዴቅም በጎብስትና በወይን ያስታኩት ነበር ። (ዘፍ· 14፡18)።

እነዚህን ትንቢቶችና ምሳሌዎች ለመፈጸምና አማናዊ ለማድረግ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምሴተ ሐሙስ በተዘጋጀው የፋሲካ ዕራት ጎብስቱን እንስቶ አመስግኖ ባርኮ ቆርሶ ለደቀ መዛሙርቱ «ይህ ሥጋዬ ነው ፣ እንኩ ብሉ» ብሎ ሰጣቸው ጽዋውንም አንሥቶ አመስግኖ ባርኮ «እንኩ ሁላችሁ ከዚህ ጠጡ ፣ ለሐዲስ ኪዳን ኃጢአትን ለማስተሠረይ ስለ ብዙ ሰዎች የሚፈስ ደሜ ይህ ነው» ብሎ ሰጣቸው ። (ማቴ 26፡28። ማር· 14፡22። ሉቃ· 22፡19)። ይህ ምሥጢር አሁንም በቤተክርስቲያናችን ይፈጸማል ።

ቁሱ በቅዳሴ ጊዜ ጎብስቱን በግሕል ወይኑን በጽዋዕ አድርጎ እየባረከ ጸሎተ ቅዳሴውን ሲያደርስበት ጎብስቱ ተለውጦ አማናዊ ሥጋ ወልደ እግዚአብሔር ፣ ወይኑ ተለውጦ አማናዊ ደመ ወልደ እግዚአብሔር ይሆናል ።

ይህንም ሊቁ ቅዱስ አትናቴዎስ «ካህኑ፡— ሳይባርከውና ሳያከብረው ጎብስትና ወይን እንደሆነ ካህኑ በባረከውና ባከበረው ጊዜ ግን ጎብስቱ ከጎብስትነት የአምላክ ሥጋ ወደ መሆን ፣ ወይኑም ከወይንነት የወልደ እግዚአብሔር ደም ወደ መሆን እንደሚለወጥ እናምናለን» ብሎአል ። (አትናቴዎስ ሃይ/አበው· ምዕ· 28· ክፍ· 14· ቁ·22 ፤)

ስለዚህ በምሴተ ኀሙስ ሐዋርያት የተቀበሉት በዕለተ ዐርብ በመስቀል ላይ የተሠዋው ፣ ዛሬም በአራቱ መዓዝነ ዓለም እስከ ምጽአት ድረስ የሚሠዋው መሥዋዕት አንድ ነው ። ይኸውም «አማናዊ ሥጋ ወልደ እግዚአብሔር ፣ አማናዊ ደመ ወልደ እግዚአብሔር ነው እንጂ ምሳሌ ወይም መታሰቢያ አይደለም» ብላ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ታምናለች ታሳምናለች ። «ዛሬ በየጊዜው ካህናት የሚያቀርቡአት ንጽሕት መሥዋዕት ያን ጊዜ በቀራንዮ በመልዕልተ መስቀል የተሠዋችው ናት» ። (ዮሐ· አፈ· ቅዳሴ፡85)።

www.zeyeneta.com

5· ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን

ትንሣኤ ሙታን ማለት ከአዳም እስከ ምጽአተ ክርስቶስ ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩና የሚለዩ የሰው ልጆች ሁሉ በነፍስና በሥጋ አዲስ ሕይወት ለብሰው የሚነሡበት ምሥጢር ነው ።

ሰው ሁሉ በሚሞትበት ጊዜ የጻድቅም ሆነ የኃጥእ ሥጋው በመቃብር ይቆያል ። የጻድቃን ነፍስ በገነት ፣ የኀጥአን ነፍስ በሲኦል ትቆያለች ። (ሉቃ 16፡19–31)።

የዚህ ዓለም ፍጻሜ ሲደርስ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሕያዋንና በሙታን ሊፈርድ በሚመጣበት ጊዜ የሰው ልጆች ሁሉ ይነሣሉ ። «ስለዚህ ነገር አታድንቁ በመቃብር ያሉት ሙታን ሁሉ ቃሉን የሚሰሙባት ሰዓት ትመጣለች ሕጉን የፈጸሙ በሕይወት ለመኖር ይነሣሉ ። ክፉ ሥራን የሠሩት ግን በፍዳና በጨለማ ለመኖር ይነሣሉ» ። (ዮሐ· 5፡28)።

ስለ ትንሣኤ ሙታን እምነትና ትምህርት ማረጋገጫ በብሉያት በሐዲሳት በብዙ ቦታ ይገኛል ። በዘዳግም 32፡39 ላይ «እኔ እገድላለሁ ፣ አድንማለሁ» በማለት ራሱ እግዚአብሔር የተናረው ቃል ተስፋ ትንሣኤን የሚያረጋግጥ ነው ። ነቢዩ ኢሳይያስ «ሙታን ይነሣሉ ፣ በመቃብር ያሉ ሕያዋን ይሆናሉ ። በምድር ውስጥ ያሉም ደስ ይላቸዋል ። ከአንተ የሚገኝ ጠል ሕይወታቸው ነውና» ። (ኢሳ 26፡19–20)። ዳንኤልም «በዚያም በመጽሐፉ ተጽፎ የተገኘው ሕዝብህ ሁሉ እያን ዳንዱ ይድናል። በምድርም ትቢያ ውስጥ ካንቀላፉት ብዙዎቹ ይነቃሉ ፣ እኩሌቶቹ ወደ ዘለዓለም ሕይወት ፣ እኩሌቶቹም ወደ ዕፍረትና ወደ ዘለዓለም ጉስቁልና ይሄዳሉ» በማለት ተናግሮአል ። (ዳን· 12፡1–3)።

«እኔን ግን የሚቤገርኝ ሕያው እንደሆነ በመጨረሻም ዘመን በምድር ላይ እንዲቆም ይህ ቁርበቴም ከጠፋ በኋላ በዚያን ጊዜ ከሥጋዬ ተለይቼ እግዚአብሔርን እንዳይ አውቃለሁ ። እኔ ራሴ አየዋለሁ ዓይኖቼም ይመለከቱታል» ሲል ፡ ኢዮብ የትንሣኤን ነገር ገልጦአል ። (ኢዮብ 19፡25–27)።

የትንሣኤ ሙታን ትምህርት በቃል ብቻ የተነገረ አይደለም ከሞቱ ሰዎች መካከል እየተነሡ በተግባር ተገልጦአል ነቢዩ ኤልያስና ደቀ መዝሙሩ ኤልሳዕ ሙታንን አስነሥተዋል ። (1 ነገሥ· 17፡21 ። 2 ነገሥ·

www.zeyeneta.com

13፡21)። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በዚህ ዓለም በሚያስተምርበት ጊዜ ሙታንን አስነሥቶአል ። (ማቴ· 9፡25። ሉቃ· 7፡15። ዮሐ· 11፡14)። እንደዚሁም ሐዋርያት በትምህርት ጊዜያቸው ሙታንን አስነሥተዋል ። ጌታችን በተሰቀለበትም ዕለት ከእግረ መስቀሉ ብዙዎች ሙታን ተነሥ ተዋል ። (ማቴ· 27፡52)።

ይህ ሁሉ የሚያመለክተው የሰው ልጅ በመቃብር ውስጥ ፈርሶና በስብሶ እንደ ማይቀርና በመጨረሻ ቀን እንደሚነሣ ነው። ለትንሣኤያችን መሠረት የምናደርገው ግን የክርስቶስን ትንሣኤ ነው። «ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ እንደተነሣ እኛንም በሐዲስ ትንሣኤ እንደሚ ያስነሣን እናውቃለን» ፣ (2 ቆሮ· 4፡14)። የቤተክርስቲያን ሊቃውንት አምንዮስና አውሳብዮስም «ክርስቶስ የሥጋችንን መነሣት ያስረዳን ዘንድ ተነሣ» ብለዋል (መቅድመ ወንጌል)

ትንሣኤ ለሰው ዘር ሁሉ ነው ፣ ጻድቃንም ኃጥአንም ይነሣሉ ። የመጨረሻው የሙታን ትንሣኤ የሚሆነውም ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዓለምን ለማሳለፍ በሚመጣበት ጊዜ ነው ።

በዘመኑ መጨረሻ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሙታንና በሕያዋን ይፈርድ ዘንድ በክብሩና በጌትነቱ ይመጣል ። (መዝ· 49፡2/ማቴ· 25፡31–32። ራእ 1፡7)። አስቀድሞም መላእክትን ይልካ ቸዋል። እነርሱም የመለከት ድምፅ ያሰማሉ ፣ ሙታንም ይነሣሉ ፣ ምድርም አደራዋን ታስረክባለች ።

ከዚህ በኋላ ጻድቃንን በቀኙ ፣ ኃጥአንን በግራው ያቆማቸዋል ፣ ያን ጊዜ ጻድቃን በበጎ ምግባራቸው ይመሰገናሉ ፣ ኃጥአንም በክፉ ምግባ ራቸው ይወቀሳሉ ። ጻድቃን ከፀሐይ ሰባት እጅ አብርተው ፣ አምላካቸው ክርስቶስን መስለው መንግሥቱን ይወርሳሉ ። ኃጥአን ግን ጠቁረው ፣ ጨለማ ለብሰው ለሰይጣንና ለሠራዊቱ ወደ ተዘጋጀው ወደ ዘለዓለም ኩነኔ ይሄዳሉ። (ማቴ·13፡42–49። ማቴ 25፡31–43። 2 ቆሮ· 5፡10። ራእ· 20፡12)።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ትምህርተ ሃይማ ኖትን ለምእመናን የምታስተምረው ከዚህ በላይ በአምስት ተከፍለው በተገለጡት አዕማደ ምሥጢር መሠረትነት ነው ።

www.zeyeneta.com

ምዕራፍ ፭

ሰባቱ ምሥጢራተ ቤተክርስቲያን

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በሰባት ዐበይት ምሥጢራት ምእመናንን ታገለግላለች ምሥጢራት የተባሉበትም ምክንያት በዓይናችን ልናያቸው በእጃችን ልንዳስሳቸው የማንችል ልዩ ልዩ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች በእነዚሁ ምሥጢራት አማካይነት የሚሰጡን ስለሆነ ነው ።

ሰባቱ ምሥጢራት

1ኛ· ጥምቀት
2ኛ· ቅብዓተ ሜሮን
3ኛ· ቁርባን
4ኛ· ክህነት
5ኛ· ተክሊል
6ኛ· ንስሐ
7ኛ· ቀንዲል ናቸው ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በአዕማድ ምሳሌነት በምሳሌ ሰሎሞን የተነገረውን መነሻ በማድረግ ምሥጢራት ሰባት መሆናቸውን ትቀበላለች ፡ ምሳሌ ሰሎሞን· 9፡1 ፡ እነዚህ ሰባት ምሥጢራት በሚታየውና በሚዳሰሰው በግዙፉ አካል አማካይነት ረቂቁን የማይታየውንና የማይዳሰሰውን የእግዚአብሔርን ጸጋ ለምእመናን የምታሳትፍባቸው ናቸው ። ከእነዚህ ሰባት ምሥጢራት ስድስቱ በጳጳስም ፡ በቄስም ይፈጸማሉ ፡ የክህነትን ሥልጣን መስጠት ግን የሚፈጸመው በጳጳስ ብቻ ነው ።

1· ጥምቀት

ጥምቀት፡ ከሰባቱ ምሥጢራት የመጀመሪያው ጥምቀት ነው፡ ጥምቀት ዳግመኛ ተወልደን ወደ እግዚአብሔር መንግሥት የምንገባበት ምሥጢር ነው ። ዮሐ፡3፡5፡ ጥምቀት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትእዛዝ አለው ። (ማቴ 28፡19–20) ።

በጥምቀት ኃጢአት ይሠረያል የሐዋ·ሥራ 2፡8 ። መንጻትና መቀደስም በጥምቀት ነው ። (1ኛ·ጴጥ· 3፡21፡ ቲቶ 3፡5–6) ።

www.zeyeneta.com

በቤተክርስቲያናችን ሕፃናትን እናጠምቃለን በብሉይ ኪዳን ሕፃናት በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት የሚኖራቸው በተገረዙ ጊዜ ነበር፡ በሐዲስ ኪዳንም ሕፃናት በሕፃንነት ዕድሚያቸው ተጠምቀው የክርስቶስ ቤተሰቦች ስለሚሆኑ በሕፃንነት ይጠመቃሉ እግዚአብሔር ሕፃናትን ከጸጋው ለይቷቸው አያውቅም ፡ ለምሳሌ ኤርምያስ የተቀደሰው በእናቱ ማኅፀን ነበር ። (ኤር 1፡5) ። ዮሐንስ መጥምቁም በእናቱ ማኅፀን ሳለ በመንፈስ ቅዱስ ተመልቶ ነበር ። (ሉቃ· 1፡15) ። ጌታችን መድኃኒታችን በማስተማር ዘመኑ ሕፃናትን ባርኳቸዋል ይህም ሕፃናት ዕድሚያቸው ወደ እግዚአብሔር ከመቅረብ የሚከለክላቸው አለመሆኑን ያሳያል ። (ማቴ 19፡13-15 ፡ ማር 10፡13-15 ፡ ሉቃ· 18፡15-17 ፡ የሐዋ·ሥ 16፡33፡1 ቆሮ 1፡16) ። በቤተክርስቲያናችን ሥርዓት ወንድ ልጅ ሲወለድ በዐርባ ቀን፡ ሴት ልጅ ስትወለድ በሰማንያ ቀን ይጠመቃሉ ። በብሉይ ኪዳን ወንድ ልጅ በተወለደ በዐርባ ቀኑ ወደ እግዚአብሔር ቤት ይገባ ነበር ፡ ሴት ልጅ ስትወለድም በሰማንያ ቀኗ ወደ እግዚአብሔር ቤት ትገባ ነበር ። (ዘሌዋ· 12፡1-5። ሉቃ· 2፡21-24) ። ሕፃናት ሃይማኖታቸውን ለመመስከር ስለማይችሉ ለወንድ ሕፃን የክርስትና አባት ለሴቲቱ ሕፃን የክርስትና እናት ይሰየሙላቸዋል ። ጥምቀት በመዝፈቅ ነው ። ጥምቀት በሥላሴ ስም ነው። (ማቴ· 28፡19-20) ። ከመጠመቃቸው አስቀድሞ ለክርስቶስ ሲሉ በሰማዕትነት ደማቸውን ያፈሰሱ ሰማዕታትም በደማቸው እንደተጠመቁ ይቈጠራሉ ። (ማቴ· 10፡32።16፡25) ።

ሥርዓተ ጥምቀት

– ጥምቀት ውሃ በብዛት ከሚፈስበት ጥምቀተ ባሕር/በወንዝ/ ይፈጸማል ።
– በቤተክርስቲያን ብዛት ያለው ውሃ ካልተገኘ በቤተክርስቲያኑ ቅጥር ግቢ ኩሬ በማበጀት ወይም ሰፊ ገንዳ በመሥራት ሰውነትን በሙሉ ሊያጠልቅ በሚችል ውሃ ይፈጸማል ።
– ተጠማቂውን የሚያጠልቅ ውሃ በማይገኝበት ስፍራ የተገኘውን ውሃ ሦስት ጊዜ በእጅ ታፍነው ወይም በጽዋዕ ቀድተው መላ ሰውነቱን እንዲነካው በማድረግ ያጠምቃል ። (ዲድስቅልያ 34። ፍት· ነገሥ · አንቀጽ·3) ።
– ካህኑ የጥምቀቱን ጸሎት ከፈጸመ በኋላ ተጠማቂውን ይዞ «አሰግደከ/ኪ/፡

www.zeyeneta.com

ለአብ ፡ አሰግዶክ/ኪ ለወልድ ፡ አሰግዶክ/ኪ ለመንፈስ ቅዱስ» እያለ በወራቱ መዓዝን ያሰግዱዋል ። ሲያጠምቅም «አጠምቀክ ኪ በአብ ፡ አጠምቀክ ኪ በወልድ አጠምቀክ/ኪ በመንፈስ ቅዱስ» እያለ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም ያጠምቃል ። (ማቴ· 28፡19 20) ።

– ተጠማቂው ወደ ጥምቀት ሲቀርብ ጠንሩን ይላጫል ልብሱን ያወልቃል።

– ተጠማቂው ከተጠመቀ በኋላ ወዲያውኑ ተቀድሶ ሥጋውንና ደሙን ይቀበላል ። ይህም የሚሆንበት ምክንያት ቅዱስ ቁርባን የምሥጢራት ሁሉ መደመደሚያ ስለሆነ ነው ።

– ተጠማቂዎቹ አዋቂዎች ከሆኑ የተወሰነ የትምህርት ጊዜ ተሰጥቶ መሠረተ እምነት እንዲማሩና ዐውቀው አምነው እንዲጠመቁ ይደረጋል ።

– ወንዶች ወንዶችን፡ ሴቶችም ሴቶችን ብቻ ክርስትና ያነግሳሉ ። (ፍት· ነገ· አን·3 ዲድስቅ· 34 ። ዘኂቅ 24) ።

– ማንኛውም ሰው ለመጠመቅ ከተወሰነው ጊዜ በፊት ለሞት የሚያሰጋ ሕመም ቢደርስበት ሥርዐተ ጥምቀት ይፈጸምለታል ። (ፍት· ነገ· አን·3) ።

– ተጠማቂዎቹ ተምረው ዐውቀው የሚጸልዩ ከሆነ ራሳቸው ፡ የማይችሉ ከሆነ የክርስትና አባቶች ወይም እናቶች ጸሎተ ሃይማኖትን እንዲጸልዩ ላቸው ይደረጋል። ትምህርተ ሃይማኖትንም እያስተማሩ ለማሳደግ ቃል ይገባሉ ።

– ከክርስቲያን ቤተሰብ የሚወለዱ ሕፃናት ወንዶች በ40 ቀን ሴቶች በ80 ቀን ይጠመቃሉ ።

ነገር ግን ማንኛውም ሰው በክርስቶስ አዳኝነት ከአመነ በማንኛውም ዕድሜ ከመጠመቅ አይከለከልም ።

– ጥምቀት በሥላሴ ስም ነው ። (ማቴ· 28፡19)

– ጥምቀት አይደገምም (ሮሜ· 6፡3 ፡ 4 ። ኤፌ· 4፡4–7) ።

– ጥምቀት በውሃ ብቻ ነው ። (ዮሐ· 3፡5 ። ፍ· ነገሥ· 3) ።

– ተጠማቂው ከተጠመቀ በኋላ ማተብ በእንገቱ ይታሰርለታል ይህም የክርስቲያን ምልክትና መለያ ነው ። ጥምቀት የክርስቶስ ሞት ምሳሌ ነው ፡ የክርስቶስ መቶ መቀበር ተጠማቂው ወደ ማጥመቂያው

www.zeyeneta.com

ለመግባቱ ምሳሌ ሲሆን ክርስቶስ በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተለይቶ መነሣቱ ደግሞ ተጠማቂው ትንሣኤ ዘለክብርን የሚነግ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው ። (ዲያስቅ· 34· ሮሜ· 6·3 6) ። ከዚህም ጋር ጥምቀት በመጽሐፈ ክርስትናና በፍትሐ ነገሥት በተወሰነው መሠረት ይፈጸማል ።

2· ሜሮን

ሜሮን፡ ተጠማቂው ከማጥመቂያው ሲወጣ የሚቀባው ቅዱስ ዘይት ነው ፡ ሜሮን እንደ ጥምቀት ነው ፡ አይደገምም። በቅብዐተ ሜሮን ተጠማቂው የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ ይቀበላል ። በሐዋርያት ጊዜ አማኞች ከተጠመቁ በኋላ በእንብሮተ እድ መንፈስ ቅዱስን ያሳድሩባቸው ነበር ። (የሐዋ· ሥራ 20፡14 17) ። በቤተክርስቲያን እየተስፋፋች በሔደች ጊዜ ግን በአንብሮ እድ ፋንታ በሐዋርያተ መንበር የተተኩ ኤጲስ ቆጶሳት በቅዱስ ሲኖዶስ ሜሮን እያዘጋጁ አዲስ የተጠመቀ ሁሉ እንዲታተምበት ፈቀዱ ።

በሜሮን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ— መጽሐፍ ቅዱሳዊ መመሪያ አለው ።

ሜሮን የሚቀባው ተጠማቂው ወዲያው ከማጥመቂያው ሲወጣ ነው። ሐዋርያት ሲያጠምቁ ሕዝቡንም ሆነ ሽማግሌውን ወዲያው በእንብሮተ እድ መንፈስ ቅዱስን ያሳድሩበት ነበር ። (የሐዋ· ሥራ 8፡14–17 ፡ 19፡5–6) ። ሕፃናት ከተጠመቁ በኋላ መንፈስ ቅዱስን እንዲቀበሉ ወዲያውኑ በሜሮን ይቀባሉ ። እንኳን ተወልደው በእናታቸው ማኅፀን ሳሉ በመንፈስ ቅዱስ የከበሩ ሕፃናት እንዳሉ መጽሐፍ ቅዱስ ይመሰክራል ። (ሉቃ· 1፡15 ኤር· 1፡1–8) ። ሜሮን የመቅባት ሥልጣን ያለው በሐዋርያት መንበር የተቀመጠው ኤጲስ ቆጶስ ነው ። ቄሶችም እንዲቀቡ ተፈቅዷል ።

3· ምሥጢረ ቁርባን

በቤተክርስቲያናችን የምሥጢራት ሁሉ መደምደሚያ ቅዱስ ቁርባን ነው ። ቁርባን ማለት መሥዋዕት ማለት ነው ። ይኸውም ሰው

www.zeyeneta.com

ለእግዚአብሔር ያቀረበው ሳይሆን እግዚአብሔር ስለሰው ያቀረበው ነው። በብሉይ ኪዳን በምሳሌ የተሠዋው በግና ፍየል ሁሉ በአዲስ ኪዳን በቤተክርስቲያን ለሚሠዋው የክርስቶስ ሥጋና ደም ምሳሌ ነበር ። መልከ ጼዴቅ ለአብርሃም ያበረከተው ኅብስተ አኰቴት ጽዋዐ በረከት ። (ዘፍ· 14፡ 18) ። እሥራኤል የነጻነታቸው ዕለት የሠዉት መሥዋዕት የፋሲካችን በግ የክርስቶስ ሥጋ ምሳሌ ነበር ። ቁርባን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት አለው ። (ማቴ· 26፡26 ። ቀዳ· ቆሮ· 11፡23–25) ። ቄሱ ኅብስቱን በጸሐል ወይኑን በጽዋዕ አድርጎ ጸለየ ቅዳሴውን ሲያደርስ ኅብስቱ ተለውጦ ሥጋ መለኮት ፣ ወይኑ ተለውጦ ደመ መለኮት ይሆናል ። በቤተ ክርስቲያናችን ለምእመናን የምናቀብለው ከሥጋውም ከደሙም ነው ። (ዮሐ· 6፡54–58 ። ማቴ· 26፡27) ።

– ቄሱ ሥጋውን ሲያቀብል ዲያቆኑ ደሙን በዕርፊ መስቀል ያቀብላል ።
– ወደ ቤተክርስቲያን መምጣት ለማይችሉ በሽተኞች በዕለቱ ተቀድሶ በቤታቸው እንዲቈርቡ ይደረጋል ።
– መሥዋዕት ከዕለቱ አያልፍም ፣ አይውልም ፣ አያድርም ። ቁርባን የሚቈረበው ሳይበላ ሳይጠጣ ቢያንስ ለ15 ሰዓት በመጾም ነው ።
– በቤተ ክርስቲያናችን ቅዱስ ቁርባን ፍጹም የክርስቶስ ሥጋና ደም ነው። (ዮሐ· 6፡51–55) ።

እንደ ሌሎቹ ምሥጢራት ሁሉ ምሥጢረ ቁርባንን የሚፈጽሙ በሐዋርያት መንበር የተቀመጡ ጳጳሳት ነበሩ ። ቤተክርስቲያን እየተስፋፉች ስትሔድ ግን ለቀሳውስት ፈቀዱላቸው ፣ ዲያቆናት የጳጳሱና የቄሱ ረዳቶች ናቸው ። ራሳቸውን በንስሓ የመረመሩና ያጸዱ ምእመናን ሥጋውን ደሙን መቀበል ይችላሉ ራሳቸውን በንስሓ ያላዘጋጁ ግን ቢቀበሉም ዕዳ ይሆንባቸዋል ። (ቀዳ· ቆሮ· 11፡28–29) ዮሐ· አፈ/ወርቅ ቅዳሴ)።

4· ክህነት

ክህነት፡– የቤተክርስቲያን ከፍተኛው መንፈሳዊ መዐርግ ነው ። ክህነት መጽሐፍ ቅዳሳዊ መሠረት አለው ። (ማቴ· 28፡19 ፣ 20 ። ኤፌ 4፡11 ። የሐዋ· ሥራ 28፡20) ።

www.zeyeneta.com

በቤተክርስቲያናችን የክህነት መዐርጋት ሦስት ናቸው ፡ እነሱም ዲቁና ፡ ቅስናና ጵጵስና ናቸው ።

1ኛ· ዲያቆን ፡ ሀ) ከማግባቱ በፊት ዲቁና ይሾማል ።

ለ) አግብቶ ወይም መንኩሶ የቅስና መዐርግ ይቀበላል ።

ሐ) አገልግሎቱም የቂስና የጳጳስ ረዳትነት ነው ።

መ) የሚሾመው በጳጳስ ነው ።

ሠ) በቤተ ክርስቲያናችን ከሙሉ የዲቁና መዐርግ በፊት ለተልእኮ የሚያበቁ 3 መዓርጋት የሚሰጡ በአንብሮተ እድ ሳይሆን በቃለ ቡራኬ ብቻ ነው ።

ረ) ዲያቆናት በአንብሮተ እድ ብቻ ይሾማሉ ።

ሰ) ሥልጣነ ክህነት ለመቀበል ዋጋ አይሰጥም ። (የሐዋ· ሥራ 8፡18 -26) ።

ሸ) ክህነት በዘር ሐረግ ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ ጥሪና በቤተክርስቲያን ቀኖና ነው ።

2ኛ· ቄስ ፡ ዲያቆኑ ካገባ ወይም ከመነኮሰ በኋላ የቅስና ሥልጣን ይቀበላል። አገልግሎቱም ሥልጣነ ክህነት ከመስጠት ሜሮን ከማዘጋጀት አዲስ ቤተክርስቲያንና አዲስ መንበር አዲስ ጽላትና ሌሎችንም አዳዲስ ንዋየ ቅድሳት ከመባረክ በቀር ሌላውን ሁሉ ይፈጽማል ።

በድንግልና የቀሰሰ ከሆነ ወደ ጵጵስና መዐርግ መድረስ ይቻላል ፡ ባለ ሕግ ከሆነ ግን በዚህኛው መዐርግ ብቻ ይወሰናል ። ይህም በአንብሮተ እድና በንፍሐት በጳጳስ ይሾማል ።

3ኛ· ጳጳስ (ኤጲስ ቆጶስ) ኤጲስ ቆጶስነት የሚሾመው በድንግልና የመነኮሰ ካህን ነው ። የሚሾመው በመላ የሲኖዶስ አባላት ነው ። በችግር ጊዜ ግን ከሁለት ባላነሱ ኤጲስ ቆጶሳት በአንብሮተ እድና በንፍሐት ይሾማል ። አገልግሎቱም ምሥጢራትን ከመፈጸም ጋር ጠቅላላ የቤተክርስቲያን መሪና ጠባቂ ነው ። እነዚህን መዐርጋት የሚቀበሉ ሁሉ የሚያሟሏቸው ግዴታዎች አሏቸው ።

ሀ) ጤንነት ያላቸው

ለ) ሃይማኖታቸውን ለማስፋፋት በቂ ትምህርት ያላቸው

ሐ) በጠባይ የተመሰገኑ መሆን አለባቸው

www.zeyeneta.com

መ) ወደ መዐርገ ክህነት የሚቀርቡ ሁሉ በቤተክርስቲያናችን ሥርዓት ወንዶች ብቻ ናቸው ።

ሠ) ክህነት አይደገምም ወይም አይታደስም በድጋሚ ክህነት የሚቀበል ወይም የሚሰጥ ሁለቱም ከክህነታቸው ይሻራሉ ። (የሐዋርያት ቀኖና 68) ። ክርስቶስ ለቤተክርስቲያኑ የተወሰኑ ሰዎችን ለክህነት መርጦአል ። (ሉቃስ 6፡12፡13 ። ዮሐ· 20፡19–25) ። ለሌላ ያልተሰጠ ልዩ ሥልጣንም ሰጥቷቸዋል ። (ማቴ· 18፡18) ። በዕርገት ሲሰናበታቸው እስከ ዓለም ፍፃሜ እንደማይለያቸው ቃል ገብቶላቸዋል ። (ማቴ· 28፡20) ። ሲያርግም ጠቅላላ መዐርገ ክህንነትን ሾሟቸው ዐረገ ። (ሉቃ· 24፡51) ።

ከሐዋርያት አላልነት በወጣው በይሁዳ ምትክ ለመምረጥ በሲኖዶስ ተሰብስበው ለቤተክርስቲያን አገልግሎት ማትያስን መምረጣቸው የሐዋርያት አገልግሎት ከሌላው ሕዝባዊ አገልግሎት የተለየ መሆኑን ያሳያል ። (የሐዋ· ሥራ 1፡15–26) ።

5· ተክሊል

የክርስቲያኖች ጋብቻ በቤተክርስቲያን ምስክርነት የሚፈጸም ጸጋ መንፈስ ቅዱስንም የሚያሰጥ ስለሆነ ከሰባቱ ምሥጢራት አንዱ ነው ጋብቻ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት አለው ። (ዘፍ· 1፡27 28 ። 2፡18 ማቴ· 19፡4 6) ።

በቤተክርስቲያናችን ቀኖና መሠረት ክርስቲያናዊ ጋብቻ ከመፈጸሙ በፊት የሚከተሉት ግዴታዎች መሟላት አለባቸው ።

ጸጋ መንፈስ ቅዱስን በእኩልነት የሚቀበሉ ስለሆኑ ሁሉም ክርስቲያን መሆን አለባቸው ።

ሁለቱም የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን አባላት መሆን አለባቸው።

ሁለቱ አንድ ካልሆኑ ግን ጋብቻው ከመፈጸሙ በፊት የቤተክርስቲያናችን አባል መሆን ግዴታ ነው ።

ከጋብቻ በፊት ሥጋዊ ግንኙነት አይፈቀድም ።

ለጋብቻው ሁለቱም ፈቃደኞች መሆን አለባቸው ።

በቤተሰብ መካከል የሥጋዊም ሆነ የመንፈሳዊ ተዘምዶ ገደብ በጋብቻ

www.zeyeneta.com

እንዳይፈርስ እስከ ሰባት ትውልድ ድረስ መከበር አለበት (ዘሌዋ· 18፡6–21 ። ዘዳግም 7፡3–4) ።

– በሞት ፣ በዝሙት ካልሆነ በቀር ከሁለቱ አንዱ ተለይቶ ለማግባት አይችልም ። (ማቴ· 19፡6 ፣ 9 ።)

– የክርስቲያኖች ጋብቻ የክርስቶስና የቤተክርስቲያን አንድነት ምሣሌ ስለሆነ አይፈርስም ። (ኤፌሶን 5፡32) ።

– የተክሊልን ምሥጢር የሚፈጽሙ ጳጳሳትና ቀሳውስት ናቸው ።

– ተክሊል ያለሥጋ ወደሙ አይፈጸምም ። (ፍት· መን· 24 ቁ·899) ።

– በጋብቻ ጊዜ የወላጆች ፈቃድ መጨመር አለበት ።

6· ንስሓ

ንስሓ፡– መጸጸት ፣ መመለስ ፣ ከኃጢአት መንጻት ማለት ነው ። ክርስቲያኖች በጥምቀት እንደገና የተወለዱ ቢሆኑም ሰው ሆኖ ወደ ኃጢአት ማዘንበል የማይቀር ነውና ፣ እያንዳንዱ ክርስቲያን መምህረ ንስሓ ሊኖረው ይገባል ።

– ክርስቲያኖች ወደ መምህረ ንስሓ እየሄዱ ኃጢአታቸውን ይናዘዛሉ ። (ዘሌ· 14፡31 ማቴ· 8፡4 ኤጲፋንዮስ ሃይ አበ ምዕ59 ቁ· 20) ። ወደ እግዚአብሔር ለመመለስ ያደረጉት ሙከራና ኃጢአታቸውንም መናዘዛቸው ጸጋ እግዚአብሔርን ያሰጣቸዋል ። ሥጋውን ደሙን ተቀብለው ወደ ቀደመ ክብራቸው ይገባሉ ።

– ኑዛዜ መቀበልና ማስተሥረይ የሚገባቸው ጳጳሳትና ቀሳውስት ብቻ ናቸው ።

ንስሓ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት አለው ። (ማቴ· 8፡4፡16 ፣ 19) ። ንስሓ ተነሳሒው በመምህረ ንስሓው ፊት ቀርቦ ኃጢአቱን በመናዘዝ የሚያፈሰው እንባ የኃጢአቱን ክብደት እያስታወሰ የሚያሳየው ጭንቀት በመንፈስ ቅዱስ እንደገና እንዲታደስ ያደርገዋል ። (አትና ቴዎስ ቅዳሴ)

– ንስሓ ከሚደጋገሙ ምሥጢራት ጋር የሚቆጠር ነው ። ከነቢያት ጀምሮ የመጥምቁ ዮሐንስ ፣ የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስና የተከታዮቹ የሐዋርያት የትምህርት ዋና ዓላማ ሰው ሁሉ በንስሓ እንዲመለስና ወደ እግዚአብሔር መንግሥት እንዲገባ “መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና

www.zeyeneta.com

ንስሓ ግቡ” የሚል ነበር ። ዛሬም ቤተክርስቲያን ስለ ንስሓ የምታስተምረው ይህንኑ መሠረት አድርጋ ነው ። (ዘካ· 1፡3 ። ማቴ· 3፡1–2 ። 4፡17) ።

7· ቀንዲል

ቀንዲል፡– ቤተክርስቲያናችን ከምትገለገልባቸው ሰባት ምሥጢራት አንዱ ነው ። ይህ ምሥጢረ ቀንዲል ለበሽተኞች የሚቀባ ነው ። ቀንዲል መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት አለው ። (ማር· 6፡13 ያዕቆብ 5፡13–15) ።

በቤተክርስቲያናችን የቀንዲል መጽኃኒትነት ለሥጋ ብቻ ሳይሆን ለነፍስም ስለሆነ በኃጢአት ደዌ ለተያዘ ቀንዲል ይደረግለታል ። የቀንዲል ምሥጢር የሚፈጸመው በጳጳሳትና በቀሳውስት ነው ።

ሰባቱ ምሥጢራተ ቤተክርስቲያን ለእያንዳንዳቸው የሚፈጸም የእየራሳቸው የሆነ መጽሐፈ ጸሎትና የአፈጻጸም ሥርዐት አላቸው ሁሉም ምሥጢረ ቤተክርስቲያን የቤተክርስቲያኒቱ ሥርዐተ አምልኮ ማስፈጸሚያና የሃይማኖት መመሪያ ነው ።

እነዚህ ምሥጢራት ሁሉም በቤተክርስቲያን ይፈጸማሉ ፡ ሆኖም እንደእየሁኔታው በሌላም ቦታ ይፈጸማሉ ፡ ውግዘት የለበትም ። የሁሉም ምሥጢራት ዋና ዓላማ ሰውን ለማዳን ነው ።

ምዕራፍ ፫

ቅዱሳት መጻሕፍት ፡

ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ በመንፈስ እግዚአብሔር የተጻፉ ወይም እስተንፍሰ እግዚአብሔር ናቸው ። በሌላም አገላለጽ መጻሕፍት አምላካዊ ውደት ይባላሉ ። (ፍት·ነገ· አን· 2) ። ቅዱሳት መጻሕፍት እስትንፍሰ እግዚአብሔር ለመሆናቸው ወይም በመንፈስ እግዚአብሔር ለመጻፋቸው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በ2ኛ ጢሞ· 3·17 «የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል» ብሎ ጽፎአል ። ቅዱስ ቂርሎስ ዘእስክንድርያም «ቅዱሳት መጻሕፍት እስትንፍሰ እግዚአብሔር ናቸው» ብሎአል ። (ቂር·ሃይ/አበ 78፡67) ።

www.zeyeneta.com

በመሆኑም በቅዱሳት መጻሕፍት የተጻፈው ሁሉ ፍጹም እውነት ነው ፡ ሊለወጥ ሊሻሻል ፡ ሊጨመርበት ወይም ሊቀነስለት የማይቻል ነው። በመንፈስ እግዚአብሔር የተቃኙ ቅዱሳን ሰዎች ጽፈውታልና (2ጴጥ. 1፡20 ። ማቴ. 5፡18 ። ሉቃ. 16፡17) ።

ልዑል እግዚአብሔር ቅዱሳት መጻሕፍትን «እንዲህ ብለህ ተናገር ፡ እንዲህ ብለህ ጻፍ» እያለ ድምፁን በማሰማት ፡ በራእይ እየተገለጸ ፡ በልቡና እየቀረፀ እንዲጻፉ ማድረጉ ተገልጦአል ። (ዘጸአ. 34፡27 ። ዘዳግ. 31፡19 ። ኢሳ. 8፡1) ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በቀኖና የተቀበለቻቸው የብሉያትና የሐዲሳት መጻሕፍት ቁጥር 81 ነው ።

ሀ) የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት፡-

1. ኦሪት ዘፍጥረት
2. ኦሪት ዘጸአት
3. ኦሪት ዘሌዋውያን
4. ኦሪት ዘኍልቁ
5. ኦሪት ዘዳግም
6. መጽሐፈ ኢያሱ
7. መጽሐፈ መሳፍንት
8. መጽሐፈ ሩት
9. 1ኛና 2ኛ ሳሙኤል
10. 1ኛና 2ኛ መጽሐፈ ነገሥት
11. 1ኛ መጽሐፈ ዜና መዋዕል
12. 2ኛ መጽሐፈ ዜና መዋዕል
13. መጽሐፈ ኩፋሌ
14. መጽሐፈ ሄኖክ
15. መጽሐፈ ዕዝራና ነህምያ
16. ዕዝራ ካልእና ዕዝራ ሱቱኤል

www.zeyeneta.com

17· መጽሐፈ ጦቢያ
18· መጽሐፈ ዮዲት
19· መጽሐፈ አስቴር
20· መጽሐፈ መቃብያን ቀዳማዊ
21· 2ኛና 3ኛ መጽሐፈ መቃብያን
22· መጽሐፈ ኢዮብ
23· መዝሙረ ዳዊት
24· መጽሐፈ ምሳሌ
25· መጽሐፈ ተግሣጽ
26· መጽሐፈ ጥበብ
27· መጽሐፈ መክብብ
28· መጽሐፈ መኃልየ መኃልይ
29· መጽሐፈ ሲራክ
30· ትንቢተ ኢሳይያስ
31· ትንቢተ ኤርምያስ
32· ትንቢተ ሕዝቅኤል
33· ትንቢተ ዳንኤል
34· ትንቢተ ሆሴዕ
35· ትንቢተ አሞጽ
36· ትንቢተ ሚክያስ
37· ትንቢተ ኢዩኤል
38· ትንቢተ ዐብድዩ
39· ትንቢተ ዮናስ
40· ትንቢተ ናሆም
41· ትንቢተ ዕንባቆም
42· ትንቢተ ሶፎንያስ
43· ትንቢተ ሐጌ
44· ትንቢተ ዘካርያስ
45· ትንቢተ ሚልክያስ
46· መጽሐፈ ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን
ድምር 46

www.zeyeneta.com

የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት

1· የማቴዎስ ወንጌል
2· የማርቆስ ”
3· የሉቃስ ”
4· የዮሐንስ ወንጌል
5· የሐዋርያት ሥራ
6· ወደ ሮሜ ሰዎች
7· ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 1ኛ
8· ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 2ኛ
9· ወደ ገላትያ ሰዎች
10· ወደ ኤፌሶን ሰዎች
11· ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች
12· ወደ ቆላስይስ ሰዎች
13· ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 1ኛ
14· ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 2ኛ
15· ወደ ጢሞቴዎስ 1ኛ
16· ወደ ጢሞቴዎስ 2ኛ
17· ወደ ቲቶ
18· ወደ ፊልሞና
19· ወደ ዕብራውያን
20· የጴጥሮስ መልእክት 1ኛ
21· የጴጥሮስ መልእክት 2ኛ
22· የዮሐንስ መልእክት 1ኛ
23· የዮሐንስ መልእክት 2ኛ
24· የዮሐንስ መልእክት 3ኛ
25· የያዕቆብ መልእክት
26· የይሁዳ መልእክት
27· ራእይ

www.zeyeneta.com

የሥርዓት መጻሕፍት

1· ሥርዓተ ጽዮን
2· ትእዛዝ
3· ግጽው
4· አብጥሊስ
5· 1ኛ መጽሐፈ ኪዳን
6· 2ኛ መጽሐፈ ኪዳን
7· ቀሌምንጦስ
8· ዲድስቅልያ

ድምር 35

የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ድምር 46
የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ድምር 35
ጠቅላላ ድምር 81

ስለቅዱሳት መጻሕፍት የተለያየ አቈጣጠር ቢኖርም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የምትቀበላቸውና በፍትሐ ነገሥት ትርጓሜ ተዘርዝረው የሚገኙ መጻሕፍት ከዚህ በላይ የተመለከቱት 81 መጻሕፍት ናቸው ።

ከነዚህም ጋር የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በብሉይና በሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ላይ የተመሠረቱ የብሉያትና የሐዲሳትን ምሥጢራት አብራርተውና አጉልተው የሚገልጡ በልዩ ልዩ ቅዱሳን አበው የተደረሱ የሃይማኖት ፣ የትምህርት የጸሎት መጻሕፍት ከብሉያትና ሐዲሳት ተውጣጥተው የተደረሱ የቅ/ያሬድ የፀዋትወ ዜማ መጻሕፍት ሌሎችም የአገልግሎት መጻሕፍት አሉአት ።

ቅዱስ ያሬድ

ቅዱስ ያሬድ በኢትዮጵያ ዘመን አቈጣጠር በ505 ዓ·ም· የተነሣ ኢትዮጵያዊ ሊቅ ነው ። ቅ/ያሬድ በዓለም በሚታወቅበት ሙያውና ዕውቀቱ በመንፈስ ቅዱስ የተቃኘ የመንፈሳዊ ዜማ ደራሲ ፣ የቅኔ ተመራማሪ ኪሩቤልን በሚያስመስለው ጣዕመ ዝማሬ የተወደደና ድምፀ መልካም ማሕሌታዊ ነው።

www.zeyeneta.com

ቅዱስ ያሬድ ድጓ ፣ ዝማሬ ፣ መዋሥዕትና ምዕራፍ የተሰኙ የዜማ መጻሕፍት አሉት ። የብሉያት ፣ የሐዲሳትና የሊቃውንት መጻሕፍት ትርጓሜም ሊቅ ነው ። ከነዚህ ከብሉያት ከሐዲሳትና ከሊቃውንት መጻሕፍት ለጸሎትና ለማሕሌት የሚስማሙትን ቃላት እየመረጠ ፣ ምሥጢራትን ከትርጓሜ እያስማማ ዜማዎቹን በዐራቱ ክፍላተ ዘመን በመፀው ፣ በሐጋይ ፣ በጸደይና በክረምት በመክፈል የየወቅቱን የተፈጥሮ ሥነ ባሕርይ በአንክሮና በምስጋና በሚገለጽ ጣዕም እንዲዘመሩና እንዲጸለዩ ያደረገ ታላቅ ኢትዮጵያዊ ደራሲ ነው ። ዜማውንም ግእዝ ፣ ዐዝልና አራራይ በሚል በ3 የዜማ ስልት ከፍሎ ዘምሮታል ።

ሊቁ ቅ/ያሬድ የዜማ ድርሰቱን ያዘጋጀው ከ540–560 ዓ·ም· ባለው ዘመን ነው ። ማሕሌታዊው ቅ/ያሬድ በኢትዮጵያ ሰሜናዊ ክፍሎች ለ11 ዓመታት እየተዘዋወረ ሲያስተምር ፣ ቤተክርስቲያንን ሲያገለግልና ሲያስገለግል ቈይቷል ።

በመጨረሻም በሰሜን ተራራዎች ሥር ካሉት ገዳማት በአንዱ ዋሻ ውስጥ ገብቶ በጾም በጸሎት ፣ በብሕትውና ዘመኑን አሳልፎአል ። ሊቁ ቅ/ያሬድ እስከዛሬ ጎልፈትና ውላጤ ያላገኘው ፣ በጣዕመ ዝማሬውና በምልክቱ ልዩ የሆነ የዜማ ድርሰቱን ለኢትዮጵያ ያበረከተ ታላቅ ኢትዮጵያዊ ሊቅ በመሆኑ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ዝክረ ስሙን በጥንቃቄ ጠብቃ ፣ በስሙ ጽላት ቀርፃ ፣ ቤተክርስቲያንን አንፃ ፣ ገድሉን ጽፋ ታከብረዋለች ።

ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት ከቅዱስ ያሬድና ከሌሎችም መጻሕፍት ሌላ በቀደምት የጋራ አባቶች የተደረሱና ተተርጉመው ወደ ኢትዮጵያ የገቡ ይገኙባቸዋል ። የእመቤታችን የቅ/ድንግል ማርያምን ተአምር ፣ ንጽሕናዋንና ቅድስናዋን የሚያረጋግጡ ፣ የቅዱሳን መላእክትን ፣ ተልእኮ የቅዱሳን ጻድቃንና የሰማዕታትን የነቢያትንና የሐዋርያትን ተአምርና ገድል የሚገልጡ የተሰጣቸውን ቃል ኪዳን ጸጋና ክብር የሚናገሩ ገድላትና ድርሳናት የተአምራት መጻሕፍት አሉአት ።

www.zeyeneta.com

ምዕራፍ ፮

ትውፊት

ትውፊት ማለት ከጥንት ጀምሮ በቤተክርስቲያን በኩል ቃል በቃል ሲነገር የመጣ በቃልም በጽሑፍም ከአበው ወደ ትውልድ ሲተላለፍ የኖረና የሚኖር ማለት ነው ።

የሰው ልጅ እምነቱንና ሥርዓቱን ባህሉንና ታሪኩን በጽሑፍ ከመያዙ አስቀድሞ ከአዳም እስከ ሙሴ ቃል በቃል እየተነገረ በተላለፈ ትውፊት መቄየቱ ይታወቃል ። ይህም የትውፊት አመጣጥ መሠረት ነው።

ትውፊት በቅዱሳት መጻሕፍት ያልተጻፉትን ከአበው ቃል በቃል የተላለፉትን የእምነት የሥርዓት ፣ የትምህርትና የታሪክ ውርሶች እያጐላ ያቀርባል ። መሠረታቸው ቅዱሳት መጻሕፍት ሆነው በትርጉም ያልተገለጡትን በተግባር ያሳያል ። ትውፊት ከቅዱሳት መጻሕፍት ምሥጢርና ትርጉም ጋር የሚቃረን አይደለም ።

ትውፊት ትምህርተ ሃይማኖትን ሥርዓተ ቤተክርስቲያንን ባህልንና ታሪክን ብቻ ሳይሆን ከጥንት ጀምሮ ሳይፋለስና ሳይለወጥ የተላለፈውን የሥርዓተ አምልኮት አፈጻጸምን ሁሉ ያካትታል ።

የቤተክርስቲያን እምነትና ትምህርት በጽሑፍ ሳይሆን ይሰጥ የነበረው በቃል ነው ። የተጻፈም በቃል ሲነገር የነበረው ነው ። ‘‘ማመን ከመስማት ነው ፣ መስማትም በእግዚአብሔር ቃል ነው’’ ተብሎ ተጽፎአልና (ሮሜ 10፡17)።

ከነቢያት እየጻፉ ያስተማሩ መኖራቸው ቢታወቅም ብዙዎቹ በቃል አስተምረዋል ። ሐዋርያትም ጌታችን ወደ ዓለም በላካቸው ጊዜ በቃል አስተምረዋል ። (ማቴ· 28፡19። ማር· 16፡15)

ቅዱሳን ሐዋርያት ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርትና ተአምራት ጥቂቱን ብቻ መጻፋቸውን በግልጥ ተናግረዋል ። (ዮሐ· 20፡30። ዮሐ· 21፡25) ። ራሳቸውም ያስተማሩትን ትምህርትና ያደረጉትን ተአምር በሙሉ አልጻፉም ። (2ዮሐ· ቁ· 12፡3 ዮሐ· ቁ· 13–14)።

ስለ ትውፊት ቅዱሳት መጻሕፍት በብዙ ቦታ ይመሰክራሉ ። (1 ቆሮ· 11፡2 ፣ 23 ። 15፡1–3። 1ተሰ· 2፡13። 2ተሰ· 2፡15)። ስለዚህ ቅዱስ

www.zeyeneta.com

መጽሐፍና ትውፊት ይደጋገፋሉ ትውፊት መጽሐፍ ቅዱስን ይጠብቃል ፣ ይተረጉማል ፣ ከመጽሐፍ ቅዱስ የቀረውንም ይሞላል ። ይህንንም ለማረጋገጥ ቅዱስ ጳውሎስ በ2 ጢሞቴዎስ 3፡8 ላይ «ኢያኔስና ኢያንበሬስ ሙሴን እንደ ተቃወሙት» ሲል ይናገራል ። የኢያኔስና የኢያንበሬስ ስም በአሪቱ አልተጻፈም እንደዚሁም በሐዋርያት ሥራ 20፡35 ላይ «ጌታችን እንደተናገረ ከሚቀበል ይልቅ የሚሰጥ ብፁዕ ነው» በማለት የተናገረው በአራቱም ወንጌሎች ተጽፎ አይገኝም ። ቅዱስ ጳውሎስ እነዚህን ሁሉ የጻፋቸው በትውፊት በተገኘው ትምህርት ነው ።

እንደዚሁም አራቱን ወንጌሎች የጻፉ ወንጌላውያን ማቴዎስ ፣ ማርቆስ ፣ ሉቃስና ዮሐንስ መሆናቸው የተገለጠው በትውፊት ነው ።

ታላቁ ቅዱስ ባስልዮስም «መስቀል ማድረግና በመስቀል ማማተብ፣ በጸሎት ጊዜ ፊትን ወደ ምሥራቅ ማዞርና ቀጥ ብሎ መቆም... የመጠመቂያ ውሃን መባረክ ፣ ተጠማቂውን በዐራት መዐዘን ማሰገድ ፣ ተጠማቂዎችን ሜሮን መቀባት ፣ ሰይጣንና ሠራዊቱን «እከህደከ» ማሰኘት ትውፊት እንደሆነ ተናግሮአል ። (ባስልዮስ ድርሳን 27፡66)።

በቤተክርስቲያናችንም ትምህርትና ሥርዓት ፣

– መስቀል ማሳለም ፣

– ለሥዕልና ለመስቀል መስገድ

– ማተብ ማሰር

– በቤተክርስቲያን ዕጣን ማጠን

– በተለያዩ የአምልኮት ሥርዓት ማስፈጸሚያ በሆኑ ንዋያተ ቅድሳት ማገልገል

– የቤተክርስቲያን ሕንፃ አሠራርና የውስጥ ክፍሎች አከፋፈል ።

– ልብሰ ተክህኖና የመሳሰሉትም ሁሉ በትውፊት የተገኙ ናቸው ።

ስለዚህ ቤተክርስቲያናችን ጥንታዊት ታሪካዊትና ሐዋርያዊት ስለሆነች ከቀደምት አበው ሲያያዝ የመጣና ሲሠራበት የኖረውን ትውፊት ጠብቃና አክብራ ትገለገልበታለች ።

www.zeyeneta.com

ምዕራፍ ፲፪

ክብረ ቅድስት ድንግል ማርያም

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ቅድስና ድንግልና ፡ ቃል ኪዳንና አማላጅነት በሰፊው የታመቀ ነው ።

ቅድስና

አምላክን በድንግልና ወንሳ በድንግልና የወለደች እመቤታችን ድንግል ማርያም ከአዳም ዘር የተላለፈ ኀጢአት (ጥንተ አብሶ) ያላገኛት ፡ መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ የሌለባት ገና ከመወለዷ አስቀድሞ በአምላክ ኅሊና ታስባ ትኖር የነበረች ፡ በሰው ልማድና ጠባይ ከሚያርሰው ሥጋዊ አሳብና ፈቃድ ሁሉ የተጠበቀች ፡ ከተለዩ የተለየች ንጽሕት ቅድስተ ቅዱሳን ናት መሓል· 4፡7 ።
«ምልዕተ ፀጋ ምልዕተ ክብር ሆይ! ደስ ይበልሽ» ተብላ በቅዱሳን መላእክት አንደበት በቅድስናዋ ተመስግናለች ፡ ትመሰገናለችም ። (ሉቃ· 1፡28 30) ።

እመቤታችን በውስጥ በአፍአ በነፍስ በሥጋ ቅድስት ስለሆነች እግዚአብሔር ለልጁ ማደሪያ መርጧታል ፡ ማኅደረ መለኮት እንድትሆን አድርጓታል ። አምላክን ለመውለድ ያስመረጣትና ያበቃት ፡ ድንግልናዋ ንጽሕናዋ ነው ። (ሕርያቆስ· ቅዳሴ ፡ 45 መዝ· 132፡13)። ንጽሐ ሥጋ ንጽሐ ነፍስ ንጽሐ ልቡና ለእመቤታችን ገንዘቧ ናቸው ።

ድንግልና

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን ከተለዩ የተለየች ከከበሩ የከበረች የሚያደርጋት ማኅተመ ድንግልናዋ ሳይለወጥ አምላክን በድንግልና ወንሳ በድንግልና መውለዷ ነው (ማቴ· 1፡18 20)። እመቤታችን ጊዜን ከመፅነሷ በፊት ፡ በፀነሰች ጊዜ ፡ ከፀነሰች በኋላ ፡ ከመውለዷ በፊት በወለደች ጊዜ ከወለደች በኋላ ድንግል ናት ። እመቤታችን ከሌሎች ሴቶች ሁሉ ተለይታ እግዚአብሔር ከፈጠራት ጀምሮ በአሳብ ፡ በመናገር ፡

www.zeyeneta.com

በመሥራት ፡ ንጽሐ ጠባይዕ ያላደፈባት ንጽሕት ድንግል ናት ። ቴዎዶሮስ ዘእንቀራ ሃይ አበ· ም· 53፡22/ ድንግል የሚለው ቃል በርግጥ ቅድስናዋን ንጽሕናዋን ያመለክታል ። በዓለም ከነበሩና ከሚኖሩ ሴቶች እንደ እመቤታችን ድንግልናን ከእናትነት ፡ እናትነትን ከድንግልና አስተባብሮ የተገኘች ሴት የለችም ። እመቤታችን ዘለዓለም ድንግል ናት/ ቅዳሴ ባስልዮስ 73 መሐልይ 4፡15 ሕዝ· 44፡3 ወንጌላዊ ሉቃስ «ቅዱስ ገብርኤል ወደ አንዲት ድንግል ተላከ ፡ የዚያችም ድንግል ስም ማርያም ነው» በማለት ስለ ድንግልናዋ ተናግሯል። (ሉቃ· 1፡27) ። እመቤታችን የደናግል ሁሉ መመኪያ ናት ። (ኤፍሬም 6፡3) ።

ክብረ ድንግል

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከመላእክት ትበልጣለች ፡ በክብርም ፡ በአማላጅነትም ፡ ከቅዱሳን ሁሉ ቅድሚያ ያላት ናት ። ሌሎች ሴቶች የሚከበሩ ነቢያትን ሐዋርያትን ጻድቃን ሰማዕታትን ወለዱ ተብለው ነው ። እሷ ግን የምትከበረው እመ አምላክ ፡ ወላዲተ አምላክ ተብላ ነው ። በመሆኑም ድንግል ማርያም ከፍጡራን በላይ ፡ ከፈጣሪ በታች ክብሯ ከፍ ያለ ነው ። የአክብሮት ወይም የጸጋ ስግደት ይሰገድላታል ። (ዮሐ· አፈ· ሃይማ· አበ· ም· 28፡36–39) ።

በእግዚአብሔር ዘንድ ባለሚልኔትን አግኝተሻልና ደስ ይበልሽ «ሉቃ· 1 27»

ምስጋና

ስለ እመቤታችን ክብርና ልዕልና ከሥጋዌ አስቀድሞ ብዙ ትንቢቶች ተነግረዋል ። አምላክን በድንግልና ፀንሳ በድንግልና የመወ ለድዋ ምሥጢርም በነቢያት የተነገረ ነው (መዝ· 132፡13 ፡ ኢሳ· 7፡14 ። ሕዝ· 44፡3) ።

የቤተክርስቲያን አበው ሊቃውንት በየዘመናቸው በመንፈስ ቅዱስ እየተቃኙ በውስጥ አንቺ ቅድስት ነሽ ንጽሕት ነሽ እያሉ ስለ ዘለዓለማዊ ንጽሕናዋና ቅድስናዋ በውዳሴያቸው ፡ በድርሰታቸው አመስግነዋታል ። ውዳሴ ፡ ቅዳሴ ደርሰውላታል ። ከዚያውም ሁሉ እነ ቅ/ኤፍሬም ፡ አባ ሕርያቆስ ቅ/ዮሐንስ አፈወርቅና አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ቅድስት ንጽሕት

www.zeyeneta.com

እያለ በሠፈው አመስግነዋታል ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
ቤተክርስቲያንም ቅድስናዋን ፣ ንጽሕናዋን ትመሰክራለች ፣ ታመሰግናታ
ለችም ። የእመቤታችን ሕይወት ከእግዚአብሔር የማዳን ሥራ ጋር
የተዋሐደ ነው ።

ኖኅ በእግዚአብሔር ጥበብ የሠራት መርከብ ፣ ራሱንና ቤተሰቡን
ከጥፋት ውሀ በማዳን ለሰው ዘር መትረፍ ምክንያት እንደሆነች ሁሉ ፣
እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምም የዓለም መድኃኒት ኢየሱስ
ክርስቶስን በመውለድ ምክንያተ ድኂን ሆናለች ። በቤተክርስቲያናችን
እምነትና ትምህርት ድንግል ማርያም ከፍጡራን በላይ ከፈጣሪ በታች ሆና
ትከበራለች ። በመዝሙራችንም ሆነ በቅዳሴአችን ከስመ ሥላሴ ቀጥሎን
የምንዘምረው የድንግል ማርያምን ውዳሴ ነው ።

አምላክ ሰው በመሆኑ ለሰው ልጆች የዋለውን ውለታ፡— በበረት
መወለዱን ፣ በጨርቅ መጠቅለሉን ፣ ስደቱን ፣ መንከራተቱን ፣ ሕማሙን ፣
ስቅለቱንና ሞቱን በምናስብበት ጊዜ ድንግል ማርያምን መለየት
አይቻልም ።

«ደስ ያለሽ ምልዕተ ክብር ሆይ ፣ ደስ ይበልሽ ከሴቶች ተለይተሽ
አንቺ የተባረክሽ ነሽ ፣ ··· በእግዚአብሔር ዘንድ ባለሟልነትን አግኝተ
ሻልና ··· መንፈስ ቅዱስ ያድርብሻል ፣ የልዑል ኃይልም ይጋርድሻል
ተብሎ የተመሰገነ ከእርስዋ በቀር ማንም የለም ። (ሉቃ· 1፡28–35) ።
ከዘመዶችዋም ወገን ቅድስት ኤልሣቤጥ በመንፈስ ቅዱስ ተቃኝታ
«አንቺ ከሴቶች ተለይተሽ የተባረክሽ ነሽ ፣ የማኅፀንሽም ፍሬ የተባረከ
ነው›› ብላ ከማመስገኗ በላይ የጌታዬ እናት ወደኔ ትመጪ ዘንድ እኔ
ምንድነኝ? በማለት ወላዲተ አምላክ መሆኗን መስክራለች ፣ ከእግዚአ
ብሔር ስለእርስዋ የተነገረው ሁሉ እንደሚፈጸም አምና የምትቀበል ንዕድ
ክብርት እንደሆነች አረጋግጣለች ።

የሰላምታ ድምዕዋን በሰማችም ጊዜ በማኅፀኗ የነበረው ፅንስ
(ዮሐንስ) በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ በመዝለል ከቅድስት ድንግል
የሚወለደው አምላክ ወልደ አምላክ መሆኑን አረጋግጦአል ። ራሷ
እመቤታችን ቅድስት ማርያም «ከእንግዲህስ ወዲህ ትውልድ ሁሉ
ብፅዕት ነሽ እያሉ ያመሰግኑኛል» በማለት ተናግራለች ። (ሉቃ· 1፡48) ።

www.zeyeneta.com

በዚሁ መሠረት በልጅዋ ያመኑ ክርስቲያኖች ሁሉ የንጽሕናቸው ፡ መሠረት የድንግልናቸው መመኪያ ፡ የደኅንነታቸው ምክንያት አድርገው ያመሰግኑአታል ።

የአማላጅነት ቃል ኪዳን

በተክርስቲያናችን ስለ እመቤታችን አማላጅነትና ቃል ኪዳን የምታስተምረው በቅዱስ መጽሐፍ በተጻፈው ቃልና ፍጹም በሆነ ሐዋርያዊ ትውፊት ነው ። እመቤታችን የእናትነት ክብርና የአማላጅነት ቃል ኪዳን ከልጅዋ ከጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተቀብላለች ፡ በቃና ዘገሊላ ሠርግ ቤት ልጅዋ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ውኃውን ወደ ወይን ለውጦ የመጀመሪያውን ተአምር ያደረገው በእመቤታችን አማላጅነት ነው ። (ዮሐ· 2፡1 -5) ። ጌታ በመስቀል ላይ ሳለ «እነሆ ልጅሽ» (ዮሐንስ 19፡26) ብሎ ቤተክርስቲያንን ለርሷ «እነሆአት እናትህ» ብሎ እርሷን ለቤተክርስቲያን አደራ ሰጥቷል ። እመ አምላክ ፡ ወላዲተ አምላክ መሆኗን አምነው «ሰአሊ ለነ ቅድስት» ቅድስት ሆይ ለምኝልን እያሉ ስሟን የሚጠሩትን ሁሉ እንደሚምርላት የማይለወጥ ቃል ኪዳን ተቀብላለች ።

ስለዚህ ቤተክርስቲያን ከልጅዋ ከኢየሱስ ክርስቶስ የተቀበለችውን አደራ በመጠበቅ ቅድስት ማርያም

የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ
የአምላክ እናት
ዘለዓለም ድንግል
ቅድስተ ቅዱሳን ስለሆነች
ቅዱስ መጽሐፍም ይህን ክብሯን ስለሚመሰክር ፡

ቅዱሳን መላእክትና ደቂቀ አዳም ስላከበሯት ፡ በየጊዜው በስሟ ስለሚደረጉ ተአምራት ታከብራታለች ። ታመሰግናታለች ፡ ትማጸንባታለች፡ (ያዕቆብ ዘሥሩግ ቅዳሴ ሐዳፌ ነፍስ፡99)

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከቅዱሳን ሐዋርያት ሲተላለፍ በመጣው ትውፊት በተገለጠው መሠረት በ64 ዓመት ዕድሜዋ በጥር 21 ቀን ዐርፋለች ። መላእክት ሥጋዋን አሳርገው በገነት ከዕፀ ሕይወት ሥር አኖሩት ። በዚያው ዓመት ሥጋዋ እስከ ነሐሴ 14 ቀን በገነት

www.zeyeneta.com

ከቆየ በኋላ ነሐሴ 14 ቀን መላእክት አምጥተው ለሐዋርያት ሰጡአቸውና በጌቴሴማኒ ቀበሩአት ፡ በሦስተኛው ቀን ነሐሴ 16 ቀን ተነሥታ ፡ በክብር ወደ ሰማይ ዐርጋለች ። የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ስለ ቅድስት ድንግል ማርያም ዕረፍት ፡ ትንሣኤና ዕርገት ይህን ታምናለች። ታሳምናለች ። በየዓመቱም ነሐሴ 16 ቀን የፍልሰትዋን መታሰቢያ በታላቅ ሥነ ሥርዓት ታከብራለች (ስንክሳር ነሐሴ 16 ቀን) ።

ምዕራፍ ፲

ክብረ ቅዱሳን

ቅዱስ የሚለው ቃል በግእዝ ንጹሕ ክቡር ልዩ መሆንን የሚያመለክት ነው ። ይህ ቃል ለእግዚአብሔር የባሕርይ መገለጫ ነው ። እግዚአብሔር በባሕርዩ ቅዱስ ነውና ። ቅዱሳን የሚለውም ቃል በባሕርዩ ቅዱስ የሆነውን አምላክ ለሚያገለግሉ መላእክትና ደጋግ ሰዎች የሚሰጥ ነው ።

መላእክትን ቅዱሳን እንላቸዋለን ። ከማንኛውም ክፋ ነገር የራቁ ሥርዓታቸውን የጠበቁ ፡ እግዚአብሔርን ያወቁ ፡ እግዚአብሔርን የሚያመሰግኑ ስለሆኑ ቅዱሳን ይባላሉ ። ከመወርገ መላእክት የደረሱ ደጋግ ሰዎችም በዘሁ የቅድስና ስም ይጠራሉ ። ራሱ ቅዱስ እግዚአብሔርም እኔ ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁኑ ··· ብሎአል ። (ዘሌዋ· 19፡2 1ጴጥ· 1፡15 16) ።

ነቢያት ፡ ሐዋርያት ጻድቃን ሰማዕታት ሁሉ ለቅዱስ እግዚአብሔር ሲሉ ሕይወታቸውን መሥዋዕት አድርገው ስለሰጡ ፡ ለስሙ ስለመሰከሩ ፡ በተጋድሎአቸውና በትሩፋታቸው ስላገለገሉ የቅድስናና የብፅዕና ማዕርግ ተሰጥቶአቸዋል ፡ ይሰጣቸዋልም ። ጌታችንም በወንጌል «አባት ሆይ በእውነትህ ቀድሳቸው ቃልህ ቅዱስ ነው» ብሎ ስለቅድስናቸው ተናግሮአል ። (ዮሐ· 17፡17) ።

ከእነዚህ ሁሉ በላይ ግን ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም የቅዱሳን አክሊል የሆነች ቅድስት ናት ፡ ስለዚህም ቅድስተ ቅዱሳን ትባላለች ።

www.zeyeneta.com

ሀ) ክብረ መላእክት ቅዱሳን

ተፈጥሮአቸው

መላእክት በዕለተ እሑድ ከተፈጠሩ ፍጥረታት አንድ ክፍል ናቸው (ኩፋ· 2፡6–8) ። የመላእክት ተፈጥሮ ከእሳትና ከነፋስ እንደሆነ ቅዱስ መጽሐፍ ያስረዳል ። (3መቃ· 2፡10–11) ።

መላእክት አንድ ጊዜ የተፈጠሩና በየጊዜው የማይባዙ ናቸው ። መላእክት በተፈጥሮአቸው ነባብያን ለባውያን ሕያዋን ነያላንም ናቸው ። ሕማምና ሞት የለባቸውም ። የመላእክት ቁጥር በእንዝ አይወሰንም ፡ የብዙ ብዙ ናቸው ። መላእክት በነገድና በአለቃ ይከፈላሉ ፡ በነገድ መቶ በከተማ ዐሥር እንደነበሩ ይታወቃል ።

አገልግሎታቸው

ቅዱሳን መላእክት ለእግዚአብሔር የቅርብ አገልጋዮች ናቸው ። ዘወትር በዙፋኑ ዙሪያ ሆነው ያመሰግኑታል (ራእ· 4፡8፡11) ። በተልእኮአቸውም ፈጣኖች ናቸው መዝ· 103፡4 (ዕብ 1፡6) ። በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ለተልእኮ ይወርዳሉ ይወጣሉ ለሰው ልጆችም ይራዳሉ (ዮሐ· 1፡52 ፡ ዕብ· 1፡14) ።

— የመላእክት ተልእኮ በጥቅሉ ሲገለጥ በሰውና በእግዚአብሔር መካከል መላላክ ፡

— የሰውን ጸሎት ምጽዋትና መሥዋዕት ወደ እግዚአብሔር ማቅረብ፡

— የእግዚአብሔርንም ምሕረትና ቸርነት ወደ ሰዎች ማድረስ ነው ። (ዳንኤል 9፡20–22 ። ሉቃ· 1፡13 ። የሐዋ· 10፡3–5) ።

— ሰዎች በሞቱ ጊዜ ነፍሶቻቸውን ወደ እግዚአብሔር ያቀርባሉ (ሉቃ· 16፡22 ። ሱቱ· ዕዝ· 6፡6–20) ።

— እያንዳንዱን ፍጥረት አዘውትረው ይጠብቃሉ (ማቴ· 18፡10 ። ዳን· 4፡13) ።

— ለምሕረትም ለመዓትም ይላካሉ (ሮሜ 9፡22) ።

— በመከራና በችግር ጊዜ ለተራዳኢነት ይላካሉ (የሐዋ· 12፡7 -11 ፡ መዝ· 89፡7) ።

www.zeyeneta.com

በፍጻሜ ዘመንም ይህ ዓለም በሚያልፍበት ጊዜ ይላካሉ ፡ ኑዮአንን ከዳጽቃን ይለያሉ (ማቴ· 24፡31 ። ራእ· 7፡1 4) ።

አማላጅነታቸው

የቅዱሳን መላእክት አማላጅነትና ተራዳኢነት የሰዎችን ጸሎትና ምጽዋት ወደ እግዚአብሔር ለማቅረብ በተሰጣቸው ባለሚልነት ነው ። በቅዱስ መጽሐፍ በሰፈው እንደምንረዳው የብዙዎችን ሰዎች ጸሎት መሥዋዕትና ምጽዋት ወደ እግዚአብሔር እያቀረቡ የሚፈልጉትን መልካም ነገር ሁሉ ያሰጣሉ ። ደስታራ የምሥራችን ሁሉ ለሰዎች ያበስራሉ ። ደስታን ማብሠር ፡ ማጽናናትና የምሥራችን መንገር ከእግዚአብሔር የተሰጣቸው ጸጋ ነው ። (ዘፍ·48፡16 ፡ ዳን·10፡10 12 ፡ ሉቃ· 1፡13 ፡ ሉቃ·1፡28 32 ፡ ይሁዳ 9) ።

የቅዱሳን መላእክት አማላጅነት በቅዱሳት መጻሕፍት በስፋት ይነገራል ። በተለይ በሄኖክ ምዕራፍ 10፡7 እና በዘካርያስ 1፡12 ዘጸአ 23፡ 20 23፡ መዝ· 33፡7 ላይ የተመለከቱት ጥቅሶች በግልጥ ያስረዳሉ ።

ቅዱሳን መላእክት ንስሓ ገብተው በተመለሱ ሰዎች ደስታ እንደሚ ያደርጉ በሉቃስ ወንጌል 15፡10 ላይ የተጻፈው ስለ ሰው ልጆች ደኅንነት ያላቸውን ፍቅርና አማላጅነት ያመለክታል ።

ክብራቸው

ቅዱሳን መላእክት በእግዚአብሔር ፊት የሚቆሙ ባለሚሎች ስለሆኑ ፡
ለአምላካቸው ቀናኢያን
ለነፍሳት ቀዋምያን ስለሆኑ
ለምሕረትም ለመዓትም ስለሚላኩ
ሰዎችን በችግራቸው ጊዜ ስለሚረዱና ስለሚያማልዱ በተክበርስቲያን ታክብረቸዋለች ። በስማቸው ጽላት ቀርፃ ፡ በተክርስቲያን አሳንፃ ድርሳናቸውን አስጽፋ እንዲመሰገኑና እንዲከበሩ ታደርጋለች ። የአጋና የአክብሮት ስግደት ይሰገድላቸዋል ። (ዳንኤል 8፡15–18፡ ዘፍ· 22፡31። ዘኑል· 22፡31፡ ኢያሱ 5፡13 15) ።

www.zeyeneta.com

ለ) ቅዱሳን ነቢያት

ነቢያት በመንፈስ እግዚአብሔር እየተቃኙ የወልደ እግዚአብሔርን ሰው መሆን እስከ ዳግም ምጽአቱ ተንብየዋል። ይህንንም ተልእኮአቸውን በፈጸሙበት ጊዜ እስከ ሞት ድረስ ፀዋትወ መከራ የተቀበሉ አሉ። በዚህም መሠረት ቤተክርቲያናችን በቅድስናቸው ታከብራቸዋለች። ቅድስናቸውንም ትመሰክራለች።

የዓለም መድኃኒት ኢየሱስ ክርስቶስ ዓለሙን በደሙ ለማዳን እንደሚመጣ በትንቢትና በምሳሌ የተናገሩበትን የተስፋ ዘመን ለማስታወስ "ጸመ ነቢያት" በመባል በሚታወቀው ዘመነ ሱባዔ ከአዳም እስከ ክርስቶስ የተነሡ አበው ነቢያትን ታስታውሳቸዋለች።

ሐ) ቅዱሳን ሐዋርያት

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "አብ እኔን እንደላከኝ እንዲሁ እኔ እልካችሁአለሁ፣ ወደ ዓለም ሁሉ ሂዳችሁ ወንጌልን ለፍጥረት ሁሉ አስተምሩ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቁ..." ብሎ በላካቸው መሠረት ዓለምን ዙረው ያስተማሩና ስለክርስቶስ ስም የመሰከሩ ሐዋርያት ክርስቶስ የመረጣቸውና የቀደሳቸው ቅዱሳን ናቸው። በሐዋርያት እግር ተተክተው ስለ ስሙ የመሰከሩና የሚመሰክሩ ሁሉ የዚህ ክብርና ቅድስና ወራሾች ናቸው።

መ) ቅዱሳን ሰማዕታት

ስለ ክርስቶስ ስም በዓለውያን ነገሥታት ፊት እየቀረቡ ሳይፈሩና ሳያፍሩ የመሰከሩ በዚህም ምክንያት ሕይወታቸውን የሠዉ ሰማዕታት ቅዱሳን ናቸው።

ሠ) ጻድቃን

ሰው ዓለሙን ሁሉ ቢገዛና ቢነዳ በነፍሱ ግን ከተጐዳ ምን ይጠቅመዋል? (ማቴ.16፡26) ። ተብሎ በተጻፈው መሠረት ሕይወታቸውን ለእግዚአብሔር ሰጥተው፣ ከዓለም ተለይተው፣ በበዓት ተወስነው፣ ግርማ ሌሊትን ድምፀ አራዊትን ፀብዐ አጋንንትን ታግሠው ፣ በምናኔ በተባሕትዎ በገድል በትሩፋት ዘመናቸውን ያሳለፉ ፣ ከክፉ ነገር የራቁ ፣

www.zeyeneta.com

ጣዕመ ዓለምን የናቁ ፡ የሚታየውን በማይታየው ለውጠው የኖሩ ሁሉ የቅድስና መዓርግ አግኝተዋል ።

እነዚህን ስለ እግዚአብሔር ስምና ክብር የተጋደሉ ቅዱሳን ቅድስት ቤተክርስቲያን በዕድሜ በነገድ በያታ ሳትለይ ለሁሉም በቀኖናዋ መሠረት የቅድስና መዐርግ እየሰጠች ፡ ገድላቸውንና የሕይወታቸውን ታሪክ እየጻፈች ፡ ያደረጉትንና በየጊዜውም የሚያደርጉትን ተአምራት እየመዘገበች በስማቸው ጽላት እየቀረፀች ፡ ቤተክርስቲያን እያሳነጸች ስማቸውና ክብራቸው የቅድስናም ታሪካቸው ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላለፈ ሲነገር እንዲኖር አድርጋለች ታደርጋለችም ።

የቅዱሳን ቃል ኪዳንና አማላጅነት፡

ቅዱሳን በዚህ ዓለም ሳሉ ባደረጉት ተጋድሎ በእግዚአብሔር ዘንድ ባለሙዋልነት ተሰጥቷቸዋል ። በዚህ ዓለም ሳሉ ሙታንን በማንሣት ፡ ድውያንን በመፈወስ ፡ አጋንንትን በማውጣት ብዙ የተአምር ሥራ እንዲሠሩ መንፈሳዊ ኃይልና ሥልጣን እንደተሰጣቸው ሁሉ ከዚህ ዓለም በሞት በሚለዩበት ጊዜም ስማቸውን የሚጠራ ፡ መታሰቢያቸውን የሚያደርግ ፡ በአማላጅነታቸው የሚያምን ሁሉ ዋጋ እንደሚያገኝ ከልዑል እግዚአብሔር ቃል ኪዳን ተሰጥቶአቸዋል ። ጻድቁን በጻድቅ ፡ ነቢዩን በነቢይ ስም የተቀበለ በክርስቶስ ተከታዮችና አገልጋዮች ስም ቀዝቃዛ ውሃ እንኳ የሰጠ ዋጋው እንደማይጠፋበት ጌታችን በወንጌል አረጋግጦአል ። (ማቴ 10፡41–42)።

ቅዱሳን በዐፀደ ሥጋ ብቻ ሳይሆን በዐፀደ ነፍስም ያማልዳሉ ፡ ለዚህም ቅዱሳት መጻሕፍት ይመሰክራሉ (ዘጸአ 32፡2–15 ፡ ሄኖክ 12፡33–40) በነፍስ ሕያዋን ናቸውና (ሉቃ 20፡37–40)።

የእግዚአብሔር ቃል ሕያው ነው ፡ በሕያዋንም ላይ ሲሠራ ይኖራል፡ ቃል ኪዳኑም አይለወጥም ፡ ቅዱሳኑም ሕያዋን እንደሆኑ ራሱ ተናግሯል። በዚህ እምነትና ትምህርት መሠረት ቤተክርስቲያን የቅዱሳን ሐዋርያትን የሰማዕታትንና የጻድቃንን ቃል ኪዳንና ክብር ትቀበላለች።

ስለ ክርስቶስ ስምና ክብር ሁሉን ትተው የተከተሉት ፡ በተጋድሎአቸውም መስቀሉን ተሸክመው በመከራው የመሰሉት ቅዱሳን

www.zeyeneta.com

በተሰጣቸው ቃል ኪዳን በዚህ ዓለም ላሉ ብቻ ሳይሆን ክርስቶስ ዳግመኛ ለፍርድ በሚመጣበት ጊዜ በ12 የፍርድ ዙፋን ተቀምጠው በእስራኤል ዘነፍስ እንደሚፈርዱ ቃል ኪዳን ተሰጥቶአቸዋል ። (ማቴ· 19፡28)።

ቅዱሳንን ከአምላካቸው በተሰጣቸው ቃል ኪዳን መሠረት ቤተክርስቲያን ታከብራቸዋለች ። ምእመናን ይማጸኑባቸዋል ። ቤተክርስቲያን በስማቸው እየሠሩ መታሰቢያቸውን እያደረጉ ፡ ሥዕላቸውን እየሣሉ የቅድስና ሕይወታቸውን ሲያስታውሱ ይኖራሉ።

ረ) ክብረ ዐፅመ ቅዱሳን

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በገድላቸውና በትሩፋታቸው ፡ እግዚአብሔርን አገልግለው ስለ ስሙና ስለ አምልኮቱ መስክረው በሞት የተለዩ ቅዱሳንን ዐፅም ታከብራለች።

በሕይወት ሳሉ በትምህርታቸውና በጸሎታቸው ፡ ከሞትም በኋላ በመቃብራቸው ወይም በዐፅማቸው ላይ የተለያየ ምልክት የታየላቸው ቅዱሳን ዐፅማቸው ከቤተ ክርስቲያን ቅፅር ግቢ በልዩ ቦታ በክብር እንዲቀመጥ ያደረጋል።

የጥንት ክርስቲያኖች በስደት ጊዜ ከቦታ ወደ ቦታ ሲዘዋወሩና በግዘፀ ምድር ሲኖሩ የቅዱሳን ሐዋርያትንና የሰማዕታትን ዐፅም በክብር ጠብቀው ይኖሩ ነበር ። እግዚአብሔርም በቅዱሳኑ ዐፅም አማካኝነት ተአምራትን ያሳያል በረከትንና ልዩ ልዩ ፈውስን ይሰጣል ። (2 ነገሥ·13፡20 21)።

ለቅዱሳን ዐፅም ክብር መስጠት ፡ በክብር ማስቀመጥና መጠበቅ መጽሐፋዊ መሠረት አለው ። እስራኤላውያን የያዕቆብንና የዮሴፍን ዐፅም ከግብጽ በክብር አውጥተው በክብር ቦታ አኑረውታል ። (ዘጸአ·13፡19፡ ኢያሱ· 24፡32 የሐዋ·7፡15)። ከአዳም እስከ ኖኅ የነበሩ አበውም ዐፅማቸው ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላለፈ በክብር ተጠብቆ ይኖር እንደነበርና በማየ አይኅ ጊዜም ኖኅ በመርከብ ውስጥ ይዞት እንደገባ የታሪክ ትውፊት ያስረዳል ።

ነፍሳቸው በገነት ያለች ቅዱሳንን ካከበርን ከነፍሳቸው ጋር መከራ የተቀበለና የተሠቃየ ሥጋቸውንና ዐፅማቸውንም ልናከብር ይገባል። (ኩፋ·ነገ·አን·20)።

www.zeyeneta.com

እግዚአብሔር የቅዱሳንን ዐፅም ለፈውስና ለተለያየ ጸጋ ምልክት ስለሚያደርገው ቤተክርስቲያናቸን ታከብረዋለች ። ልዩ የክብር ቦታም ትሰጠዋለች ። (መዝ·33፡19 -20)።

ቅዱሳን ያማቸው በፈሰሰበት ዐፅማቸው በተከሰከሰበት ገድላቸው በተፈጸመበት ፡ ወላቸው በነጠበበት ፡ ቤተክርስቲያናቸው በታነጸበት ፡ ስማቸው በተጠራበት ሁሉ ተአምራት ሲያደርጉ ይኖራሉ የክብራቸውና የቅድስናቸው ምልክትም ይህ ነው ። የቅዱስ እግዚአብሔር ምስክሮች ናቸውና። (መዝ·33፡20 ሉ·ቃ·24፡47)

ምዕራፍ ፱

ቤተክርስቲያን

ቤተክርስቲያን የሚለው ቃል ሁለት ፍች አለው። አንደኛው ብክርስቶስ አምነው የተጠመቁ የምእመናን አንድነት ወይም ማኅበረ ምእመናን ነው ። (ፍት·ነገ·አን 1 ፡ ማቴ· 18፡17 ፡ የሐዋ·20 ፡28) በብሉይ ኪዳን የነበሩ ሕዝበ እግዚአብሔር ቤተ እሥራኤል ተብለው ይጠሩ እንደነበሩ በሐዲስ ኪዳን ያሉ ሕዝበ እግዚአብሔርም ቤተክርስቲያን ተብለዋል ። ይህም ሕዝበ ክርስቲያን ነገደ ክርስቲያን ማለት ነው።

ሁለተኛው አምልኮተ እግዚአብሔር የሚፈጸምበት ምእመናን የሚሰበሰቡበት ሕንፃ ቤተክርስቲያን ነው።

ሐመረ ኖኅ ፡ ሐይመተ አብርሃም ደብተራ ኦሪትና መቅደስ ሰሎሞን ለቤተክርስቲያን ምሳሌዎች ሆነው መሥዋዕት ሲሠዋባቸው አምልኮተ እግዚአብሔር ሲፈጸምባቸውና ስመ እግዚአብሔር ሲቀደስባቸው ኖረዋል።

እነዚህ ሁሉ ካለፉ ዘኁላ የቤተክርስቲያን መሠረትና ራስ የሆነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አማናዊት ቤተ ክርስቲያንን በደሙ መሠረተ።

የቤተክርስቲያን አባቶች ብጸሎተ ሃያማኖት ውስጥ በመሰኑት መሠረት ፡ ቤተክርስቲያን «አንዲት ቅድስት በሁሉ ዘንድ ያለች ሐዋርያት የሰበሰቡአት» ትባላለች (ጸሎተ ሃያማኖት)

www.zeyeneta.com

ቤተክርስቲያን :— ማኅደረ እግዚአብሔር ናት ፥

- የትምህርት የጸሎትና የአምልኮት ቤት ናት ። (ማቴ 21፡13 ፥ ዮሐ 2፡7 ፥ መዝ 68፡9)።
- የጎጢአት ማስተሥርያ መስገጃና መማጸኛ ናት ፥
- ወንጌል ይሰበክባታል ፥ ቅ/ቁርባን ይቀርብባታል፥ በጥምቀት ልጅነት ይሰጥባታል ፥
- የክርስቲያኖች ዐፅም ያርፍባታል ፥
- በሰዎች መካከል የዕድሜ ፥ የኀገድ የጸታ ልዩነት ሳይደረግ መንፈሳዊ አገልግሎት ይሰጥባታል ።
- ቤተክርስቲያንን ቤተክርስቲያን የሚያሰኙትና ከሌላው ቤት ልዩ የሚያደርጋት፡—
- በኤጲስ ቆጶሳት (ጳጳሳት) ጸሎትና ቡራኬ ትቀደሳለች፡
- በቅብዐ ሜሮን ትከብራለች፡
- ታቦተ ሕግ ይቀመጥባታል፡
- ምሥጢራት ቤተክርስቲያን ሁሉ ይፈጸሙባታል።

እንደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሥርዓትና ትውፊት የቤተክርስቲያን የሕንፃ አሠራር የተለያየ ሆኖ በመሠረተ አቅዋም ሦስት ክፍል አለው፡

ሀ) **ቅኔ ማሕሌት**— መዘምራን ስብሓተ እግዚአብሔር ማሕሌተ እግዚአብሔር የሚያደርሱበት ክፍል ነው።

ለ) **ቅድስት** :— የቤተክርስቲያኑ ማዕከላዊ ክፍል ነው ፥ ምእመናንም ሥጋውንና ደሙን የሚቀበሉበት በዚሁ ነው ።

ሐ) **መቅደስ** :— ታቦተ ሕጉ የሚቀመጥበት መንበር ያለበት ሥጋውና ደሙ የሚፈተትበት ባጠቃላይ ሥርዓተ ቅዳሴው የሚፈጸምበት ዋና ክፍል ነው። በዚህ ክፍል መግባት የሚችሉ ሥልጣነ ክህነት ያላቸው ብቻ ናቸው ። እንደ ኢትዮጵያ

www.zeyeneta.com

አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሥርዓት ቤተ መቅደሱ ሦስት ዋና በሮች አለ።

ምዕራብ፡ ስብሓተ እግዚአብሔር ይደርስበታል ሥጋውና ደሙ ይሰጥበታል።
ሰሜን፡ ወንዶች ምእመናን ያስቀድሱበታል ካህናት ሰዓታት ያደርሱበታል ።
ደቡብ፡ ምእመናት ሴቶች ያስቀድሱበታል ይጸልዩበታል ።

በቤተክርስቲያን ጉልላት ላይ መስቀል ይደረጋል የቤተክርስቲያን አርማ መስቀል ነውና ። የመስቀል ምልክት ከሌለው ቤተክርስቲያን አይባልም። በቤተክርስቲያን በስተምሥራቅ ቤተልሔም በስተምዕራብ ደጀ ሰላም ይገኛል። ሁሉም የተለያየ አገልግሎት አላቸው።

ምዕራፍ ፲

ታቦት

ታቦት እግዚአብሔር በደብረ ሲና ዐሠርቱ ቃላትን በላዩ ጽፎ ለሙሴ ለሰጠው ጽላት ማደሪያ ፡ ማኖሪያ ነው ። በቤተክርስቲያናችን ግን ጽላቱ ታቦት እየተባለ ይጠራል ። ይህም አዳሪውን በማደሪያው ለመጥራት ነው ። ታቦቱ የጽላቱ ማደሪያ ማኖሪያ ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔር መገለጫ ነው ። በታቦት ፊት የሚጸለየው ፡ የሚሰገደው ዐሠርቱ ቃላት ስለተጻፉበት ብቻ አይደለም እሥራኤል ንጢአት ሠርተው ሲበድሉ ፡ ሲያሳዝኑትና ሲያስቀይሙት ፡ ተመልሰው ንስሓ ገብተው ሲያለቅሱና ሲለምኑት እግዚአብሔር እየራራ በቃል ኪዳን ታቦቱ እየተገለጠ ይመራቸውና ያነጋግራቸው ስለነበረ ታቦት የምህረትና የደኅንነት መገለጫም በመሆኑ ነው። ዘፀ (25፡20-25)።

የታቦት አገልግሎት በብሉይ ኪዳን ተጀምሮ የቀረ አይደለም። ጽላተ ሙሴ ወደ አትዮጵያ ስለመጣች ሀገራችን ኢትዮጵያ ከክርስትና በፊት ብሉይ ኪዳንን ተቀብላ አምልኮተ እግዚአብሔርን አጽንታ

www.zeyeneta.com

ቍጽጋለች ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ብሉይ ኪዳንንና ሥርዓቱን ተቀብላ በመጠበቅ ብቻ ያቆየችው አይደለም። ጌታ በወንጌል "አሪትንና ነቢያትን ልፈጽማቸው እንጂ ልሽራቸው አልመጣሁም ። እውነት እውነት እላችኋለሁ ሥራዋ አንዲት ፡ አቀራረጿ አንዲት የምትሆን የውላ ሰማይና ምድር እስኪያልፍ ሁሉም እስኪሆን ፡ እስኪደረግ ድረስ ከአሪት ከነቢያት ተለይታ አታልፍም ከነዚህ ትእዛዛት አንዲቱን አሳንሶ የሻረ ፡ ለሰው እንዲህ ታንሳለች ብሎ የሚያስተምር በመንግሥተ ሰማይ ታናሽ ይሆናል ። እንዲህ የሚሠራ የሚያስተምር ግን እርሱ በመንግሥተ ሰማይ ታላቅ ይሆናል" ። (ማቴ· 5፡17 19) ብሎ ባስተማረው መሠረት ፡ ቤተክርስቲያን ከብሉይ ኪዳን ወስዳ ከምትገለገልባቸው አንዱ ስመ እግዚአብሔር የተጻፈበት ጽላተ ኪዳን (ታቦት) ነው ። ታቦት ፡ በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ጸንቶ ለሚኖረው ቃል ኪዳን ሕያው ቃል የተጻፈበት የኪዳን ምስክር ነው ። ጥንታዊት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሥርዓተ አሪትን ከሥርዓተ ወንጌል አጣምራ የያዘች ስለሆነ በክርስትና ጊዜ ከብሉይ ኪዳን ያገኘቻቸውን በክርስትና መንፈስ እየተረጐመች ትገለገልባቸዋለች።

እሥራኤል ታቦተ ኪዳኑን እየያዙ በተንዘባቸው መንገዶችና በሠፈሩባቸው መንደሮች ሁሉ ብዙ የተአምራት ሥራ ተሠርቶላቸዋል ። ጽላተ ሕጉን ያዘው በዘመቱባቸው የጦር መስኮች ሁል ድል አድርገው በታል ። ንጠኢት በሠሩ ጊዜ ረድኤተ እግዚአብሔር እየተነሣቸው ድል ይሆኑ ነበር ። (ሳሙ· 4፡11) በሀገራችንም ታቦት ንዴለ መዊእና ንዴለ ረድኤት ያለው በመሆኑ ቤተክርስቲናችን የውጭ ጠላት በተነሣ ጊዜ ሁሉ ታቦታን እየያዘች በግንባር ቀደምትነት በመሰለፍ ድል ስታደርግበትና ሀገሯን ስትጠብቅበት ኖራለች። በታቦተ ሕጉ አምነው የተቀበሉት ፡ ያከበሩት ሁሉ የተአምራቱ በረከት ሲደርሳቸው የተዳፈሩትና ሳይገባቸው የነኩት ደግሞ ተቀስፈውበታል ። ጠፍተውበታልም ። (1 ሳሙ· ምዕ·4፡4-6 ፡ 2 ሳሙ·ምዕ·6)።

ታቦት በሐዲስ ኪዳንም በቤተክርስቲያናችን አምልኮተ እግዚአብሔር ይፈጸምበታል። ታቦት እውነተኛው የሕይወት ምግብ የክርስቶስ ሥጋና ደም የሚቀርብበትና የሚፈተትበት መሠዊያ ነው። የሚከበረውና የሚሰገድለትም ስለዚህ ነው ።

www.zeyeneta.com

ቅዱስ ጳውሎስ "ክርስቶስን ከሰይጣን ጋር አንድ የሚያደርገው ማነው? ምእመናንንስ ከመናፍቃን ጋር አንድ የሚያደርጋቸው ማነው? የእግዚአብሔርንስ ታቦት በጣዖት ቤት ውስጥ የሚያኖር ማነው?" በማለት አስተምሮአል ። (2 ቆሮ 6፡15 16)።

ከዚህም በላይ ወንጌላዊ ዮሐንስ "ከዚህ በኋላ በሰማይ ያለው የእግዚአብሔር መቅደስ ተከፈተ በመቅደሱም ውስጥ የእግዚአብሔር የሕጉ ታቦት ታየ" በማለት በራእዩ ገልጾአል ። (ራእ 11፡19) ።

ስለዚህ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ከብሉይ ኪዳን የተቀበለችውን ታቦተ ሕግ አክብራ በራሷ እየተሸከመች አምልኮተ እግዚአብሔርን ስትፈጽም ፡ ስለእግዚአብሔር ስም በአደባባይ ስትመሰክር ትኖራለች ። ታቦት ለቤተክርስቲያናችን ትልቁ የእምነትና የሥርዓት መገለጫ ነው ። ታቦት በስመ ሥላሴ ፡ በቅድስት ድንግል እመቤታችን ፡ በቅዱሳን መላእክት በነቢያት ፡ በሐዋርያት ፡ በጻድቃንና ሰማዕታት ስም ይቀረጻል ። ታቦት በማይገባቸው ሰዎች ቢገሠሥ ቢማረክ እንደገና በኤጲስ ቆጶስ ጸሎት ተባርኮ ይቀደሳል ፡ ሜሮን ተቀብቶ ይከበራል ።

- ሙሴ እንደ መጀመሪያዎቹ ጽላት እንደገና እንዲቀርጽ በታዘዘው መሠረት ጽላት በየጊዜው ይቀረጻል ፡ (ዘፀ 34 ፡ 1) ።
- ታቦት ስመ እግዚአብሔር ስለ ተጻፈበት ይሰገድለታል (ፊል 2፡ 10) ።
- እንደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን እምነትና ሥርዓት ታቦት ከማይነቅዝ ዕፅና ከዕብነበረድ ይቀረጻል ።
- በታቦቱ ላይ ስመ እግዚአብሔር በ4 ገጽ ይጻፍበታል ።
- ሥዕለ ኪሩብ ሥዕለ ሥላሴ ሥዕለ ቅ ድንግል ማርያም ሥዕለ ዮሐንስ ወንጌላዊ ይሣልበታል ።
- በኤጲስ ቆጶስ ጸሎት ተባርኮ ይቀደሳል ፡ ሜሮን ተቀብቶ ይከብራል ፡ ከዚያም በመንበሩ ይሰየማል ።
- ጽላት በሌለበት ቤተክርስቲያን ቅዳሴ አይቀደስም ። ቤተክርስቲያንም አይባልም ።
- ታቦቱን ለመያዝና ለመሸከም ሥልጣን ያላቸው ቋሚዎችና ቀሳውስት ናቸው ።

www.zeyeneta.com

ምዕራፍ ፲፩

ሃይማኖትና ምግባር

ሃይማኖትና ምግባር ሁለቱ በአንድነት በክርስትና ሕይወት ውስጥ ሲገኙ ደኅንነትን እንደሚያሰጡ ቤተክርስቲያናችን ታምናለች ታስተምራለችም ። ነገር ግን እምነት ይቀድማል ፣ መልካም ሥራ ይከተላል ።

ታላቁ የቤተክርስቲያን አባት ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ እንደገለጠው «እምነት መሠረት ናት ፣ ሌሎቹ ግን ሕንፃና ግንብ ናቸው» ። ይኸው አባት ይህን ሲያብራራ እንዲህ ይላል «መሠረት ሕንፃውን ሁሉ እንደሚሸከም እምነትም ምግባራትን ሁሉ ትይዛለች ማለት ምግባር ታሠራለች ። ሕንፃ ያለ መሠረት ሊቆምና ሊታይ እንደማይችል ክርስቲያንም ያለ ምግባር ክርስቲያን መሆን አይችልም» ብሎአል ። (ዮሐ· አፈወርቅ ድርሳን 9)።

ሃይማኖት ተስፋ ስለምናደርገው ነገር የሚያረጋግጥ ፣ የማናየውንም ነገር የሚያስረዳ ነው ። ለአባቶች የተመሰከረላቸው በዚህ ነውና ። (ዕብ· 11፡1–2)። ሃይማኖት የማይታየውን እንደሚታይ አድርጎ ሊያረጋግጥና ሊያስረዳ የሚችለው በምግባር ሲገለጥና ሲጸና ነው ።

ቅዱስ ጳውሎስ «ሃይማኖት ፣ ተስፋ ፣ ፍቅር እነዚህ ሦስቱ ጸንተው ይኖራሉ ፣ ከእነዚህም የሚበልጠው ፍቅር ነው» በማለት ለምግባር ከፍተኛ ደረጃ ሰጥቶአል ። (1 ቆሮ· 13፡13)።

ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብም እምነትና ምግባር በክርስቲያናዊ ሕይወት ውስጥ መነጣጠል እንደሌለባቸው ሲገልጥ ሥራ የሌለው ሃይማኖት አይጠቅምም ፣ አያድንም ፣ እምነት ፍጹምና ሕያው ሊሆን የሚችለው በሥራ ነው ። ሃይማኖትና ምግባር የሌሉት ሰው ከንቱ ነው ፣ ከነፍስ የተለየ ሥጋ የሞተ እንደሆነ እንዲሁ ደግሞ ከሥራ የተለየ ሃይማኖት የሞተ ነው ካለ በኋላ የአብርሃምና የረዐብን እምነትና ምግባር ምሳሌ አድርጎ አቅርቦአል ። (ያዕ· 2፡14–26)።

በዚህ መሠረት መልካም ሥራ የሃይማኖት ውጤት ወይም ፍሬ ነው እውነተኛ ሃይማኖት ያለው ሁሉ ግድ መልካም ሥራ ይሠራል ። (1 ቆሮ· 13፡2)።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም «መልካም ፍሬ የማያፈራ ዛፍ

www.zeyeneta.com
ይቆረጣል ፡ ወደ እሳትም ይጣላል» (ማቴ· 7፡19)። ካለ በኋላ «በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ ጌታ ሆይ ፡ ጌታ ሆይ የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም» ብሎ መዳን ወይም መንግሥተ ሰማያት መግባት የሚቻለው ምግባር በሃይማኖት መሠረትነት ላይ ሲጸና ሃይማኖትም በምግባር ሲገለጥና ሲፈጸም መሆኑን ተናግሮአል ። (ማቴ· 7፡20–21 ፡ ሉቃ 3፡8)።

በፍርድ ቀን ማንም ሰው የሚጠየቀው አምኖ ስለሠራው ሥራ ነው እንጂ ምግባር ስለሌለው ሃይማኖቱ አይደለም (ማቴ· 25፡41–45)። በቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ የተነገረው ሁሉም እንደየሥራው ዋጋውን ይቀበላል የሚል ነው ። (ማቴ· 16፡27 ፡ ዮሐ· 5፡28–29 ፡ 2 ቆሮ· 5፡10 ፡ ራእ· 14፡13 ፡ 20፡12 እና 22፡12)።

በዚህ መሠረት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሃይማኖት ብቻውን እንደማይጠቅም አውቃ በሃይማኖት ላይ ምግባር መሥራት እንደሚገባ ታምናለች ታስተምራለች ።

www.zeyeneta.com

ምዕራፍ ፲፩

ሃይማኖትና ምግባር

ሃይማኖትና ምግባር ሁለቱ በአንድነት በክርስትና ሕይወት ውስጥ ሲገኙ ደኅንነትን እንደሚያሰጡ ቤተክርስቲያናችን ታምናለች ታስተምራለችም ። ነገር ግን እምነት ይቀድማል ፣ መልካም ሥራ ይከተላል ።

ታላቁ የቤተክርስቲያን አባት ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ እንደገለጠው «እምነት መሠረት ናት ፣ ሌሎቹ ግን ሕንፃና ግንብ ናቸው» ። ይኸው አባት ይህን ሲያብራራ እንዲህ ይላል «መሠረት ሕንፃውን ሁሉ እንደሚሸከም እምነትም ምግባራትን ሁሉ ትይዛለች ማለት ምግባር ታሠራለች ። ሕንፃ ያለ መሠረት ሊቆምና ሊታይ እንደማይችል ክርስቲያንም ያለ ምግባር ክርስቲያን መሆን አይችልም» ብሎአል ። (ዮሐ· አፈወርቅ ድርሳን 9)።

ሃይማኖት ተስፋ ስለምናደርገው ነገር የሚያረጋግጥ ፣ የማናየውንም ነገር የሚያስረዳ ነው ። ለአባቶች የተመሰከረላቸው በዚህ ነውና ። (ዕብ· 11፡1–2)። ሃይማኖት የማይታየውን እንደሚታይ አድርጎ ሊያረጋግጥና ሊያስረዳ የሚችለው በምግባር ሲገለጥና ሲጸና ነው ።

ቅዱስ ጳውሎስ «ሃይማኖት ፣ ተስፋ ፣ ፍቅር እነዚህ ሦስቱ ጸንተው ይኖራሉ ፣ ከእነዚህም የሚበልጠው ፍቅር ነው» በማለት ለምግባር ከፍተኛ ደረጃ ሰጥቶአል ። (1 ቆሮ· 13፡13)።

ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብም እምነትና ምግባር በክርስቲያናዊ ሕይወት ውስጥ መነጣጠል እንደሌለባቸው ሲገልጥ ሥራ የሌለው ሃይማኖት አይጠቅምም ፣ አያድንም ፣ እምነት ፍጹምና ሕያው ሊሆን የሚችለው በሥራ ነው ። ሃይማኖትና ምግባር የሌሉት ሰው ከንቱ ነው ፣ ከነፍስ የተለየ ሥጋ የሞተ እንደሆነ እንዲሁ ደግሞ ከሥራ የተለየ ሃይማኖት የሞተ ነው ካለ በኋላ የአብርሃምና የረዐብን እምነትና ምግባር ምሳሌ አድርጎ አቅርቦአል ። (ያዕ· 2፡14–26)።

በዚህ መሠረት መልካም ሥራ የሃይማኖት ውጤት ወይም ፍሬ ነው እውነተኛ ሃይማኖት ያለው ሁሉ ግድ መልካም ሥራ ይሠራል ። (1 ቆሮ· 13፡2)።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም «መልካም ፍሬ የማያፈራ ዛፍ

www.zeyeneta.com
ይቆረጣል ፡ ወደ እሳትም ይጣላል» (ማቴ· 7፡19)። ካለ በኋላ «በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ ጌታ ሆይ ፡ ጌታ ሆይ የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም» ብሎ መዳን ወይም መንግሥተ ሰማያት መግባት የሚቻለው ምግባር በሃይማኖት መሠረትነት ላይ ሲጸና ሃይማኖትም በምግባር ሲገለጥና ሲፈጸም መሆኑን ተናግሮአል ። (ማቴ· 7፡20–21 ፡ ሉቃ 3፡8)።

በፍርድ ቀን ማንም ሰው የሚጠየቀው አምኖ ስለሠራው ሥራ ነው እንጂ ምግባር ስለሌለው ሃይማኖቱ አይደለም (ማቴ· 25፡41–45)። በቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ የተነገረው ሁሉም እንደየሥራው ዋጋውን ይቀበላል የሚል ነው ። (ማቴ· 16፡27 ፡ ዮሐ· 5፡28–29 ፡ 2 ቆሮ· 5፡10 ፡ ራእ· 14፡13 ፡ 20፡12 እና 22፡12)።

በዚህ መሠረት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሃይማኖት ብቻውን እንደማይጠቅም አውቃ በሃይማኖት ላይ ምግባር መሥራት እንደሚገባ ታምናለች ታስተምራለች ።

www.zeyeneta.com

ክፍል ፪

ሥርዓተ አምልኮት

ጥንታዊ ሃይማኖታዊ ሥርዓት ከአላቸው ጥንታውያን አብያተ ክርስቲያናት መካከል አንዱዋ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ናት ። ከዚህም የተነሣ አገራችን ኢትዮጵያ «የክርስትና ደሴት» እየተባለች ትጠራለች ። ከልደተ ክርስቶስ በፊት በብሉይ ኪዳን ትመራ የነበረች ሀገረ እግዚአብሔር በመሆኗ ፣ የሳምንት በዓል የሆነውን ቀዳሚት ሰንበትን ማክበር ፣ በሳምንት ሁለት ቀናት መጾም ፣ ወንድ ልጅ በተወለደ በስምንተኛው ቀን ወደ ቤተ ግዝረት መውሰድ በአርባ ፣ በሰማንያ ቀን ዕጥለ ርግብ ዘውግ ማዕጎቅ ይዞ ሕፃናትን ወደ ቤተመቅደስ መውሰድና ወደ እግዚአብሔር በማቅረብ እንደሥርዓቱ መፈጸም የቆየ ሥርዓት ስለነበር ለሥርዓተ ቤተክርስቲያን አሠራር መነሻ ሆኗል ።

ከቀዳሚት ሰንበት ጋር እሑድን የማክበር ፣ በጾመ አስቴርና በጾመ ዮዲት ፈንታ ዓርብና ረቡዕን መጾም ፣ ሕፃናት በተወለዱ በስምንተኛው ቀን ወደ ቤተ ግዝረት ፣ በአርባ በሰማንያ ቀን ዕጥለ ርግብ ፣ ዘውግ ማዕጎቅ ይዞ ወደ ቤተመቅደስ በመሄድ ፈንታ ወንድ ልጅ በተወለደ በአርባኛው ቀን ፣ ሴት ልጅ በተወለደች በሰማንያኛ ቀን ወደ ቤተክርስቲያን ወስዶ የማስጠመቅን ሥርዓት ቤተክርስቲያናችን ወስና እየሠራችበት ትገኛለች።

እግዚአብሔር ለአብርሃም «በእኔና በአንተ መካከል ፣ ከአንተም በኋላ በዘርህ መካከል የምትጠብቁት ቃል ኪዳኔ ይህ ነው ከእናንተ ወንድ ሁሉ ይገረዝ በእኔና በእናንተ መካከል ያለው ቃል ኪዳን ምልክቱ ይህ ይሆናል» ዘፍ· 17፡9—11 ፣ ሮሜ·4·/9 ብሎ ጌታ ለአብርሃም በነገረው መሠረት ግዝረት ለአብርሃም የቃል ኪዳን ምልክት ሆኖ በመሰጠቱ በስምንተኛው ቀን ያልተገረዘ ሁሉ ከአብርሃም ቤተሰብነት አይቆጠርም ፣ ምድረ ርስትን አይወርስም ፣ ከተስፋውም አይካፈልም ፣ የእግዚአብሔር ወገን አይባልም ነበር ። (ዘፍ·17፡7)።

በሐዲስ ኪዳን ግን በግዝረት ፈንታ ጥምቀት ተተክቶአል ፣ ያልተጠመቀ ሁሉ የእግዚአብሔር ልጅ አይባልም መንግሥተ ሰማያትን አይወርስም ። (ዮሐ· 3፡5 ቆላ· 2፡11)።

www.zeyeneta.com

ይህም ተያይዞ የመጣው ሥርዓት አምልኮተ እግዚአብሔርንና ምግባረ ወንጌልን ለመጠበቅና ለማስጠበቅ የተሠራ ነው ።

ሥርዓተ አምልኮትን ተከትሎ የሚጸለየው ፣ የሚጾመው ፣ የሚከበረው በዓል በትምህርት ብቻ የሚወረስ ሳይሆን ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲወርድ ሲወራረስ የመጣ የተቀደሰ ሥርዓተ ትውፊትም ነው ።

ምዕራፍ ፲፪

ሥርዓተ ጾም

ጾም ሰውነት ከሚፈልጋቸው ነገሮች ሁሉ መከልከልና የጾም ጊዜ እስኪፈጸም ድረስ ከጥሉላት ፣ በዚህም በጾሙ ጊዜ ለተወሰነ ሰዓት ከማንኛውም ምግብ ተከልክሎ መጾም ነው ። (ፍትሕ መንፈሳዊ አንቀጽ 15 ፣ ማቴ· 6፡16)። በጠቅላላም ለሰውነት የሚያምረውን የሚያስጐመጀውን ነገር ሁሉ መተው ነው ።

የጾም ዋና ዓላማም ፈቃደ ሥጋ ለፈቃደ ነፍስ እንዲገዛ ለማድረግና በደልን ለማስተሥረይ የነፍስ ዋጋን ለማብዛት ነው ።

ጾም ከሃይማኖት ጋራ ግንኙነት ስላለው የአፈጻጸሙ ሥርዓት ይለያይ እንጂ ሃይማኖት ላለው ሁሉ ጾም አለው ። ይልቁንም በብሉይ ኪዳን ጾም ከፍተኛ ቦታ ነበረው ። የብሉይ ኪዳን ነቢያት ከእግዚአብሔር ጋር በሚገናኙበት ወራት እህል ውሃ ባፋቸው አይገባም ነበር ። (ዘፀ· 34፡28)።

በነቢያት ብዛት የታዘዘው የእግዚአብሔር መዓት የሚመለሰው ሕዝቡ በጾም ሲለምኑትና ሲማልዱት ነበር ። (ዮናስ 3፡7–10 ፣ ኢዩ·2፡12–18)።

በሐዲስ ኪዳንም ጾም ሰው ሠራሽ ሕግ ሳይሆን ራሱ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ሥጋዌ የሥራ መጀመሪያ አድርጎ የሠራው ሕግ ነው ። (ማቴ· 4፡2 ፣ ሉቃ· 4፡2)።

ጾም ርኩሳን መናፍስትን የማራቅ ኃይል እንዳለው መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አስተምሮአል (ማቴ· 17፡21 ፣ ማር· 9፡2)።

በተክርስቲያንን እንዲያገለግሉ የታዘዙ ሐዋርያትም ከመንፈስ

www.zeyeneta.com

ቅዱስ በየጊዜው ትእዛዝ የሚቀበሉት በጾምና በጸሎት ላይ እንዳሉ ነበር ። (የሐዋ·ሥራ 13፡2)።

ለስብከት ወንጌል የሚያገለግሉ ዲያቆናትና ቀሳውስት የሚሾሙትም በጾምና በጸሎት ነው ። (የሐዋ· ሥራ 13፡3 ፡14፡23)።

ደጋግ ሰዎች ሁሉ የፈለጉትን ያዩና ያገኙ በጾምና በጸሎት ፈጣሪያቸውን ማልደው ነው ። (ዕዝራ 8፡21 ፡ ነህምያ 9፡1–3፡ አስቴር 4፡16–17፡ የሐዋ· ሥራ 10፡30 ፡ 13፡2–3)።

የጾም ሃይማኖታዊ ትርጉም ፈጣሪን መለመኛ የንጢአት ማስተሥረያ ስለሆነ በጾም ወራት ላምሮት ለቅንጦት የሚበሉ ወይም ለመን ፈሳዊ ንኡል ተቃራኒ የሆነ ሥጋዊ ፍትወትን ከሚያበረታቱ ከአልኮል መጠጥ ከሥጋና ከቅቤ ከወተትና ከእንቁላል መከልከል ይገባል ። (ዳን 10፡ 2–3)።

ጾም በትምህርተ ሐዋርያትና በሊቃውንትም ዘንድ ሲሰበክ ኖሯል። (ፍትሕ·መን·አን· 15 ፡ ዲድስቅልያ አን· 29)።

ነዳያንን ለመመገብ የሚጾም ንዑድ ክቡር ነው· እንደተባለ ጠመኛው ለምሳው ወይም ለራቱ ያሰበውን ወጭ ነዳያንን እንዲረዳበት ለድኩማን ድርጅት· ወይም በቤተክርስቲያን አካባቢ ለሚገኙ ነዳያን መስጠት· ጾሙን የበለጠ ፍጹም ያደርገዋል ። (ኢሳ· 58፡ 6–11)።

ጾም ከመባልዕት መከልከል ብቻ ሳይሆን ዐይን ክፉ ከማየት አንደበት ክፉ ከመናገር ጆሮ ክፉ ከመስማት የተቆጠበ እንደሆነ ጾሙን እውነተኛ ጾም ያደርገዋል ። (ማቴ· 5፡21–30)። (ያሬድ ጾመ ድጓ)

የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የራስዋ የሆኑ የጾም ሕግና ሥርዓት አላት ፡

በሕጉም መሠረት ሰባት አጽዋማት አሉአት ፡

1ኛ· ዐቢይ ጾም

2ኛ· ረቡዕና ዓርብ

3ኛ· ነነዌ

4ኛ· ገሃድ

5ኛ· ጾመ ነቢያት

6ኛ· ጾመ ሐዋርያት

7ኛ· ጾመ ፍልሰታ ለማርያም

www.zeyeneta.com

ሀ) ዐቢይ ጾም

ዐቢይ ጾም፡ ክብር ምስጋና ይግባውና ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከተጠመቀ በኋላ የጾመው የዓርባ ቀናት ጾም ነው። ማቴ· 4፡1 ቤተ ክርስቲያንም ጌታ ያደረገውን ምሳሌ ተከትላ ትጾ ማለች ።

ዐቢይ ጾም ስምንት ሳምንታት ወይም 55 ቀኖች አሉት ።

የመጀመሪያው ሳምንት ጾመ ሕርቃል ይባላል ። ሕርቃል (ኢራቅ ሊዮስ) የቢዛንታይን ንጉሥ ነበር ፡ (614 ዓ·ም)። ይህ ሳምንት በስሙ የተጠራበትም ምክንያት እንደሚከተለው ነው ። በዘመኑ ፋርሶች ኢየሩሳሌምን ወርረው የጌታን መስቀል ማርከው ወስደው ነበር ። እሱ ወደ ፋርስ ዘምቶ እነርሱን ድል አድርጎ መስቀሉን ይዞ ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሷል ። በዚህ ምክንያት ክርስቲያኖች ተደስተው ለስሙ መታሰቢያ ይሆን የጾም ሳምንት በቀኖና ውስጥ አስገብተው ለታል ቤተ ክርስቲያናችንም በቀኖናዋ አስገብታ ተቀብላዋለች ከዐቢይ ጾምም ጋር አንድ ሁኖ ተቆጥሮአል ። (ፍት·ነገ·15)።

የመጨረሻው ሳምንት ሰሙነ ሕማማት ነው ፡ ሐዋርያት የጌታችንን ነገረ መስቀል እያሰቡ የጾሙት ነው ። ያም ሆነ ይህ ሁሉም ከዐቢይ ጾም ጋር አንድ ሆነው ተቆጥረዋል ።

ዐቢይ ጾም መባሉ

1ኛ· የጌታ ጾም ስለሆነ ፡

2ኛ· የሰይጣን ፈተናዎች (አርእስተ ነጣውእ) ድል የተነሱበትና የሚነሱበት በመሆኑ ነው ፡

የቤተ ክርስቲያናችንን መዝሙር ንዛቤን ከዘመው አስማምቶና አጠናቅሮ የተናገረው አትዮጵያዊው ሊቅ ቅዱስ ያሬድ በጾመ ድጓው በዓቢይ ጾም ለሚገኙት እሑዶች ሁሉ የተለየ መዝሙር ስለሠራላቸው እያንዳንዱ እሑድ በመዝሙሩ ስም ይጠራል ።

የመጀመሪያው እሑድ ዘወረደ ይባላል

በመጽሐፉ መጀመሪያ አምላክ ከሰማይ መውረዱን ሰው መሆኑንና መሰቀሉን ስለሚያወሳ ነው ። (ዮሐ· 3፡13)።

www.zeyeneta.com

ሁለተኛው እሑድ ቅድስት ይባላል

በተለይ ስለ ዕለተ ሰንበት ቅድስና ስለሚያወሳ ነው ።

ሦስተኛው እሑድ ምኩራብ ነው

ጌታ በመዋዕለ ትምህርቱ በሰንበት በምኩራብ ገብቶ ማስተማሩን ስለሚያወሳ ነው ።

አራተኛው እሑድ መጻጉዕ ነው

ድውያንን መፈወሱን ዕውራንን ማብራቱን የሚያነሣ መዝሙር ይዘመርበታል ። (ዮሐ. 5፡1-9)።

አምስተኛው እሑድ ደብረ ዘይት ይባላል

በደብረ ዘይት ተራራ ላይ ሁኖ ያስተማረውን የዳግም ምጽአት ነገር የሚያስታውስ መዝሙር ይዘመራል ።

ስድስተኛው እሑድ ገብር ኄር ነው

የጌታውን ብር ተቀብሎ ያተረፈው ፡ በጌታውም ፊት ምስጋናን ያገኘው ሰው ታሪክ ይነገርበታል ፡ ይዘመርበታል ።

ሰባተኛው እሑድ ኒቆዲሞስ ነው

በሌሊት ወደጌታ እየመጣ ይማር የነበረውን የኒቆዲሞስን ታሪክ የሚያስታውስ መዝሙር ይዘመርበታል ።

ስምንተኛው እሑድ ሆሣዕና ነው

ጌታ ሆሣዕና በአርያም እየተባለ ወደቤተ መቅደስ የገባበት ዕለት መታሰቢያ ነው ። ከሠርክ ሆሣዕና እስከ ትንሣኤ ያለው ሰባት ቀን «ሰሙነ ሕማማት» ይባላል ። በነዚህ ቀናት ብዙ አገልግሎት አይበሉም ። ስግደት ይሰገዳል ። የጌታን መከራና ሞት የሚያስታውሱ ምንባባት ከቅዱሳት መጻሕፍትና ከድርሳናት ተውጣጥተው በግብረ ሕማማት ይነበባሉ ። አዳም ከፈጣሪው ተጣልቶ የኖረውን

www.zeyeneta.com

የፊሕለማና የመከራ ዘመን በማስታወስ መንበረ ታቦቱ በጥቁር ልብስ ይሸፈናል ። ልብሰ ተክህኖውም ጥቋቁር ነው ። ይህ ሳምንት የ5500 ዘመን ዓመተ ፍዳና ዓመተ ኩነኔ መታሰቢያ ስለሆነ በዚህ ሳምንት ጸሎተ ፍትሐትና ጸሎተ አስተሥርዮ አይፈጸምም ። ጸሎተ ፍትሐትና ጸሎተ አስተሥርዮ የሚያረገው የሠዓዳና ዕለት ነው ።

ጸሎተ ሐሙስ፡—

ጸሎተ ሐሙስ ጌታ በፍጹም ትሕትና የደቀ መዛሙርቱን እግር ያጠበበትና ግብር ያገባበት ፡ ምሥጢረ ቁርባንን ያሳየበት ዕለት ነው። በዚህ ዕለት ቅዳሴ ይቀደሳል ። ከቅዳሴውም ቀደም ብሎ ካህኑ ውነውን በብርት አድርጎ ጸሎተ አኰቴት አድርሶ በጌታ አምሳል የምእመናንን እግር ያጥባል ጸሎተ ቅዳሴውም ከተፈጸመ በኋላ ምእመናኑ ወደየቤታቸው ይሄዳሉ ።

ከጸሎተ ሐሙስ በበኑጋው ወርብ የስቅለቱ መታሰቢያ ዕለት ሥዕለ ስቅለት ተሠርቶ ለስቅለቱ ነክ የሆኑ ምንባባት ሲነበቡ ይዋላል ። ሠርክ ሲሆን እያንዳንዱ ምእመን ወደ ቂሱ እየቀረበ በወይራ ቅጠል ይጠበጠባል። ቂሱም በወይራ ቅጠል እየጠበጠበ ተዉሕማሪ ስግደት ይሰጠዋል ። ይህም በወይራ ቅጠል መጠብጠብ የጌታ ግርፋት ምሳሌ ነው ። ቀጥሎም አረጋ መቶ እግዚአብ ይደርሳል ። ለበዓሉ የተሠሩ መዝሙራትና ምንባባት ከተደረሱ በኋላ «ንሴብሐ ለእግዚአብሔር» ተብሎ መስቀል ከማሳለም በቀር ኑዛዜ ተደርጎ እግዚአብሔር ይፍታ ይባላል ። ጸሎተ አስተሥርዮ ይደረጋል (ፍትሕ መንፈሳዊ አንቀጽ 15፡601) በአሥራ ሁለት ሰዓት ሠርሐት ሕዝብ ይሆናል ። ሐዋርያት የጌታን ትንሣኤ ሳናይ እህል ውሃ አንቀምስም ብለው እስከ ትንሣኤ አክፍለዋል ። በዚህም መሠረት በቤተ ክርስቲያናችን የሚችል ዓርብንና ቅዳሜን እንዲያ ከፍል ፡ የማይችል ሰው ግን ቅዳሜንን ብቻ እንዲያከፍል ታዟል (ለ.ቃ. 5፡33—35፡ ፍትሕ መን. አንቀጽ 15፡578)።

ቅዳሜ ጧት ምእመናኑና ካህናቱ ወደ ቤተ ክርስቲያን ይሰበ ሰባሉ። የጧት ጸሎት ሲፈጸም «ንብረ ሰላመ በመስቀሉ» ክርስቶስ በመስቀሉ ሰላምን መሠረተ ሰላምን አደረገ የምሥራች እየተባለ

www.zeyeneta.com

በቤተ ክርስቲያን ለተሰበሰበው ሁሉ ቂጣማ ተባርኮ ይሰጣል ፡ የምሥራች ምልክት ነውና ። ምእመናኑም በራሳቸው ያሥሩታል ።

ወደ ቤተ ክርስቲያን ላልመጡትም ካህናት በየሰበካቸው ልብሰ ተክህኖ ለብሰው መስቀልና ቃሬል ይዘው ቂጣማውን የምሥራች እያሉ ያድላሉ።

የፈተኛው ቀዳም እግዚአብሔር ፍጥረታትን ፈጥሮ ከሥራው ያረፈበት ዕለት እንደሆነ ይህ ደግሞ የማዳን ሥራውን በመስቀል ላይ ፈጽሞ ስኩብ በመቃብር ሆኖ የዋለበትና ያደረበት ዕለት ነው ። ይህ ዕለት «ስዑር ቀዳም» ይባላል ። ስዑር መባሉም ባመት አንድ ቀን ስለሚጾም ነው ። «ለምለም ቀዳምም» ይባላል ። በዚህ ቀን ቂጣማ ይታደላልና ቂጣማውም የምሥራች ምልክት መሆኑ ከታሪክ ጋር የተያያዘ ነው።

ቅዱስ መጽሐፍ እንደሚነግረን ዓለም በማየ አይኅ በተጥለቀለቀ ጊዜ የኖኅ መርከብ ማረፊያ አጥታ ስትንሳፈፍ የውሃውን ሁኔታ ለመረዳት ኖኅ ርግብን በመርከቡ መስኮት አሾልኮ ላካት ። እሷም የወይራ ቅጠል ባፏ ይዛለት ተመልሳለች ። ኖኅ በዚህ የወይራ ቅጠል የውኃውን መድረቅ ተረድቶ ተደሰተ ። መርከቡንም ለማሳረፍ ተዘጋጀ ። «የወይራው ቅጠል» ለጥፋት ውሃ መድረቅ የምሥራች መንገሪያ እንደሆነ ሁሉ አሁንም በክርስቶስ ሞት «ማየ ሥራዌ ፡ ማየ ድምሳሴ ፡ ኃጢአት ፡ ሞተ ነፍስ ከሰው ልጆች ተወገደ» የምሥራች ፡ እያለች ቤተ ክርስቲያን ለምእመናን ቂጣማ ትድላለች ። (1 ጴጥ· 3፡19—21)።

ለ) ከፀቢይ ጾም ቀጥሎ ሁለተኛው ጾም የረቡዕና የዓርብ ጾም ነው

ረቡዕና ዓርብ ከትንሣኤ ጀምሮ እስከ ጰራቅሊጦስ እሑድ ድረስ ከሚገኙና እንዲሁም ልደትና ጥምቀት ከሚውሉባቸው ረቡዕና ዓርብ በቀር ዓመት እስከ ዓመት ይጾማሉ ። የሚጾሙበትም ምክንያት አላቸው ።

www.zeyeneta.com

ረቡዕ፡–

ረቡዕ የአይሁድ ሸንጎ ጌታን ዓርብ ዕለት ለመስቀል ምክረ ሞቱን የፈጸመበት ዕለት ነው ። (ዮሐ· 11፡46–53) ። መድኃኔዓለም ክርስቶስ ለሰው ልጆች ሲል የተወሰነበትን የሞት ውሳኔ ሁልጊዜ በማስታወስ ክርስቲያኖች በዚህ ዕለት እንዲጾሙ ታዟል ።

ዓርብ፡–

ዓርብ እንደሚታወቀው ጌታ የተሰቀለበት በሥጋ የሞተበት ብዙ ዘመን ሲጠበቅ የነበረው ተስፋ የተፈጸመበት ቅዱስ ዕለት ነው። (ዮሐ· 19፡17–30 ፣ ሉቃ· 23፡26–49)። ስለሆነም ልደትና ጥምቀት ከሚውሉባቸው እንዲሁም በበዓለ ሃምሳ ውስጥ ከአሉት ረቡዕና ዓርብ በቀር በየሳምንቱ በጾምና በጸሎት እንዲከበሩ በቤተ ክርስቲያናችን ታዟል ፣ (ፍት·መን·አን· 15 ፣ ዲድስቅ 29)።

ሐ) ሦስተኛው ጾም የነነዌ ጾም ነው

ይህ ጾም የሦስት ቀን ጾም ነው ። ሰኞ ፣ ማክሰኞ ፣ ረቡዕ ። ይህ ጾም «በመባጃ ሐመር» «በኢየዓርግና ኢይወርድ» ስለሚመላለስ ቁጥሩ ከአጽዋማት አዋድያት ነው ። አንድ ጊዜ በጥር አንድ ጊዜም በየካቲት ይሆናል ። የቤተ ክርስቲያን አባቶች ይህን ጾም የወሰኑት የነነዌ ሰዎች በጾምና በጸሎት ከመዓትና ከጥፋት እንደ ዳኑ (ዮናስ 3፡5–9 ፣ ማቴ· 12፡39)። ምእመናንም በጾምና በጸሎት ከፈጣሪያቸው ምሕረትንና በረከትን እንዲያገኙ በማለት ነው ።

መ) አራተኛው ጾመ ገሃድ ነው

ይህ ጾም በልደትና በጥምቀት ዋዜማ የሚጾም ነው ። ልደትና ጥምቀት ረቡዕና ዓርብ ሲውሉ በሌሊት ስለሚቀደስና ስለሚበላ በለውጡ በዋዜማው ሐሙስና ማክሰኞ ይጾማል ፣ (ፍት·መን·አን· 15)። ይህም ጾም በያመቱ እንዲጾም በቀኖና ቤተ ክርስቲያን ተወስኗል ።

www.zeyeneta.com

ሠ) አምስተኛው ጾም ጾመ ነቢያት ይባላል

የጾሙ ጊዜ ከሕዳር 15 እስከ ታኅሣሥ 28 ቀን ያለው ነው ። ይህን ጾም የምንጾመው ነቢያት በየዘመናቸው ስለክርስቶስ መምጣት በናፍቆት ይጾሙና ፣ ይጸልዩ ስለነበር የእነርሱን አርአያ ተከትለን የክርስቶስን ልደት ከማክበራችን ቀደም ብለን ይህን ጾም እንድ ንጾም በሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ተሠርቷል ። (ፍት·መ ን·አን·15)።

ረ) ስድስተኛው ጾም ጾመ ሐዋርያት ነው

የሰኔ ጾምም ይባላል ።

ሐዋርያት መንፈስ ቅዱስን ከተቀበሉ በኋላ ለስብከተ ወንጌል ከመሔዳቸው በፊት የጾሙት ነው ። ምእመናንም እነርሱን ምሳሌ አድርገው ከጸራቅሊጦስ እሑድ ማግስት ጀምረው እንዲጾሙ ቤተ ክርስቲያናችን ታዛለች ። ይህ ጾም «በኢየዐርግና ኢይወርድ» ስለሚመላለስ የተወሰነ ቀን የለውም ፣ አንዳንድ ጊዜ ከአርባ ቀን ይበልጣል ፣ አንዳንድ ጊዜም ከሠላሳ ቀን ያንሳል ።

ሰ) ሰባተኛው ጾም ጾመ ፍልሰታ ለማርያም ነው

የፍልሰታ ጾም ከነሐሴ 1 እስከ 15 ቀን ያለው ነው ። እመቤታችን ያረፈችው በጥር 21 ቀን 50 ዓ·ም ነው ። ሐዋርያት ሊቀብሩ ወደጌቴ ሴማኒ ይዘዋት ሲሔዱ አይሁድ በታተኗቸው ። በዚህ ጊዜ መላእክት የእመቤታችንን ሥጋዋን ወስደው በገነት ከዕፀ ሕይወት ሥር አኑረውታል ። (ተአምረ ማርያም ፣ ስንክሳር ነሐሴ 16 ቀን)።

ዮሐንስ በተመስጦ እየሄደ ሥጋዋን ያጥን ነበር ። ለሐዋርያት ይህን ይነግራቸዋል ። ለዮሐንስ ተገልጣ ለእኛ ሳትገለጥ ብለው በነሐሴ ሱባዔ ገቡ ። ሁለተኛው ሱባዔ ሲፈጸም በ14ኛው ቀን መልአክ ሥጋዋን አምጥቶ ሰጥቶአቸው ቀብረዋታል ። በሦስተኛው ቀን ነሐሴ 16 ቀን ተነሥታ አርጋለች ። (ተአምረ ማርያም ፣ ስንክሳር ነሐሴ 16 ቀን) ።

ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን የእመቤታችንን

www.zeyeneta.com

በረከት ለማግኘት ትጾማለች ። በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ይህን ጾም ሕፃናቱ ሳይቀሩ ይጾሙታል ።

በዚህ የአሥራ አምስት ቀን ገዜ ውስጥ የማይጾምና የማይቆርብ ሕፃን የለም ። ብዙ ሰዎች ቤታቸውን እየተዉ ሱባዔ እየገቡ ከላመ ከጣመ ምግብ በመከልከል ጥሬ እየቆረጠሙ ፣ ውሃ እየጠጡ ፣ በጾምና በጸሎት ይሰነብታሉ ።

በፍልሰታ ጾም ጊዜ በጠቅላላ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ያለው ሁኔታ ሕዝቡ ልጅ አዋቂ ሳይል የሚያሳየው ሃይማኖታዊ ሥርዓት ኢትዮጵያ ለእመቤታችን የቃል ኪዳን አገር መሆኗን ይመሰክራል ።

እነዚህን አጽዋማት ከሰባት ዓመት በላይ ያለ ሁሉ እንዲጾማቸው ተወስኗል ። ቅዳሴ የሚቀደሰውም ከእሑድና ከቅዳሜ በቀር በጾም ወራት ውሎ ነው ።

ምዕራፍ ፲፫

ሥርዓተ ጸሎት

ጸሎት ሰው በሃይማኖት ፈጣሪውን እያመሰገነና ሥርየተ ኃጢአትን እየለመነ ከፈጣሪው ጋር የሚነጋገርበት ቃል ነው ። (ፍትሕ መንፈሳዊ አንቀጽ 14፡528) ።

የጸሎት መሠረቱ ፣ «ሹ ታገኛላችሁ ፣ ለምኑ ይሰጣችኋል ፣ ደጅ ምቱ ይከፈትላችኋል» የሚለው አምላካዊ ቃል ነው ፣ (ማቴ፡7፡7) ።

ለጸሎቱ አፈጻጸም የተለየ ጊዜና ቦታ አለው ። በዚህም መሠረት ፦ ካህናትና ምእመናን ለጸሎት ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚሔዱባቸው ጊዜያት ጥዋትና ማታ ናቸው ።

የጸሎት ጊዜያት

የጸሎት ጊዜያት ሰባት ናቸው (መዝ· 118፡164)

እነርሱም፦

ሀ) ነግህ

ለ) ሠለስት

www.zeyeneta.com

ሐ) ቀትር
መ) ተስዓት (ዘጠኝ ሰዓት)
ሠ) ሠርክ
ረ) ሰዓተ ንዋም (የምሽቱ ሰዓት)
ሰ) መንፈቀ ሌሊት (ዕኩለ ሌሊት) ናቸው ።

ከ7ቱ ጊዜያት ካህናትና ምእመናን ወደ ቤተ ክርስቲያን ሔደው የሚጸልዩባቸው ነግህና ሠርክ ናቸው ። በቀሩት ጊዜያት ግን በያሉበት ሊጸልዩ ይገባል (ዳት·መን·አን·14 ረስጣ 48 ፡ 47 ድስቅ 12) ።

ጸሎት በ3 ይከፈላል ።

= የግል ጸሎት
= የቤተሰብ ጸሎት
= የማኅበር ጸሎት

ሀ) የግል ጸሎት

የግል ጸሎት የሚጸለየው በቤትና በአመቺ ቦታ ነው ። የግል ጸሎት ማንም ሳያየውና ሳይሰማው አንድ ሰው በግሉ የጸሎት ቤቱን ዘግቶ በስቲለ ጎሊና ሆኖ ፈጣሪው ብቻ እንዲያየው እንዲሰማው አድርጎ በኅቡዕ የሚጸልየው ጸሎት ነው፡ (ማቴ· 6·5—13) ።

ለ) የቤተሰብ ጸሎት

የቤተሰብ ጸሎት ቃሉ እንደሚያመለክተው አንድ ቤተሰብእ በአንድነት ሁኖ የሚያደርገው ጸሎት ነው ። ለዚህም የመቶ አለቃው የቆርኔሌዎስ ጸሎት ምሳሌ ይሆናል ። (የሐዋ· ሥራ· 10፡2 6) ።

ሐ) የማኅበር (የቤተክርስቲያን) ጸሎት

የማኅበር ጸሎት የሚባለው ካህናትና ምእመናን ወንዶችና ሴቶች ሽማግሌዎችና ወጣቶች በአንድነት ሆነው በቤተ ክርስቲያንና አመቺ በሆኑ ቦታዎች ሁሉ ተሰብስበው የሚጸልዩት ጸሎት ነው ።

www.zeyeneta.com

በብሉይ ኪዳን የነበሩ አማንያን ወደ ቤተ እግዚአብሔር እየሔዱ ይጸልዩ ነበር ። (1ኛ· ሳሙ· 1·9 13፡ መዝ· 121·1 ፡ ሉቃ 18፡10 14) ።

በሐዲስ ኪዳንም ሐዋርያትና የሐዋርያት ተከታዮች የሆኑት ክርስቲያኖች የቤተ ክርስቲያን መነሻዎች በሆኑት በጽርሐ ጽዮን በማርቆስ እናት በማርያም ቤት እንዲሁም በመጀመሪያዋ በአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን እየተሰበሰቡ ይጸልዩ ነበር (የሐ·ሥ· 1 ፡ 14 ፡ 25። 3 ፡ 1 ፡ 12፡12 ፡ 13፡ 1 3) ።

በዚሁ መሠረት በሰንበትና በበዓላት ቀናት ሁሉ ካህናትና ምእመናን በቤተ ክርስቲያን እየተገኙ በሰዓታት በማሕሌትና በጸሎተ ቅዳሴ እንዲያመሰግኑ ቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓት አላት ።

ሰዓታት በገዳማትና በአድባራት ከዓመት እስከ ዓመት ፡ በገጠር አብያተ ክርስቲያናት በእሑድ ፡ በበዓላትና በጸሎተ ፍትሐት ጊዜ ሌሊት በቤተ ክርስቲያን የሚጸለይ የካህናት የጉባረት ጸሎት ነው ። የመዓልት ሰዓታትም አለ (በአጽዋማት ጊዜ በቀን በየሰዓቱ የሚጸለይ (አባ ጊዮርጊስ ሰዓታት ።)

ማሕሌት በዝማሚ በመቋሚያ (ዘንግ) በጸናጽልና በከበሮ የሚዘመር የካህናት የጉባረት መዝሙር ነው ። የዐቢይ ጾም ማሕሌት ያለ ጸናጽልና ከበሮ በመቋሚያ ብቻ እየተዘመመ ይዘመራል ።

በካህናት መሪነት በምእመናን ተሳታፊነት (ተሠጥዎ ተቀባይነት) የሚፈጸሙ ፡

ጸሎተ ቡራኬ ቤተ ክርስቲያን
ጸሎተ ጥምቀተ ክርስትና
ጸሎተ ሚሙተ ክህነት
ጸሎተ ተክሊል
ጸሎተ ኖላ
ጸሎተ ፍትሐት
ጸሎተ ቅዳሴና የመሳሰሉት ናቸው ።

www.zeyeneta.com

ጸሎተ ቅዳሴ

ጸሎተ ቅዳሴ ሦስት ዋና ዋና ክፍሎች አሉት ።

እነርሱም፡-

1ኛ· «አ እንየ ሀለ· በዝንቱ ልቡና» ከሚለው አንስቶ «ሚመጠን ግርምት» እስከሚለው የዝግጅት ክፍል ፡

2ኛ· «ሚመጠን ግርምት» ከሚለው አንስቶ «ዓአ· ንዑሰ ክርስ ቲያን» እስከሚለው የትምህርት ክፍል ፡

3ኛ· «ዓአ» ከተባለ በኋላ ያለው ፍሬ ቅዳሴ ነው ፡ የዚህም አፈጻጸም ሥርዓት በሥርዓተ ቅዳሴውና በፍትሕ መንፈሳዊ አንቀጽ 12 በዝርዝር የተመለከተው ነው ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥጋውንና ደሙን የምታከብርባቸው አሥራ አራት ቅዳሴያት አሏት ።

እነርሱም፡

1· ቅዳሴ ሐዋርያት
2· » እግዚእ
3· » ዮሐንስ ወልደ ነጐድጓድ
4· » ማርያም
5· » ሠለስቱ ምእት
6· » አትናቴዎስ
7· » ባስልዮስ
8· » ጎርጎርዮስ እኁሁ ለባስልዮስ
9· » ኤጲፋንዮስ
10· » ዮሐንስ አፈ ወርቅ
11· » ቄርሎስ
12· » ያዕቆብ ዘሥሩግ
13· » ዲዮስቆሮስ
14· » ካልእ ጎርጎርዮስ ናቸው ።

www.zeyeneta.com

የግልም ሆነ የማኅበር ጸሎት አፈጻጸም

በጸሎት ጊዜ ፡

ሀ) ዓምድና ግድግዳ ሳይደገፉ መቋሚያ ሳይዙ በሁለት እግር ቀጥ ብሎ መቆም ነው ። (መዝ፡5፡3)።

ለ) ወገብን መታጠቅ ፡ ልብስን ዝቅ አድርጎ ማደግደግ ነው (ሉቃ· 12፡35 ። ዳን·መን አንቀጽ 14) ።

ሐ) በጸሎት ጊዜ ፊትን ወደ ምሥራቅ መልሶ መቆም ወዲያና ወዲህ ወደ ግራ ወደ ቀኝ ፡ ወደ ሌላም አለማለት ፡ በሰፈሐ እድ ፡ በሰቂለ ሕሊና ፡ ሁኖ መጸለይ ይገባል (መዝ·133፡2፡ ዮሐ· 11፡41) ።

መ) ጸሎት ሲጀመርና ሲፈጸም አመልካች ጣትን ከሌሎች ጣቶች ጋር አመሳቅሎ በትእምርተ መስቀል አምሳል በጣት ማማተብ ነው ፡ ሲያማትቡም ከላይ ወደ ታች ከግራ ወደ ቀኝ በማድረግ ነው ። በማማተብ ጊዜ የክርስቶስን መከራ መስቀል ማሰብ ያስፈልጋል ። (ሉቃ· 11፡20) ።

ሠ) የሚጸልይ ሰው በትሕትናና በጸጥታ ሁኖ ለሌላ ሰው እንዳይሰማ ለራሱ ጆሮ ብቻ እንዲሰማ አድርጎ ኃጢአቱን እያሰበ መጸለይ ይገባዋል ይህንም የሚያደርገው ስለአለፈው ኃጢአቱና በደሉ ነው ፡ (1 ሳሙ· 1፡3) ።

ረ) የሚጸልይ ሰው በጥቡዕ ልብ በጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር ይነጋገራል ፡ አሳቡን በእግዚአብሔር ላይ ይጥላል ፡ የዓለምን አሳብ ሁሉ ይተዋል ።

ሰ) የሚጸልይ ሰው ሲያማትብ "በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አዐትብ ገጸየ ወኑለንያየ በትእምርተ መስቀል" እያለ ነው ። ሁለተኛም «እግዚኦ መሐረነ እግዚኦ መሐከነ እግዚኦ ተማሃለነ ወባርከነ አሜን» እያለ ያማትባል ።

ሦስተኛም «ስብሐት ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ይእዜኒ ወዘልፊኒ ወለዓለመ ዓለም አሜን ፡እግዚኦ ረስየነ ድልዋነ ከመንበል በአኩቴት አቡነ ዘበሰማያት» የሚለውን ጸሎት 3 ጊዜ እየደገመና እየሰገደ በማማተብ በጸሎት መጀመሪያና መጨረሻ ጊዜ ማድረግ

www.zeyeneta.com

አለበት ። እንዲሁም መስቀልን ከሚያነሣ ቃል ሲያርስ ማማተብ ፡ ስግደትንም ከሚያነሣ ቃል ላይ ሲደረስ መስገድ ይገባዋል ።

ሥ) የጸሎቱ ቅደም ተከተል መጀመሪያ አቡነ ዘበሰማያት ፡ ሁለተኛ መዝሙረ ዳዊት ፡ ውዳሴ ማርያምና ሌሎችም ፡ ቀጥሎ አቡነ ዘበሰማያት ጸሎተ እግዚእትነ ማርያም ፡ ጸሎተ ሃይማኖት በመጨረሻም አቡነ ዘበሰማያት ፡ ኪርያላይሶን 41 ጊዜ ይባላል ። ክርስቲያን ሁሉ መጸለይ አለበት ። የማያውቅ ምእመን ተምሮ መጸለይ ግዴታው ነው ካህናት ግን ሁሉንም እንዲጸልዩ ታዝዘዋል ። (ኤፌ· 5፡19-20 ፡ ማቴ· 7፡7 8) ።

በ) ሲጸልይ ማዘን ማልቀስ ይገባዋል ፡ ሲያለቅስም በደሉንና ኃጢአቱን እያሰበ ለየአንዳንዱ በደል ዕንባን ማፍሰስ ነው ።

ተ) የሚጸልይ ሰው በጸሎት ላይ ሳለ ጸሎቱን አቋርጦ ከማንም ሰው ጋር ፈጽሞ መነጋገር የለበትም ፡ ጸሎቱን ለማቋረጥ ችግር ቢገጥመው ግን በአቡነ ዘበሰማያት አሥሮ ንግግሩን ሲፈጽም ከአቋረጠበት ተነሥቶ ጸሎቱን ሊጸልይ ይገባል ።

ጸሎተ ምህላ

ይህ ጸሎት በአገር ላይ አባር ችነፈር ፡ መርዝነት ሲነግና ለማጎበረ ሰብእ አስጊ የሆነ መቅሠፍት በተከሠተ ጊዜ እግዚአብሔር መዓቱን በምሕረት ፡ ቁጣውን በትዕግሥት እንዲመልስ የምሕረትና የይቅርታ መለመኛ ነው ። (ዘኁ· 16 ፡ 46-50 ፡ ትንቢተ ዮናስ 3 ፡ 5-10 ፡ ኢዩ· 2 ፡ 12-19 ፡ 1 ነገ 8 ፡ 22-53) ።

በመሆኑም የተለየ ችግር ባጋጠመ ጊዜ ምእመናን ሁሉ በየሰበካ ቤተ ክርስቲያናቸው በጥዋትና በማታ እየተገኙ በጾምና በጸሎት ፈጣሪያቸውን እንዲለምኑ ቤተ ክርስቲያን ታዛለች ።

ጸሎተ ፍትሐት

ቤተ ክርስቲያን ለሙታን ጸሎተ ፍትሐት እንዲደረግ ታዝዛለች ። ፍትሐት ከዚህ ዓለም በሞተ ሥጋ የሚለዩት ሰዎች ከማዕሠረ ኃጢአት እንዲፈቱ ወደ እግዚአብሔር የሚቀርብ ጸሎት ነው ።

www.zeyeneta.com

ጸሎተ ፍትሐት ሥርየተ ኃጢአትን ፡ ይቅርታን ፡ ዕረፍተ ነፍስን ያሰጣል ። ለደጋንቹም በክብር ላይ ክብርን ተድላ ዕረፍትን ይፈጥራል ።

ሙታንና ሕያዋን የሚገናኙት በጸሎት አማካይነት ነው ። «ሕያዋን ለሙታን ይጸልያሉ ፡ ሙታንም ለሕያዋን ይለምናሉ ።» (ሄኖክ 12 ፡ 34) በነፍስ ሕያዋን ናቸውና፡ (ማቴ· 22፡31 32 ፡ ሉቃ· 20፡ 37 39 ። ባሮክ 3፡4) ።

ለሙታን ጸሎተ ፍትሐት እንዲደረግላቸው ፡ መሥዋዕት እንዲሠዋ ላቸው ፡ በቤተ ክርስቲያንና በመካነ መቃብራቸው እንዲጸለይላቸው ፡ ቅዱሳን ሐዋርያት አዝዘዋል ።

«በክርስቶስ አምነው ስለሞቱ ወንድሞቻችሁ ክርስቲያኖችና ሰማዕታት በቤተ ክርስቲያን ያለ ሀኬት ተሰብሰቡ ፡ በቤተ ክርስቲያን መሥዋዕት ሠዉላቸው ፡ ወደ ቤተ ክርስቲያንና ወደ መቃብር ስትወስዱአቸውም መዝሙረ ዳዊት ድገሙላቸው» (ዲድስቅልያ አንቀጽ 33) ።

የቤተ ክርስቲያን የሕግና የሥርዓት መጽሐፍ ፍትሕ መንፈሳዊም በዲድስቅልያ የተጠቀሰውን ያጸናል ። (አንቀጽ 22) ።

በዚሁ መሠረት ቤተ ክርስቲያናችን ለሞቱ ሰዎች ከወለተ ነፍስ እስከ ርደተ መቃብር ከቤት እስከ ቤተ ክርስቲያን አስፈላጊውን ጸሎት ትጸልያለች ፡ መዝሙረ ስብሐት ታደርሳለች ።

ለሙታን የሚደረገው መታሰቢያም ከዕለተ ሞት እስከ ዓመት ከዚያም በላይ ሲሆን፡

1· በዕለተ ሞት
2· በሣልስት
3· በሰባት
4· በአሥራ ሁለት
5· በሠላሳኛው ቀን
6· በዓርባኛው ቀን
7· በሰማንያኛው ቀን
8· በስድስተኛው ወር (መንፈቅ)
9· በሙት ዓመት በየዓመቱ ጸሎት እንዲጸለይላቸው ፡ ዕጣን

www.zeyeneta.com

እንዲታጠንላቸው መሥዋዕት እንዲሠዋላቸውና መታሰቢያ እንዲደረግ ላቸው ፡ ምጽዋት እንዲመጸወትላቸው ቤተ ክርስቲያናችን ታዛለች፡ (ፍት· መን·አን· 22) ።

ከዚህም ሁሉ ጋር፡—

= ስለ ሕመማን
= ስለመንገደኞች
= ስለገዳመ ምሕረት
= ስለፍሬ ምድር
= ስለወንዞች ውሃ
= ስለሙታንና ስለሕያዋን
= ስለ ንዑሰ ክርስቲያን
= ስለ ቤተ ክርስቲያን አንድነት
= ስለ ሀገርና ስለ ዓለም ሰላም
= ስለ ቤተ ክርስቲያን መሪዎችና አገልጋዮች
= ስለ ሀገር መሪዎች
= ስለ ነዳያንና ምስኪናን
= ስለ ስደተኞች
= ስለ አዘኑትና ስለተከዙት
= ስለ ታሠሩት
= ስለ በደለኞች (ኃጢአተኞች)
= ስለ ሃይማኖት ጽንዓት
= ስለ ወንዶችና ስለሴቶች ምእመናን በጠቅላላ ስለዓለም ሁሉ ቤተ ክርስቲያን ትጨልያለች ። ስለዚህም በየዓይነቱ ራሱን ችሎ የሚጸልይ መጽሐፈ ጸሎት አላት፡ (መጽሐፈ ቅዳሴ ።)

www.zeyeneta.com

ምዕራፍ ፲፬

ሥርዓተ ምጽዋት

ምጽዋት ከምግባራት ሠናያት አንዱና ዋነኛው ክፍል ነው ። የምጽዋት መሠረቱ እንጀራህን ለተራበ ስጥ ፡ ድሆችን በቤትህ አሳድር ፡ የቤትህን ርኁብ ቸል አትበል ፡ የሚራሩ ብፁዓን ናቸው ፡ (ኢሳ 58፡ 6–8፡ ማቴ· 5፡7) የሚለው ነው ።

ምጽዋት በሁለት ዓይነት መንገድ ይሰጣል ።

ሀ) ቀኝህ የምታደርገውን ግራህ አትወቅ (ማቴ· 6፡1–4) ። በማለት ጌታ በአንቀጸ ብፁዓን በተናገረው መሠረት ሌላ ሁለተኛ ሰው ሳያይና ሳያውቅ የሚሰጥ ነው ።

ለ) በፍትሕ መንፈሳዊ በአንቀጽ 16 እንደታዘዘ በቤተ ክርስቲያን ማዕከልነት የሚሰጥ ነው ።

ምጽዋት ወደ ፍጹምነት የምታደርስ ናት ። (ማቴ· 19፡21–22) ።

ምጽዋት ከትሩፋት ሁሉ በላይ ናት (ሆሴዕ፡ 6፡6 ማቴ· 12፡7) ።

ምጽዋት ሐዋርያዊ ትውፊትነት አለው (1ኛ ቆሮ·16፡1–4)፡ 2ኛ ቆሮ· 9፡6–7 ፡ ገላ·6፡9–10፡ ዕብ· 13፡16) ።

ከቤተ ክርስቲያን አባቶችም ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ሰው ባለመ ለየት ለተቸገረው ሁሉ ምጽዋት መስጠት እንደሚገባ አስተምሮአል (ዮሐ·አ·ተግ·10)።

ምጽዋት ርዳታን ለሚሹ ሁሉ የሚሰጥ የገንዘብ ፡ የልብስና የቀለብ ርዳታ ሁሉ ነው ።

ከተረጂ ወገን ትርፍን ሳይሹ ወይም ይመለስልኛል ብሎ ተስፋ ሳያደርግ· ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 6፡ 1–4 በተናገረው መሠረት የሚፈጸም ነው ።

በቤተ ክርስቲያናችን የምጽዋት አፈጻጸም የራሱ የሆነ ይዘት አለው። ይኸውም ምእመናን በሚጸሙበት ወራት ችግረኞችን እንዲ ጐበኙ· (ኢሳ·58፡6–9።) እንዲሁም በየቤተ ክርስቲያኑ ሰበካ ጉባኤ የችግረኞች መረጃ ክፍል እየተቋቋመ ችግረኞች እንዲረዱ የሚያዝ ሥርዓት አላት ፡ (ቃለ ዓዋዲ) ።

ምጽዋት ኃጢአትን ያስተሠርያል (ዳን·4፡27 ሉቃ· 7፡ 47 ፡

www.zeyeneta.com
ማር·4፡24) ። ምጽዋት ብዕዕናን ያሰጣል ማቴ·5፡7 ፣ የሐዋ· ሥራ 20፡35) ።

በዚህና በመሳሰሉት ሁሉ· ምጽዋትና ርኅራኄ ማድረግ በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ከጥንት ጀምሮ የተለመደና እንደ ሥርዓቱ ሲፈጸም የኖረ አሁንም በመፈጸም ላይ ያለ መጽሐፋዊ ሥርዓት ነው ።

ምዕራፍ ፲፩

ሥርዓተ ስግደት

ስግደት ሰው አምልኮቱንና ተገዥነቱን ለመግለጥ ራሱን ዝቅ አድርጎ ግንባሩን መሬት በማስነካት ለፈጣሪው ተገዢነቱን የሚገልጽበት ተግባር ነው ። የዚህም መሠረቱ "ለጌታ ለአምላክህ ስገድ" "በቅድስናው ስፍራ ለእግዚአብሔር ስገዱ" (ዘዳግ·6፡13 ማቴ 4፡10፣ መዝ· 28፡2) የሚለው ነው ። እንዲህ ያለውም ስግደት የአምልኮት ስግደት ይባላል ። የሚቀርበውም ለአምላክ ብቻ ነው (ማቴ·4፡10) ። ለአምላክ የሚቀርብ ስግደትም በእውነት ፣ በመንፈስ መሆን ይገባዋል (ዮሐ·4፡24) ።

ስግደት በሦስት ይከፈላል ።

እርሱም ፣

ሀ) ሰጊድ

ለ) አስተብርኮ

ሐ) አድንኖ ነው ።

ሰጊድ ፣ ከመሬት ወድቆ ግንባርን ምድር አስነክቶ መነሣት ነው ።

አስተብርኮ ፣ ጉልበትን ምድር አስነክቶ መነሣት ነው ።

አድንኖ ፣ ራስን ወደታች ዝቅ አድርጎ እጅ መንሣት ነው ።

በቤተ ክርስቲያን ስግደት የሚፈጸምባቸው ጊዜያት

ሀ) ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲገባ (መዝ፡28፡2) ።

ለ) ጸሎት ሲጀመር ፣

ሐ) በጸሎቱ መካከል ስግደት ከሚያነሣ ቃል ላይ ሲደረስ ፣

መ) እንዲሁም በጸሎቱ መጨረሻ ላይ መስገድ እንደሚገባ በፍትሕ መንፈሳዊ አንቀጽ 14፡35–37 ። በአለው የታዘዘ የአምልኮት መግለጫ ሥርዓት ነው ።

www.zeyeneta.com

ስግደት በሰንበት ፡ በበዐለ ሐምሳ ፡ በጌታችንና በእመቤታችን በሌሎችም ዐበይት በዐላት ፡ ሥጋውንና ደሙን ከተቀበሉ በኋላ ከአድንኖና ከአስተብርኮ በቀር ስግደት አይሰገድም ፡ (ፍትሕ መንፈሳዊ አንቀጽ 14፡537) ።

ስግደት ሁለት ዓይነት ነው ።

እርሱም ፡

1· ለእግዚአብሔር አምላክ የምናቀርበው ስግደት ፡ አስተብርኮና አድንኖ የባሕርይ ስግደት ነው ።

በታቦተሕጉ ፊትም ለእግዚአብሔር የሚቀርብ ስግደት የአምልኮት ስግደት ነው ። (ኢያሱ·7፡6፡ ፊል·2፡10) ።

2· ሀ) ለእመቤታችን

ለ) ለቅዱሳን መላእክት

ሐ) ለጻድቃንና ለሰማዕታት

መ) ለመስቀልና ለሥዕል የምናቀርበው ስግደት ፡

አስተብርኮና አድንኖ የጸጋ ፡ የአክብሮት ስግደት ነው ።

ምዕራፍ ፲፮

ሥርዐተ በዓላት

የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ስለ በዐላት አከባበር የራስዋ የሆነ ሥርዓት አላት ። ከሁሉ በፊት ቤተ ክርስቲያናችን ቅዳሜንና እሑድን ታከብራለች ።

የቅዳሜ መከበር በብሉይ ኪዳን ታቦአል (ዘፀ·20፡8)

በዘመነ ሐዲስ የክርስቲያኖች የቀዳሚት ሰንበት አከባበር እንደ አይሁድ ለሰው የሚከብድ እንዳይሆን ቤተ ክርስቲያን "አይደልመሙ ለክርስቲያን ከመ ያጽርኡ ተገብሮ በዕለተ ሰንበት ከመ አይሁድ አላይትገበሩ ከመ ክርስቲያን ፡ ወኢትትዓቀቡ ሰንበተ ከመ አይሁድ" (ፍት·መን·አን·19።) በሚለው መሠረት እንዲፈፀም ታስተምራለች ።

ሰንበተ ክርስቲያን እሑድም ጌታ ከሙታን ተለይቶ ስለተነሣበት የጌታ ቀን ተብላ በሐዲስ ኪዳን የከበረች ዕለት ናት፡ (ራእ· 1፡10፡1ቆሮ·16፡1) ።

www.zeyeneta.com

"ሰንበተ ክርስቲያንን አከበራት ፡ ከፍ ከፍም አደረጋት ፡ የብርሃን ቀን አላት ፡ ከዕለታትም ሁሉ አበለጣት" (ቅዱስ ያሬድ ድጓ ዘፋሲካ።)

እንዲሁም "ወዕረፍትሰ አኮ በሰኪብ ከመ ዘሐመ በደዌ አላ በትጋህ መዓልተ ወሌሊተ ከመ ንኩን ፍቁራንሃ ለዛቲ ዕለት" (ቃዳሲ አትና ቴዎስ 17–4) በሚለው መሠረት ምእመናን በቤተ ክርስቲያን እየተገኙ በመጸለይ ፡ የተቸገሩትን በመርዳት ፡ የታመሙትን በመጠየቅና የተጣሉትን በማስታረቅ እንዲያከብሩ ታስተምራለች ።

በቀኖና ቤተ ክርስቲያን መሠረት የጌታ ዐበይት በዐላት ዘጠኝ ናቸው ። እነዚህም ዐበይት በዓላት ፡

1ኛ· ትስብእት (ዕንሰት)
2ኛ· ልደት
3ኛ· ጥምቀት
4ኛ· ደብረ ታቦር
5ኛ· ሆሣዕና
6ኛ· ስቅለት
7ኛ· ትንሣኤ
8ኛ· ዕርገት
9ኛ· ጰራቅሊጦስ ናቸው ።

1ኛ· ትስብእት (ዕንሰት)፦ ይህ በዓል የሚከበረው መጋቢት 29 ቀን ነው ። መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ለድንግል ማርያም የአምላክን ከርሷ ሰው መሆን ያበሠረበት ዕለት ነው ። በመንጸፈ ያይን ወድቆ ለነበረው የሰው ዘር ታላቅ የምሕረት ቀን ነው ።

2ኛ· ልደት፦ ልደት በነቢያት ትንቢት የተነገረለት የሰውን ልጆች የፈጠረ ቃለ እግዚአብሔር ወልድ ፡ ሰውን ለማዳን ሰው ሆኖ ከቅድስት ድንግል ማርያም የተወለደበት ዕለት ነው ። ልደት በየዓመቱ የሚከበረው ታኅሣሥ 29 ቀን ነው ። በዘመነ ዮሐንስ ግን (የሉቃስ ጳጉሜን ስድስት ስትሆን) ልደት ታኅሣሥ 28 ቀን ይከበራል ።

3ኛ· ጥምቀት፦ ክርስቶስ በተወለደ በ30 ዓመቱ ተጠምቆ ሥራውን ጀምሯል ። ጌታ የተጠመቀው በፈለገ ዮርዳኖስ ነው ፡ ያጠመቀውም ዮሐንስ ወልደ ዘካርያስ ነው ። በተጠመቀም ጊዜ አብ በደመና ሁኖ የምወደው ልጄ ይህ ነው ፡ ብሎ መስክሮለታል ፡ መንፈስ ቅዱስም በርግብ አምሳል ወርዶ በራሱ ላይ ተቀምጧል ። (ማቴ·3፡1–17 ፡ ማር·1፡4–12 ፡ ሉቃ·3፡22 ፡ ዮሐ· 1፡ 29–34) ።

ይህ በዓልም በሚከበርበት ጊዜ በዋዜማው ታቦታቱ ከየቤተክርስቲያናቸው ወጥተው በወንዝ ዳር በዳስ ወይም በድንኳን ያድራሉ። ሌሊት

www.zeyeneta.com

ስብሐተ እግዚአብሔር ሲደርስ አድሮ ሥርዐተ ቅዳሴው ይፈጸማል ። ሲነጋ በወንዙ ዳር (በግድቡ) ጸሎተ አኰቴት ተደርሶ አራቱም ወንጌላት ከተነበቡ በኋላ ውሃው ተባርኮ ለተሰበሰበው ሕዝብ ይረጫል ። ይህም ጥምቀትን ለመድገም ሳይሆን የጌታችንን ጥምቀት ለማስታወስና በረከትን ለመቀበል ነው ። ጥምቀት የሚከበረው በያመቱ ጥር 11 ቀን ነው።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በያመቱ ይህን የምትፈጽመው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፡

በነቢያት የተነገረውን ትንቢት ለመፈጸም ፡

= ውሃን ለመቀደስ ፡

= ለጥምቀት ኃይልን ለመስጠት ፡

= ለእኛ አርአያና ምሳሌ ለመሆን ያሳየውን ትሕትና ለመመስከርና ለማስተማር ነው ።

4ኛ· ደብረ ታቦር፡– ደብረ ታቦር ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማስተማር በነበረበት ጊዜ በደብረ ታቦር ላይ ብርሃነ መለኮቱን የገለጠበት ዕለት ነው (ማቴ·17፡1–9) ። ይህ በዐል በያመቱ ነሐሴ 13 ቀን ይከበራል ።

5ኛ· ሆሣዕና፡– ሆሣዕና ከትንሣኤ አንድ ሳምንት ቀድሞ በሚውለው እሑድ የሚከበር ዐቢይ በዐል ነው ። ታሪኩ በወንጌል ተጽፎአል (ማቴ·21፡9–15) ።

ሆሣዕና ማለት መድኃኒት ማለት ነው ። በዚያች ዕለት ጌታ ወደ ቤተ መቅደስ ሲገባ ‘‘ሆሣዕና በአርያም’’ እያሉ ስላመሰገኑት ዕለቱ በጌታ ስም ተጠርቷል ። በዚህ በዐል ጸበርት ‘‘ዘንባባ’’ እየተባረከ ለሕዝብ ይታደላል። ሕዝቡም ጸበርቱን እየተቀበለ እንደ መስቀል አድርጎ እየሠራ በየቤቱ ይሰቅለዋል ፡ በራሱም ያስረዋል ። በዚህ በዐል በቅዱስ ያሬድ የተዘመሩት መዝሙራት እየተዘመሩ በቤተ ክርስቲያን በአራቱም ማዕዘናት አራቱ ወንጌላት ይነበባሉ ።

6ኛ· ስቅለት፡– የስቅለት በዓል ለዓለም ቤዛ ሊሆን መድኃኔዓለም ክርስቶስ የተሰቀለበት ዕለት ነው ።

7ኛ· ትንሣኤ፡– ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እኛን ለማዳን በመስቀል ተሰቅሎ ሞተ ፡ ተቀበረ ፡ በሦስተኛውም ቀን መግነገ

www.zeyeneta.com

ፍቱልኝ ፡ መቃብር ክፈቱልኝ ፡ ሳይል ከሙታን ተለይቶ ተነሣ ። ይህም የትንሣኤ ዕለት ለክርስቲያኖች የድልና የነፃነት ቀን ነው ።

የትንሣኤ በዐል በቤተ ክርስቲያናችን በጣም በደመቀ አኳኋን በመንፈሳዊ ተመስጠ ይከበራል ። ቅዳሜ ማታ ለእሑድ አጥቢያ ሕፃኑ ፡ ሽማግሌው ፡ ወጣቱ ፡ ባልቴቱ በየሰበካ ቤተ ክርስቲያናቸው ይሰበሰባሉ። ሥርዐተ ጸሎት ይጀመራል ።

ለትንሣኤ በዐል በቀኖና ቤተ ክርስቲያን የተሠራው ሥርዓተ ጸሎት ከተከናወነና ኪዳን ከተደረሰ በኋላ ካህኑ መስቀሉን ይዞ ፡ ክርስቶስ ተንሥአ እሙታን ፡

በዐቢይ ኃይል ወሥልጣን ፡

አሰሮ ለሰይጣን ፡

አግዐዞ ለአዳም ፡

ሰላም ፡

እምይእዜሰ

ኮነ

ፍስሓ ወሰላም የሚለው የትንሣኤው የምሥራችና የምስክርነት ቃል በማስተጋባል ከተባለ በኋላ የመስቀል መሳለሙ ሥርዓት ይቀጥላል ።

በመንፈቀ ሌሊት ጸሎተ ቅዳሴ ይጀመራል ። ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰዓት ሲሆን ሠርሑተ ሕዝብ ይሆናል ።

ከእሑድ ጀምሮ እስከ ዳግም ትንሣኤ ያሉት ዕለታት እንደ አንድ የትንሣኤ ዕለት ናቸው ።

8ኛ· <u>ዕርገት</u>፡— ዕርገት ጌታ ከሙታን ተለይቶ ከተነሣ በኋላ እስከ ዓርባ ቀን ድረስ ለሐዋርያት እየተገለጠ ታይቷቸዋል ፡ አስተምሯቸዋል ። በተነሣ ባርባኛው ቀን ቀደም አድርጎ እንደነገራቸው ለሐዋርያት አሁንም የመንፈስ ቅዱስን መምጣት ነግሮ ወደ ሰማይ ያረገበት ቀን ነው ። ይህ በዐል በቤተ ክርስቲያን በጸሎት በማሕሌት ይከበራል ።

9ኛ· <u>ጰራቅሊጦስ</u>፡— ጰራቅሊጦስ ጌታ ባረገ ባሥረኛው በተነሣ ባምሳኛው ቀን መንፈስ ቅዱስ በሐዋርያት ላይ የወረደበት ዕለት ነው ። ጰራቅሊጦስ ማለት አጽናኝ ማለት ነው ። ይህ በዐል በብሉይ ኪዳን የእሸት በዐል ነበር (በዐለ ሰዊት።) እሥራኤል የነፃነት በዐላቸውን ከሚያከብሩበት ከበዐለ ፋሲካ (በዓለ ፍሥሕ) ጀምረው አምሳውን ቀን በዐል

www.zeyeneta.com

አድርገው ይሰነብታሉ ። በአምሳኛይቱ ቀን በዐለ ሰዊትን (የእሸት በዐላቸውን) ያከብራሉ ።

ጌታ ባረገ ባስረኛው ቀን ከጠዋቱ በሦስት ሰዓት መንፈስ ቅዱስ በሐዋርያት ላይ ወረደ ። (የሐዋ·2፡1—5) ። ጌታ የነገራቸው የተስፋ ቃል ሁሉ ተፈጸመ ። ሐዋርያት መንፈስ ቅዱስን ተቀብለው የሞቱና የትን ሣኤው ምስክሮች ሆኑ ፡ የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ በነሱ፡ ላይ ሲያድር ለቤተ ክርስቲያን ገብ አዲስ ምዕራፍ ተከፈተ ። ሊቁ ዮሐንስ አፈወርቅ እንዳለው "ይህች ዕለት የቤተ ክርስቲያን የልደት ቀን" ትባላለች ።

የጳራቅሊጦስ በዐል ከትንሣኤው በኋላ ባምሳኛው ቀን ይከበራል ። የትንሣኤው ቀለም በቤተ ክርስቲያናችን የሚፈጸመው የጳራቅሊጦስ ዕለት ነው ።

ዘጠኙ ዐበይት በዐላት ከተግባረ ሥጋ በመታቀብ የሚከበሩ ሲሆኑ የትመጣቸውና እንዲሁም የአከባበራቸው ሥነ ሥርዓት ከዚህ በላይ እንዳየነው ነው ። ከነዚህ ውስጥ "ሆሣዕና ፡ ስቅለት ትንሣኤ ፡ዕርገትና ጳራቅሊጦስ ፡ በዐላት ዐዋድያት" ስለሆኑ በቀን አቆጣጠር መባጃ ሐመርን ተከትለው በኢየዐርግና በኢይወርድ ይመላለሳሉ ። ዕለታቸው ግን አይፋለስም ። ሆሣዕና ትንሣኤ ጳራቅሊጦስ እሑድን ፡ ስቅለት ዐርብን ፡ ዕርገት ፡ ሐሙስን አይለቅም ። ሌሎቹ ትስብእት (ጽንስት) ፡ ልደት ደብረታቦር ፡ ጥምቀት" ግን አዋድያት አይደሉም ። ዕለታቸውም የተወሰነ አይደለም ።

ከዘጠኙ ዐበይት በዐላት ሌላ ዘጠኝ ንኡሳን በዐላት አሉ ።
እነርሱም ፡

1ኛ· ስብከት
2ኛ· ብርሃን
3ኛ· ኖላዊ
4ኛ· በዐለ ጌና
5ኛ· ግዝረት
6ኛ· ልደተ ስምዖን
7ኛ· ቃና ዘገሊላ
8ኛ· ደብረ ዘይት
9ኛ· መስቀል ናቸው ።

ሀ· ስብከት
ለ· ብርሃን
ሐ· ኖላዊ ፡— እነዚህ ሦስት

www.zeyeneta.com

በዐላት ከልደት በፊት በሚውሉ ሦስት እሑዶች የሚታሰቡ ናቸው ። ነቢያት 'ይወርዳል ይወለዳል' ብለው በትንቢት ይጠባበቁት የነበረው ክርስቶስ "የዓለም ብርሃን ፡ የነፍሳት ጠባቂ ነው" ለማለት በቤተ ክርስቲያናችን የመዝሙርና የጸሎት ሥርዐት ከልደቱ ቀደም ብሎ ያሉት ሦስት እሑዶች "ስብከት ፡ ብርሃን ኖላዊ" ተብለው ተሰይመዋል ። አከባበራቸውም በስብሐተ እግዚአብሔር ነው ።

መ) <u>በዐለ ጌና</u>፡–

ይህ በዐል የሚከበረው ታኅሣሥ 28 ቀን ነው ። በቤተ ክርስቲያናችን በዐላት ሁሉ ከዋዜማቸው ጀምሮ የሚከበሩ መሆኑ ግልጥ ነው ። ስለሆነም ይህ በዐል የጌታ የልደቱ ዋዜማ በመሆኑ በየዓመቱ የሚከበር ከመሆኑም በላይ በየወሩም "አማኑኤል" (እግዚአብሔር ከእኛ ጋር) ለሚለው ስሙ መታሰቢያ ሁኖ ተሰጥቶአል ።

ሠ) <u>ግዝረት</u> ፡–

ይህ በዐል የሚውለው ጥር ስድስት ቀን ነው ። በሙሴ ሕግ እንደተጻፈ (ዘሌ·12፡3) ሕፃን ሲወለድ በስምንት ቀኑ ይገዘራል ። ይህን የሙሴን ሥርዓት ለመፈጸም ጌታ በተወለደ በስምንተኛው ቀን ወደ ቤተ ግዝረት ገብቶአል ። ሉቃ· 2፡21 የተወለደው ታህሣሥ 29 ቀን ሲሆን ስምንተኛው ቀን የሚውለው ጥር 6 ቀን ነው ፡ ይህ ቀን ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ሲከበር ይኖራል ።

ረ) <u>ልደተ ስምዖን</u>፡–

ይህም በዐል ጌታ በተወለደ በአርባኛው ቀን የሚከበር ነው ። ጌታ ሥርዐተ ኦሪትን ትንቢተ ነቢያትን ሊፈጽም እንጂ ሊሽር ስላልመጣ ለሙሴ ሕግን የሰጠ ሲሆን የሙሴን ሕግ ፈጽሟል ። ከላይ እንዳየነው በስምንተኛው ቀን ወደ ቤተ ግዝረት ገብቷል አሁን ደግሞ በተጻፈው መሠረት ዘሌ·12 የሙሴን ሕግ ለመፈጸም "ፅኑስ ርግብ ፡ ዘውግ ማዕነቅ" ይዘው ወደ ቤተ መቅደስ ወሰዱት ። በዚያም የእሥራኤልን መጽናናት ይጠባበቅ የነበረው ስምዖን የሚባል ሽማግሌ ክርስቶስን ሳያይ እንደማይሞት ከመንፈስ ቅዱስ ተረድቶ ጌታ በእናቱ እቅፍ ወደ ቤተ መቅደስ ሲገባ በእግዚአብሔር ፈቃድ ወጥቶ በእዚያ ስለነበረ ፡ ጌታን ከእመቤታችን ተቀብሎ ታቅፎ በሉቃስ ወንጌል በምዕራፍ ሁለት ከቁጥር

www.zeyeneta.com

25–32 ያለውን ጸለየ ። ወደ ቤተ መቅደስ የገባበትና በስምዖን ዕቅፍ የታየበት ዕለት በቤተ ክርስቲያን ይከበራል ። ስምዖን ጌታን በታቀፈ ጊዜ ከእርጅናው ስለታደሰ በዐሉ የጌታ ሁኖ ሳለ ልደተ ስምዖን እየተባለ ይጠራል ።

ሰ) <u>ቃና ዘገሊላ</u>፡–

ቃና በገሊላ አውራጃ የምትገኝ መንደር ናት በዚች መንደር ጌታ በሠርግ በዐል ላይ ተገኝቶ ነበር ። (ዮሐ·2፡11–12)። ይህ ዕለት የጌታ የመጀመሪያ ተአምር የተገለጠበት ስለሆነ በታላቅ ሥነ ሥርዐት እናከብረ ዋለን ። ይህ በዐል የሚውለው በየካቲት 23 ቀን ነበር ፤ ጌታ ዕለቱን ተጠምቆ ዕለቱን ወደ ገዳመ ቆሮንቶስ ሄዷል ። ከተመለሰ በኋላ በሦስተኛው ቀን ወደ ሠርግ ቤት ተጠርቶ የካቲት 23 ቀን ውሃውን የወይን ጠጅ በማድረግ የመጀመሪያውን ተአምር አሳይቷል ። (ዮሐ·2፡1–12)። አሁን ግን በዐልን ከበዐል ጋር ለማገናኘት ሲባል በተሠራው ሥርዓት መሠረት የጥምቀት በዐል በዋለ በነጋው ጥር 12 ቀን እናከብረዋለን ።

ሸ) <u>ደብረ ዘይት</u>፡–

ደብረ ዘይት የወይራ ዛፍ የመላበት ተራራ ማለት ነው ። የሚገኘውም በኢየሩሳሌም በስተምሥራቅ 75 ሜትር ያህል ራቅ ብሎ ነው ። ጌታ ቀን በቤተ መቅደስ ሲያስተምር ደቀ መዛሙርቱ የዳግም ምጽአቱን ምሥጢር አንሥተው ጠይቀውት ምልክቱን ገልጦ ነግሮአቸዋል። (ማቴ·24)።

የቤተ ክርስቲያናችን ሊቅ ቅ/ያሬድም የዐቢይ ጾምን እኩሌታ እሑድ የጌታ ዳግም ምጽአት መታሰቢያ አድርጎ መዝሙሩን በዳግም ምጽአት ደርሶታል ። ዕለቱም ደብረዘይት ይባላል ። ስለዚህ ይህ በዐል ስለ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት ፤ ስለዓለም ፍጻሜ ስለትንሣኤ ሙታን የሚነገርበት ዕለት ነው ።

ቀ) <u>መስቀል</u>፡–

የመስቀል በዐል የሚከበረው መስከረም 17 እና መጋቢት 10 ቀን ነው ። ታሪኩም በመጠኑ እነሆ ፤ ጌታ በመስቀል ላይ ሙቶ ከተነሣ በኋላ ሕመማን መስቀሉን እየዳሰሱ በመስቀሉ እየታሹ ይፈወሱ ነበር ። በዚህም ተአምራት እየተሳቡ ብዙዎች ክርስቲያን ሆኑ ። ይህን ያዩ

www.zeyeneta.com

አይሁድ መስቀሉን ባንድ ጥራጊ ማጠራቀሚያ ቦታ ጣሉት ። በየቀኑ የአካባቢው ኗሪ ሁሉ ጥራጊ ስለሚጥለበት ያ ቦታ እንደኮረብታ ሆነ። ምንም እንኳ ለማውጣት ባይችሉ ክርስቲያኖቹ ያን ቦታ ያውቁት ነበር ።

ከጊዜ በኋላ በጥሪስ ወረራ 70 ዓ·ም· ክርስቲያኖቹ ኢየሩሳሌምን ጨርሰው ለቀው ስለወጡና የከተማዋም መልክ ፈጽሞ ስለተለወጠ መስቀሉ የተዳፈነበት ቦታ ወዴት እንደሆነ ለማወቅ አልተቻለም ። በዚህም ምክንያት ከሦስት መቶ ዓመት በላይ ተዳፍኖ ቆይቷል ።

በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን (327) የንጉሥ ቆስጠንጢኖስ እናት ንግሥት ዕሌኒ ይህን ታሪክ ትሰማ ነበርና አስቆፍራ ለማስወጣት ጉዞዋን ወደ ኢየሩሳሌም ቀጠለች ። እዚያም ደርሳ ኮረብታ የሆነውን ሁሉ ብታስቆፍር መስቀሉ ያለበትን አላገኘችውም ። ሰውም ብትጠይቅ የሚያውቅላት አላገኘችም ። በመጨረሻ ግን የመስቀሉ መውጣት የእግዚአብሔር ፈቃዱ ነበርና አንድ አረጋዊ ስሙ ኪርያኮስ የሚባል (ኪራኮስ ያሬድ ድጓ ዘዕሌኒ) የዕሌኒን መቸገር አይቶ እንደሚከተለው ይመክራታል ። ''አንቺም በከንቱ አትድከሚ ሰውም በከንቱ አታድክሚ እንጨት አሰብስበሽ ከምረሽ ዕጣን አፍሺበት በእሳትም አያይገርው ፣ የዕጣኑ ጢስ ወደላይ ወጥቶ ወደታች ሲመለስ አቅጣጫውን አይተሽ አስቆፍረው ፣ በዚህ ምልክት ታገኝዋለሽ'' አላት ፣ (ስንክሳር መጋቢት 10) እሷም ያላትን ሁሉ አደረገች ። ''ዘዕጣን አንጸረ ሰገደ ጢስ'' (ድጓ ዘዕሌኒ) የዕጣኑ ጢስ ወደ ላይ ወጥቶ ወደ ታች ሲመለስ መስቀሉ ያለበትን ቦታ በጣት ጠቅሶ እንደማሳየት ያህል አሳየ ፣ ያን ምልክት ይዛ አውጥታዋለች። ''በጎልጎታ ዘደፈኑ አይሁድ ዮም ተረክበ ዕፀ መስቀል '' ድጓ ዘዕሌኒ)። ይህን በዓል በመላው ዓለም ያሉ ክርስቲያኖች ያከብሩታል። በሀገራችን በኢትዮጵያ ግን የላቀና ልዩ የሆነ የአከባበር ሥርዐት አለው ። የመስቀል በዐል ከጥቢ ወራት መግቢያ ጋር የተያያዘ ስለሆነ የተለየ ድምቀት አለው።

መስከረም 16 በከተማም ሆነ በገጠር በየአካባቢው ''መስቀል አደባባይ መስቀል ተራራ'' ተብሎ በተወሰነውና በተከበረው ቦታ ሕዝቡ ከየቤቱ ችቦውን እንጨቱን እያመጣ ይደምራል ። ካህናቱም በደመራው ፊት ለፊት ጸሎት አድርሰው ''መስቀል አብርሀ ፣ በክዋክብት አሠርገው ሰማየ እምዙሉሰ ፀሐየ አርአየ'' እያሉ ደመራውን እየዞሩ ይዘምራሉ ። ቀጥሎም ሕዝቡ ፣ ''ኢዮሃ አበባዬ መስከረም ጠባዬ'' እያሉ ደመራውን

www.zeyeneta.com

ይዞራሉ ሕዝቡ በየደጁ ችቦውን እያበራ ደስታውን ሲገልጥ ያመሻል ። በአሥራ ሰባት ጧት ደመራው ይለኮሳል ። በአዲስ አበባና በአንዳንድ ክ/ሀገር በ16 ማታ ደመራው ይለኮሳል ። አመድ እስኪሆን ድረስ ይቃጠላል ። ደመቆው የተጸለየበትና የተባረከ ስለሆነ ሕዝቡ ሕመቱንና ትርኳሹን እየተሻማ ወደየቤቱ ይዞ ይሔዳል ፣ ሰውም ከብትም ይቀባዋል ።

ንግሥት ዕሌኒ መስከረም 17 ቀን ማስቆፈር ጀምራ መጋቢት 10 ቀን መስቀሉ ስለተገኘና ስለወጣ መስከረም 17 እና መጋቢት 10 ቀን እንደ አንድ በዐል ተቆጥሮ ይከበራል ።

ከነዚህ ሌላ የእመቤታችን ሠላሣ ሦስት በዐላት በዓመት በኢት ዮጵያ ከጥንት ጀምሮ ሲከበሩ የኖሩ ናቸው ። አሁንም ይከበራሉ ። እንዲሁም በየወሩ በ29 የሚውለው በዓለ እግዚእ ፣ በ12 የሚውለው የቅዱስ ሚካኤል በዐል ፣ እንዲሁም የሐዋርያት በዐለ ዕረፍት ይከበራሉ ።

የዓመት በዐላት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የሚከበሩት በሥርዐተ ውደት ነው ። ለበዐሉ የተዘጋጀው መዝሙር እየተዘመረ ታቦቱ ከመንበሩ ተነሥቶ ቤተ ክርስቲያኑን ሦስት ጊዜ ከዞረ በኋላ ትምህርት ተሰጥቶ ሠርሐተ ሕዝብ ይሆናል ። ይህ የሚሆነው ጧት በሚቀደስባቸው ዕለታት ነው ። ውሎ ቅዳሴ ከሆነ ግን ውደት ተደርጎ ትምህርት ከተሰጠ በኋላ ታቦቱ ሲመለስ ጸሎተ ቅዳሴ ይጀመራል ። ጸሎተ ቅዳሴው ሲፈጸም ሠርሐተ ሕዝብ ይሆናል ።

የአጽዋማትና የበዐላት ኢየዓርግና ኢይወርድ የሚገኝበት ትምህርት "ባሕረ ሐሳብ" (መርሐ ዕውር) በተሰኘው የቁጥር መጽሐፍ ነው ።

በየዓመቱ በኢየዐርግና በኢይወርድ የሚመላለሱት አጽዋማትና በዐላት የሚውሉበት ዕለት የሚታወጀውም መስከረም 1 ቀን በርእሰ ዐውደ ዓመት ቅዱስ ዮሐንስ ዕለት ነው ።

የኢትዮጵያ ዘመን መለወጫ ወይም የአዲስ ዓመት መጀመሪያ ወር መስከረም ነው ። ይህም የጥፋት ውሃ መጉደል የጀመረበትና ከጥፋት ውሃ በኋላ የክረምትና በጋ መፈራረቅ እንደማያቋርጥ እግዚአብሔር ለኖኅ ቃል ኪዳን የሰጠበት ወር ነው ። (ዘፍ·8፡13–22 ፣ ኩፋሌ 7፡19–30)። የዕብራውያንና የግብፅ ዘመን መለወጫም ይኸው መስከረም ነው ። ቤተ

www.zeyeneta.com

ክርስቲያናችን ጥንታዊትና የብሉይ ኪዳን ትውፊት ያላት ስለሆነች ፡ ወሩም የዘመን መለወጫ እንዲሆን የተሰጠው ምክንያት ትክክለኛ በመሆኑ ይህን ሥርዐት ጠብቃና አስጠብቃ ትኖራለች ።

ምዕራፍ ፲፯

ሥዕል

ሥዕል በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከጥንት ጀምሮ የአክብሮት ሥርዐተ ትምህርት አለው ። ሥዕል ከክርስትና በፊት በቤተ አይሁድ የታወቀና ከአምልኮት ጋር የተያያዘ ነበር ።

በብሉይ ኪዳን በታቦተ ሕጉ ላይ ሥዕለ ኪሩብን እንዲሥል ራሱ እግዚአብሔር ሙሴን አዞታል ። (ዘፀ·25፡19 ፡ 37 ፡7 1ኛ· ነገ· 6፡23 ፡ 2ኛ ነገ·6፡2-17 ፡ ሕዝ· 9፡3 ፡ 10፡3 ፡ ሄኖክ 14፡11) ። እነዚህ የኪሩቤል ሥዕሎች ከታቦቱ አይለዩም ፡ ምክንያቱም ታቦት የእግዚአብሔር መገለጫ ዙፋን ስለሆነ ነው ሥዕለ ኪሩቤልም የፀወርቱ መንበር ኪሩቤል አምሳል ነውና ። የሚሣለትም እንደሚኖተፍ አውራ ዶሮ ሁነው ነው ።

ሥዕል በቤተ ክርስቲያን የተጀመረበት ታሪካዊ ምክንያት አለው ። በቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደሚታወቀው የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች ትምህርታቸውን ያስፋፉት ዋሻ ፈልፍለው ጉድጓድ ቆፍረው በዋሻ በፍርከኩስ (ካታኩምና) ግበበ ምድር) ውስጥ ነው ። ከዚህም ግበበ ምድር ውስጥ የሰማዕታትን አፅም እየሰበሰቡ ጸሎት ይጸልዩ ፡ ትምህርት ያስተምሩ ነበር ።

በዚህም አማኞች እየመጡ የማኅበሩ አባል መሆን ጀመሩ በዚህ ጊዜ የክርስትናን ትምህርት አስፋፍቶ ለማስረዳት በቂ መጻሕፍት ስላልነበሩ እንደ ልብም ወጥቶ ለመፈለግና ለማዘገጅት ነፃነት ስለአልነበራቸው ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንዳንድ ምሳሌዎችን በሥዕል እያቀረቡ ማስተማር ጀመሩ ።

ሥዕሎችንም የሚሥሉት ፡—

—እረኛው በጉን እንደተሸከመ አድርገው ነው ። ይህም "ክርስቶስ በእርሱ ያመኑትን በእርሱም አምነው የሞቱትን ሁሉ የሚያድናቸው ቸርና

www.zeyeneta.com

ታማኝ ጠባቂ መሆኑን ለማስረዳት'' ነበር ።
ሌላው ሥዕላቸውን የሚጀምሩት በብሉይ ኪዳን ታሪክ ነበር ።
ለምሳሌ የመጀመሪያዎቹ ሰዎች አዳምና ሔዋን እንዴት እንደተሳሳቱና
ያሳሳታቸውንም እባብ በመካከላቸው አድርገው ነበር ። (ዘፍ·3፡1–7) ።
በምህላና በጸሎት ላይ ያለችን የምእመን ነፍስ በመርከብ ውስጥ ያለውን
ኖኅን አስመስለው ይሥሉት ነበር ። (ዘፍ·7፡1–24) ። ከዚህም ጋር
የሐዲስ ኪዳንን ታሪክ በዚሁ ግብበ ምድር
የመልአኩ የቅዱስ ገብርኤል እመቤታችንን ማብሰር ፡
የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ በይሁዳ አውራጃ በዳዊት
ከተማ በቤተልሔም ምድረ ኤፍራታ መወለድ ፡
ሰብአ ሰገል በቤተ ልሔም ዋሻ ለተወለደው ሕፃን ክርስቶስ አምኑ
ሲያቀርቡ ፡
የጌታ ጥምቀትና የሦስት ዓመታት ከሦስት ወራት ትምህርት ጋር
የሠራውን ተአምራት ፡
በገሊላ አውራጃ በቃና ስለተደረገው የመጀመሪያው ተአምር ፡
የጌታ ስቅለቱን ሞቱን ፡ ትንሣኤውን ፡ ዕርገቱንና ዳግም ምጽአቱን ፡
እመቤታችን ምስለ ፍቁር ወልዳ በግራዋ በኩል ኢሳይያስ ወደ እስዋ
እያመለከተ ''ናሁ ድንግል ትፀንስ ወትወልድ ወልደ'' ብሎ የተናገ
ረላት ይህች ናት እንደ ማለት ነው ።

ይህንና ይህን የመሳሰሉ በጥንት የክርስቲያኖች መሸሸጊያ ዋሻዎች
ተሥለው ተገኝተዋል ። ይህ ሁሉ የተደረገው ከላይ እንደተገለጸው
የሃይማኖትን ታሪክ ለማስተማር ነው ።

በሌላም በኩል ስለጌታ ሥዕል ብዙ ታሪክና ትውፊታዊ ትምህርት
አለ ። ከሚነገሩት ታሪኮችም አንዱ የጌታን የነገረ መስቀሉን ታሪክ
ሐዋርያው የሐንስ እንደጣለው የሚተረከው ነው ። የሐንስ ወንጌላዊ
በዕለተ ዓርብ እንዳየው አድርጎ ጌታን ሥሎታል ። ስዕሉም ''በከመ
ሰቀሉኒ አይሁድ ቅድመ ዕራቅየ በኢየሩሳሌም ዳግመ ትሰቅሉኑ በሮም''
የሚል ድምጽ አሰምቷል ። ወዲያውም ከለሜዳ አስታጥቆ ሥሎታል ።
ከለሜዳ አሳታጥቆ መጣል የመጣም ከዚያ ወዲህ ነው ። የሐንስ
ወንጌላዊም ሥሎ ሲጨርስ ሥዕሉን ቢስመው ከንፈሩ ከሥዕሉ ጋር
ተጣብቆ ቆይቶአል ። ይህ ሁሉ ከሥዕሉ የታየው ተአምራት ነው ።

www.zeyeneta.com

የእመቤታችንን ሥዕል በመጀመሪያ የሣለ ወንጌላዊው ሉቃስ ነው ። በእኛም ቤተ ክርስቲያን የጸሎትና የመዝሙር መጻሕፍት የእመቤታችንን ሥዕል ወንጌላዊው ሉቃስ መሣሉን ይናገራሉ ።

"ሰላም ለሥዕልኪ እንተ ሠዐላ በእዱ ፡ ሉቃስ ጠቢብ እምወንጌላ ውያን አሐዱ" ይላል ። (መልክዐ ሥዕል ፡ ስንክሳር ጥቅምት 22 ቀን) ።

ሥዕል በቤተ ክርስቲያን ሁለት ዓይነት መልእክት አለው ። ከእነዚህም አንዱ ተአምራት ነክ የቅዱሳት መጽሕፍትን ታሪኮች ማንበብ ለማይችሉ ሰዎች ለማስረዳት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ማንንም ሳይፈራና ሳያፍር ስለሃይማኖቱ መስክሮ በሰማዕትነት የሞተ ወይም ስለ ዓለምና ስለራሱ በመጸለይ መላ ሕይወቱን ከፍትወታት እኩያት ከአጋንንት ጋር በመጋደል ያሳለፈውን ሰማዕት ወይም ጻድቅ በሥዕል ለማስታወስ በሥዕሉም አማካይነት እያንዳንዱ ምእመን ለሥዕሉ ባለቤት ያለውን ክብርና ፍቅር ለመግለጥ ነው ።

በሥዕል ፊት ቆሞ መጸለይ ከባለ ሥዕሉ ረድኤትን ፡ በረከትን መለመን ፡ መማጠን ነው ። ለሥዕል የጸጋ ስግደትን መስገድ ፡ ሥዕልን መሳለም ፡ በሥዕሉ አማካይነት ለሥዕሉ ባለቤት ክብርንና ፍቅርን ለመግለጥ ነው ። ይኸውም የቤተ ክርስቲያን ህልወና ከታወቀበት ጊዜ ጀምሮ የነበረ ጥንታዊ ትውፊት ነው ።

በቤተ ክርስቲያናችን ሥርዐት ለተጣሉና በጸሎት ለከበሩ የጌታ ፡ የእመቤታችን ፡ የቅዱሳን መላእክት ፡ ጻጽቃንና ሰማዕታት ሥዕሎች የጸጋ፡ የአክብሮት ስግደት ፡ አስተብርኮና አድንኖ ማቅረብ እንደሚገባ ቤተ ክርስቲያናችን ታምናለች ፡ ታስተምራለች ።

" ቅደመ ሥዕልኪ እሰግድ ፡ ወለሥዕለ ወልድኪ እገኒ ።
ማርያም ድንግል ማርያም እመ አዶኒ" (መልክዐ ሥዕል) ።

www.zeyeneta.com

ምዕራፍ ፲፰

መስቀል

መስቀል በቤተ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ ከፍተኛ ክብር አለው ። መስቀል በነቢያት ትንቢትና ምሳሌ መሠረታዊ ይዘት አለው ። ትንቢት "ሐረገ ወይን ኮነ መድኃኒትየ ዘእምሐሚሃን ይትገዘም ወበጎልጎታ የተከል" (መሐልይ 5፡2) ።

"ወወሀብኩሙ ትእምርተ ለእለ ይፍርሀከ ፡
ከመ ያምሥጡ እምገጸ ቅስት ፡
ወያድኅኑ ፍቁራኒከ" (መዝ· 59፡4 ተብሎ ተነግሮለታል ።

ምሳሌ፡ የኖኅ መርከብ የተሠራችበት እንጨት ። (ዘፍ·7–6) ።

ሙሴ የፈርዖን መሰግላንን ድል ያደረገበት በትር ። (ዘጸአ· 4፡2–9 አርዌ ብርት ዘኁል· 21፡9) ። የመስቀል ምሳሌዎች ናቸው ።

ከጌታችን ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ስቅለት በፊት መስቀል የመቅጫ ፡ የርግማንና የውርደት ምልክት ነበር ። (ዘዳግ· 21፡23 ፡ 2ኛ ቆሮ· 5፡21 ፡ ገላ· 3፡13) ።

ከጌታችን ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ስቅለት በኋላ ግን የክርስቶስ መስቀል የመንፈሳዊ ነፃነታችን ዓዋጅ የተነገረበት ሰላማዊ ዙፋን ። (መዝ·2፡6 እና 7፡44፡4፡) ስለሆነ ለክርስቲያኖች ሁሉ የነፃነትና የድል ምልክት ነው ። "ገብረ ሰላመ በመስቀሉ" ክርስቶስ ሰላምን ነፃነትን በመስቀሉ አደረገ ። (ኤፌ·2፡15–17) ።

ታላቁ ቅስጠንጢኖስ በብርሃን ቅርፅ ያየው መስቀል የድል ምልክት ሁኖ ይኖራል ። የመስቀል አማናዊና ምሥጢራዊ ኃይል ቅዱስ ጳውሎስ እንዳለው ላመኑ ነው እንጂ ላላመኑ ስንፍና ነው ። (1ኛ ቆሮ·1፡18 ፡ ፊል· 3፡18) ። እንዲያውም መስቀልን ኃይለ እግዚአብሔር ነው ማለቱ ዋነ ይመስላቸዋል ። የክርስቶስ መስቀል ለሞት ለአጋንንት መቅጫ ሆኖል ። "በመስቀሉ ዐሮ አግረረ ወልድ ዘዓለመ ፈጠረ"። (ቅዱስ ያሬድ መዋሥዕት) ።

ምእመናን በክርስቶስ አምነው በመስቀል አጋንንትን መናፍቃንን ፍትወታት እኩያትን ድል ሲያደርጉ ይኖራሉና ።

ከዚህ የተነሣ የክርስቲያኖች ኪነ ጥበብ ሁሉ ምልክቱ መስቀል

www.zeyeneta.com

ሆነ በልብሳቸው በመጽሐፋቸው በቤት ዕቃቸው ሁሉ የመስቀል ምልክት አለበት ።

በሀገራችንም ጥልፉ ዝምዝሙ ጌጣ ጌጡ ሌላው ቀርቶ ክርስቲያኖች በግንባራቸውና በሌላውም አካላቸው በመስቀል ቅርፅ ይነቀሳሉ ። በሕይወተ ሥጋ ሳሉ ብቻ ሳይሆን ከሞቱ በኋላ መስቀል ከምእመናን አይለይም ። አጽማቸው በሚያርፍበት በመቃብራቸው ላይ ሁሉ የመስቀል ቅርፅ ከዕፅ ወይም ከድንጋይ ይሠራል ። በመቃብራቸውም ላይ መደረጉ መስቀል የሞትና የመከራ ምሳሌ መሆኑ ቀርቶ የትንሣኤና የሕይወት ምልክት መሆኑን ለመግለጥ ነው ።

ከዚህ በላይ እንደገለጥነው ሥዕልና መስቀል በክርስቲያኖች ሕይወት ከፍተኛ ክብር ስላላቸው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንም በራሷ ኪነ ጥበብ በራሷ ሊቃውንት የተዘጋጁትን ሥዕልና መስቀል በጸሎተ ቡራኬ በማክበር በቤተ ክርስቲያን ምእመናንን ስታገለግልባቸው ትኖራለች ።

መስቀል በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ቡራኬ ይባረክበታል ።

ካህናት ሥልጣነ ክህነት ከተቀበሉበት ጊዜ ጀምረው መስቀል ይይዛሉ በመስቀል ይባርካሉ ። ምእመናንም ይሳለሙታል ።

በዚህም መሠረት ፡

"መስቀል ኃይልነ ፡

መስቀል ዕንዕነ ፡

መስቀል ቤዛነ ፡

መስቀል መድኀኒተ ነፍስነ አይሁድ ክህዱ ንሕነሰ

አመነ ወእለ አመነ ቢኀይለ መስቀሉ ድኅነ" እያለች ቤተ ክርስቲያን ትዘምራለች ትጸልያለች ።

ለመስቀልም የጸጋና የአክብሮት ስግደት ፡ እስተብርኮና አድንኖ ማቅረብ እንደሚገባ "ወንሰግድ ውስተ መካን ኀበ ቆመ እግረ እግዚእነ" (መዝ·131፡7)። "ለመስቀልከ ንሰግድ አሊቅነ ወለትንሣኤከ ቅድስት ንሴብሕ ዝክልነ" (ቅዱስ ያሬድ ጾመ ድጓ) የሚለውን መሠረት በማድረግ ታስተምራለች ።

www.zeyeneta.com

ምዕራፍ ፲፱

ንዋያተ ቅድሳት፡

ንዋያተ ቅድሳት ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን ለመፈጸም የሚያስችሉ የከበሩ ንዋያት ናቸው ። ለምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን አፈጻጸም አገልግሎት የሚውሉ የተለያዩ ንዋያተ ቅድሳት አሉ ።

እነዚህም ፡

= ጻሕል ፡ ቅዱስ ሥጋው የሚፈተትበት ነው ።

= ጽዋዕ ፡ ክቡር ደሙ የሚቀዳበት ነው ።

= ዕርፈ መስቀል ፡ ክቡር ደሙ የሚሰጥበት ነው ።

= ማሕፈድ ፡ በጌታ መግነዝ አንጻር ጎብስተ ቁርባኑ የሚሸፈንበት ነው ።

= መሶበ ወርቅ ፡ ጎብስተ ቁርባኑ ከቤተልሔም ወደ ቤተ መቅደስ የሚገባበት ነው ።

= ጽንሐሕ ፡ ለማዕጠንት አገልግሎት የሚውል ነው ።

= ቃጭል ፡ በቅዳሴ መግቢያ ፡ ዓሉ ንዑስ ክርስቲያን ሲባል እግዚአብ በሚያርስበት ጊዜ ፡ ድርገት በሚወረድበት ጊዜና በሌላም በጸሎተ ምህላ ጊዜ አገልግሎት የሚሰጥበትና ሌሎችም ለምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን አፈጻጸም አገልግሎት የሚውሉ ሁሉ ናቸው ።

እነዚህ ሁሉ ንዋያተ ቅድሳት ከላይ ለተገለጸው አገልግሎት የሚውሉት በጸሎት ፡ በሜሮንና በቡራኬ ከከበሩ በኋላ ነው ። ንዋያተ ቅድሳትን ለማክበር የሚጸለየው ጸሎትና የቅብዐ ሜሮን አፈጻጸም ሥርዐት በሥርዐተ ቅዳሴ መጽሐፍ ተጽፎ ይገኛል ።

ልብሰ ተክህኖ

ልብሰ ተክህኖ ካህናት ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን ለምእመናን ለመፈጸም በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ጊዜ የሚለብሱት በጸሎት የከበረ በአሠራርም በማስቀመጫም የተለየ የመንፈሳዊ አገልግሎት ልብስ ነው።

ይኸውም ፡—

ሀ) የሚቀደስባቸው አልባሳት በቤተ ክርስቲያን ዕቃ ቤት ሊቀመጡና በንጽሕና ሊጠበቁ ይገባል ። ከዚህ ውጭ በሌላ

www.zeyeneta.com

ቦታ እንዲቀመጡ ለሌላ ጉዳይም እንዲውሉ ያልተፈቀደለትም ሰው እንዲለብሳቸው አልተፈቀደም ። (ሕዝ·44 ፡ 17–19 ፡ ፍት·መን· አንቀጽ 12) ።

ለ) ካህናት የሚያርቡት ካባ ላንቃ 5 መንዲል (ክልጅ) ያለው እንዲሆን ታዟል ።

ሐ) ካህናት በቅዳሴ ጊዜ የሚለብሱት ልብስ እስከ ተረከዛቸው የሚያርስ መሆን አለበት ። (ፍት·መን·አንቀጽ 12 ፡ በስ)።

መ) ካህኑ ልብሰ ተክህኖ ከመልበሱ በፊት ልኩ የሚሆነውን መርጦ ይለብሳል ፡ ካህን ልብሰ ተክህኖ ከለበሰ በኋላ ማውለቅ አይገባውም ። ቀሚሱ ከረዘመበት ይታጠቀዋል ። (ዘፀ· 28፡ 243 ፡ ፍት·መን· አንቀጽ 12፡በስ)።

ሠ) ካህኑ ልብሰ ተክህኖ ከመልበሱ በፊት ጳጳስ ካለ በጳጳስ አስባርኮ ይለብሳል ።

ከሌለ ራሱ ባርኮ ይለብሳል ። ዲያቆናቱም አስባርከው ይለብሳሉ።

እነዚህ ንዋያተ ቅድሳትና አልባሰ ክህነት ሁሉ ወደ ቤተ ክርስቲያን ከገቡና በጸሎተ ቡራኬ ከከበሩ በኋላ ወደ ሌላ ቦታ ሊወሰዱና ለሌላ ለሥጋዊ አገልግሎት ሊውሉ አይገባም ። (ሕዝ·44 ፡ 17–19 ፡ ፍት·መን·አን· 12)።

እነዚህን ንዋያተ ቅድሳት ከቤተ ክርስቲያን አውጥቶ የሚወስድና ለማይገባ ሥራ የሚያውል ቢኖር ፡ እንደ ዖዝያንና እንደ ብልጣሶር ጥፋትንና መቅሠፍትን በራሱ ላይ ያመጣል ። (2ኛ ዜና መዋ·26 ፡ 18–20 ፡ ዳን· 5፡ 1–31)።

www.zeyeneta.com

ክፍል ፫

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የውጭ ግንኙነት

ምዕራፍ ፳

የውጭ ግንኙነት ቅድመ ክርስትና

ስለ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የውጭ ግንኙነት ጉዳይ በምልዓት ለመጻፍም ሆነ ለመናገር "ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች" ሲል ቅዱስ መጽሐፍ እንደሚናገረው ስሟ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን እምነት ተከታይ የሆነው ሕዝቧ መጠሪያ ከሆነው ከራስዋ ከአገሪቱ ጥንተ ታሪክ መነሣት ግዴታ ይሆናል ። (መዝ·67·31) ።

ከክርስትና በፊት በብሉይ ኪዳን እምነትና አምልኮ ከኢየሩሳሌም ቀጥሎ ሕገ ኦሪትን በመቀበል ሁለተኛዋ ሀገረ እግዚአብሔር የሆነችው ኢትዮጵያ ከተጓዳኟ ቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም ጋር የነበራት ግንኙነት ምን ጊዜም ሲዘከር የሚኖር ታሪካዊ ነው ። ግንኙነቱ ይደረግ የነበረውም ፡

= የብሉይ ኪዳን እምነትንና ሥርዐተ ትውፊትን በመጋራት

= በዓመት አንድ ጊዜ ቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም ላይ በመገኘት የፋሲካን በዐል በጎብረት በማክበር

= የአንድ ዓይነት ሕግ መጽሐፍዊ ተጠቃሚ በመሆን ፡ ወ·ዘ·ተ··· ሲሆን ይህም ግንኙነት የአገር ርቀት ሊገታው በማይችል ሂደት ላይ የቱን ያህል ጸንቶ የኖረና የሚኖር መሆኑን ከታሪክ ብቻ ሳይሆን በአሁኑም ዘመን ጎልቶ ከሚታየው የባህል ግንኙነት ማረጋገጥ ይቻላል ። በመሆኑም ይህ ግንኙነት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የውጭ ግንኙነት ታሪክ የመጀመሪያውን ደረጃ በመያዝ ሲጠቀስ ይኖራል ።

www.zeyeneta.com

ሀ· የግንኙነቱ መሠረታዊ ምክንያት

በብሉይ ኪዳን ኢትዮጵያና የብሉይ ኪዳን እምነትና አምልኮ ማዕከል በሆነችው ቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም መካከል ለተፈጠረው ጥንታዊ ግንኙነት ምክንያት ሴማዊና ካማዊ ትውፊት ነው ፡ የሁለቱም አህጉር ኗሪ የሆነው የብሉይ ኪዳን ሕዝብ የትውፊት የባህልና የቋንቋ ፡ የእምነትና የአምልኮ ተጓዳኝነት ያለው መሆኑ ስውር አይደለም ።

ካምና ሴም አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር የአደረገውና ከነቤ ተሰቡ ከጥፋት ውኃ የዳነው የጻድቅ ኖኅ ትውልድ እንደመሆናቸው መጠን የሁለቱም አበው ዘርዐ ትውልድ ወደ ኢትዮጵያ ዘልቆ የገባውም ሆነ ዘላቂ ኑሮውን በዚያው የመሠረተው ሴማዊ ትውልድ ቀደም ብሎ በሕገ ልቡና ፡ በኋላም በሕገ ኦሪት አፈጻጸም የጋራ ተሳትፎ ላይ የተመሠረተ ግንኙነቱን መቀጠል የማያቋርጥ ታሪካዊ ግዴታው ሆነ ፡ በቅዱስ ወንጌልም ሆነ በአንደኛ ነገሥት። (ማቴ· 12፡42 ፡ 1 ነገሥ· 10፡1–9)። በአድናቆት የተጠቀሰው የንግሥተ ሳባ የኢየሩሳሌም ጉብኝትም የዚህ ግንኙነት ውጤት ነበር ።

በሁለቱ አህጉር ሕዝቦች መካከል የቆየ ግንኙነት ባይኖርማ ኑሮ ንግሥተ ሳባም ስለኢየሩሳሌም መንግሥትና ሕዝብ ከሌላው የዓለም ሕዝብ የተለየ ዕውቀት ሊኖራት ባልቻለም ነበር ።

ለሁለቱም አህጉር ሕዝቦች ጥንተ ግንኙነት መሠረታዊ ምክንያት ይህ ሲሆን በዕርግጥ ይህ ግንኙነት በይበልጥ ሊጠናከር የቻለው ግን ከንግሥተ ሳባ የኢየሩሳሌም ጉብኝት በኋላ መሆኑ እሙን ነው ።

ለ· የግንኙነቱ ፍሬያማ ውጤት ከንግሥተ ሳባ ጉብኝት በኋላ

ከክርስቶስ ልደት በፊት በአንድ ሺህ ዓመተ ዓለም አካባቢ ከተደረገው ከንግሥተ ሳባ የኢየሩሳሌም ጉብኝት በኋላ ኢትዮጵያ በመንፈሳዊውም ሆነ ማኅበራዊው ዕድገት በኩል ያገኘችው በረከት በቀላሉ የሚገመት አይደለም ። የተገኘውን በረከት በዝርዝር ለመግለጽ ኢትዮጵያ ፡

– የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ባለቤት

www.zeyeneta.com

– የታቦተ ሕግ መንበር

– የሥዩማን ካህናት ተገልጋይ

– በተደራጀ ቤተ ክህነት የሥርዓተ አሪት አስፈጻሚ ሀገር ለመሆን የበቃችው ከንግሥተ ሳባ ታሪካዊ ጉብኝት በኋላ ነው ። ይህም የፈጠራ አንጋገር ሳይሆን በታሪክም በባህልም የተረጋገጠ ሐቅ ነው ።

ከንግሥተ ሳባ ጉብኝት በኋላ ሌዋውያን ካህናት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትንና ታቦተ ሕጉን ይዘው ወደ ኢትዮጵያ ስለገቡ በሕገ ልቡና አምልኮተ እግዚአብሔርን ተግባራዊ ታደርግ የነበረችው ሀገር ኢትዮጵያ አምልኮቷን በሕግ መጽሐፋዊ ለመፈጸም ወደምትችልበት የታሪክ ምዕራፍ ለመሸጋገር በቅታለች ።

እንደ ባጅ ያሉ ታዋቂ ታሪክ ጸሐፊዎች ኢትዮጵያ ያለሃይማኖት የኖረችበት የታሪክ ዘመን እንደሌለ ጽፈዋል ። ይህም የአገር ውስጥ ታሪክ ጸሐፊዎች ከሚሰጡት የምስክርነት ቃል ተጨማሪ ማስረጃ መሆኑ ነው ።

በአምልኮተ እግዚአብሔር አገራቱ ያላት የረዥም ዘመን ታሪክና አሁንም ከዚህች የመጽሐፍ ቅዱስ ሀገር (ኢየሩሳሌም) ጋር ያላት የቅርብ ግንኙነት ያለፈውን አሁን ባለው ላይ እንደመሥታወት የሚያንፀባርቅ ሕይወት ላለው ሕዝቧ የመታወቂያ ሰነዶች ናቸው ።

እንደዚያን ጊዜው ዘመኑ የእሥራኤል ቤተ መንግሥትና ቤተ ክህነት ባህልና ሥርዓት የኢትዮጵያ ቤተ ክህነትና ቤተ መንግሥት የመንፈሳዊና ማኅበራዊ ጽድቅን በመፈጸምና በማስፈጸም ኃላፊነት አንዱ ከሌላው የተለየ አልነበረም ፡

በኢትዮጵያ ይህ ጥምር ተግባር ይካሄድ የነበረውም የጥንታዊት ኢትዮጵያ ማዕከል በሆነችው አክሱም ነበር አክሱም ለኢትዮጵያ የአምልኮተ እግዚአብሔር ሕግና ሥርዓት መፍለቂያና ማሠራጫ ማዕከል የሆነች ቅድስት መካን ናት ።

በቅዱስ መጽሐፍ ስለ ኢትዮጵያ የሚነገረው ጥቅስም ሆነ የቤተ ክርስቲያኒቷ ጥንተ ታሪክ የሚያመለክተው አሪታዊ ለነበረውና በኋላም ክርስቲያናዊ ለሆነው የአገራቱ ሥርዓተ አምልኮ ቋንቋና ባህል ማዕከል ወደሆነችው አክሱም ነው ።

www.zeyeneta.com

የተለያዩ የጥንታዊት ኢትዮጵያ ታሪክ ምንጮችና እስከ አሁን ድረስ የተከሠቱ የከርሰ ምድር ጥናትና ምርምር ውጤቶች አሁን ካለው ቋንቋ ባህል ሃይማኖትና ሌሎች የኑሮ ገጽታዎች ጋር ተዛማጅነት ያላቸው መሆኑ ግልጽ ሁኗል ። እንደዚህ የታሪክ ማስረጃም የዚሁ ሁሉ ውርስ ማዕከል አክሱም ናት ። ከዚህም ጋር ይህን የታሪክና ባህል ማስረጃ መነሻ በማድረግ የኢትዮጵያ ቅድስት ከተማ የሆነችው አክሱም የታቦተ ሕጉ መንበር እንደሆነች በሁሉም ዘንድ የታመነ ነው ፡ ይህም ታቦተ ሕግ በሙሴ እጅ የተቀረፀው ጽላተ ሕግ ነው ።

የብሉይ ኪዳን ኢትዮጵያ ከክርስትና በፊት የነበራት የውጭ ግንኙነትና በግንኙነቷም የተገኘው ፍሬ ይህ ሲሆን ለጥንታዊነቷና ታሪካዊነቷ ዕውነትነት ትክክለኛ ማስረጃ ሆኖ ሊጠቀስ የሚችለውም ይህ ነው ።

ምዕራፍ ሰፍ

የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት በዘመነ ክርስትና

እስራኤላዊና የእስራኤልን እምነት የተቀበለ ወንድ ልጅ ሁሉ በዓመት ሦስት ጊዜ የሚያከብራቸው እጅግ የተከበሩ በዐላት ሦስት ናቸው። እነዚህም የቂጣ በዓል (በዐለናዕት) ፡ ከሰባት ሱባዔ በኋላ የሚከበረው በዐል (በዐለ ሰዊት) ፡ የዳስ በዐል (በዐለ መጸለት) ናቸው። እነዚህን በዐላት እስራኤላዊ ወንድ ሁሉ እግዚአብሔር በመረጠው ቦታ ማለት በእግዚአብሔር ቤት እየተገኘ ማክበር ግዴታው መሆኑን ሕገ አሪቱ ያዝዛል ። (ዘዳግም·16·16) ።

ይህን ሃይማኖታዊ ሕግ መሠረት በማድረግ ሕገ አሪትን የተቀበሉ ኢትዮጵያውያን ሁሉ እግዚአብሔር ወደ መረጠው ቦታ ወደ ኢየሩሳሌም እየሄዱ በዐል ያከብሩ ነበር። እስራኤላውያን በሕገ መሠረት ከፋሲካ በኋላ ሰባት ሱባዔ ቆጥረው በሚያከብሩት በዐል (በዐለ ሰዊት) የእሸት ቀዳምያት ለእግዚአብሔር በማቅረብ እግዚአብሔርን የሚያመሰግኑበት የምስጋና በዐል ነው ።

www.zeyeneta.com

ይህ በዐል ሲከበር ከየሀገሩ ተሰብስበው ከነበሩት ምእመናን መካከል ኢትዮጵያውያን ምእመናንም ይገኙ ነበር ። (ሶፎንያስ· 3·10)። ከትንሣኤ በኋላም ይህ በዓል በ34 ዓ·ም· በተከበረበት ጊዜ ሐዋርያት መንፈስ ቅዱስን ተቀብለው በየሀገሩ ልሳን (ቋንቋ) ሲናገሩና እግዚአብሔርን ሲያመሰግኑ በመደነቅ ከሰሙት ምእመናን መካከል ኢትዮጵያውያን እንደነበሩ ብዙ የቤተ ክርስቲያን አባቶች መስክረዋል ። ከእነዚህም አንዱ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በዐለ ሐምሳን አስመልክቶ ባሰማው ቃለ ስብከት "ቅዱሳን ሐዋርያት ጸጋ መንፈስ ቅዱስን በተቀበሉበት ወቅት በዚያው ከተገኙ የዓለም ምእመናን መካከል ኢትዮጵያውያንም ተገኝተው ነበር" ሲል ገልጾአል ። (ድርሳን ዘቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በሐዋ· ሥራ 2·1–13)።

የኢትዮጵያ ንግሥት ሕንደኬ ሙሉ ባለሥልጣን የነበረው ኢትዮጵያዊው ጃንደረባም ሕገ አሪት በሚያዘው መሠረት በ34 ዓ·ም· ወደ ኢየሩሳሌም ሄዶ እግዚአብሔርን ለመስግኖ በዐሉን አክብሮ ወደ ሀገሩ ሲመለስ በጋሣ መንገድ ከወንጌላዊ ፊልጶስ ጋር ተገናኘ ። በዚህ ጊዜ በሠረገላው ላይ ተቀምጦ የኢሳይያስን መጽሐፍ እየተመለከተ ሲሄድ እሱንና ወንጌላዊው ፊልጶስን መንፈስ ቅዱስ አገናኛቸው ። ወንጌላዊው ቅዱስ ፊልጶስ ኢትዮጵያዊው ባለሥልጣን ያነበው የነበረው የኢሳይያስን መጽሐፍ (ምዕራፍ አምሳ ሦስት) ስለ ጌታችን መከራ መስቀል የተነገረ ትንቢት መሆኑን ተረጐመለት ።

ከዚህም ሌላ ወልደ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ መሆኑን ። (ዮሐ·1፡29) ። በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ዓለምን ማዳኑን ተንትኖ ሰበከለት ። በዚህ ዓይነት ቅዱስ ፊልጶስ እያስተማረ ፡ ኢትዮጵያዊው ባለሥልጣን እየተማረ ውሃ ካለበት ቦታ· በደረሱ ጊዜ ኢትዮጵያዊው ባለሥልጣን ስለኢየሱስ ክርስቶስ የተማረውን ትምህርት ሙሉ በሙሉ መረዳቱን አውቆ "እነሆ ውሃ ፡ እንዳልጠመቅ የሚከለክለኝ ምንድር ነው?" አለው ፡ ፊልጶስም "በፍጹም ልብህ ብታምን ተፈቅዷል" አለው ፡ እሱም "ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ አምናለሁ" አለ ። በዚህ ጊዜ ሠረገላው ይቆም ዘንድ አዘዘ ። ቅዱስ ፊልጶስና ጃንደረባው ሁለቱም አብረው ወደ ውሃው ወረዱ ፡ ቅዱስ ፊልጶስ ጃንደረባውን አጠመቀው ።

www.zeyeneta.com

ከውሃውም ከወጡ በኋላ መንፈስ ቅዱስ ፊልጶስን ነጠቀው (ሰወረው)። ኢትዮጵያዊው ባለሥልጣን ግን ደስ ብሎት ወደ አገሩ ተመለሰ ። (የሐ·ሥራ· 8፡26–40)። በዚህ አኳኋን ይህ ኢትዮጵያዊ ባለሥልጣን የክርስትናን እምነት ተቀብሎ በታላቅ ደስታ ወደ አገሩ ገባ ። እንደተመለሰም የተቀበለውን የክርስትናን እምነትና ሥርዓተ ጥምቀቱን ለአገሩ ሕዝቦች በመግለጹ ዜና ክርስትና ከብዙዎቹ ጆሮ እንዲደርስና እንዲስፋፋ አድርጎአል ። የክርስትና እምነት በኢትዮጵያ ለፍሬ የበቃውም ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ነው ። "በእስራኤል አገር (በኢየሩሳሌም) ከሚኖሩ የእስራኤል ሕዝብ ቀጥሎ በክርስቶስ አምኖ በመጠመቅ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ የመጀመሪያው የወንጌል ፍሬ ነው" ሲል የቤተ ክርስቲያን ታሪክ አባት እየተባለ የሚጠራው አውሳብዮስ ዘቂሣርያ መስክሮአል ። አውሳብዮስ ዘቂሣርያ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ 2ኛ መጽሐፍ ቁ·1)።

ኢትዮጵያዊው ባለሥልጣን ከወንጌላዊው ከቅዱስ ፊልጶስ አንደበት በአጭር ጊዜ ውስጥ የወንጌልን ትምህርት ተምሮ የክርስትናን እምነት በመቀበል ክርስትናን ከተቀበሉት አስራኤላውያን ቀጥሎ የመጀመሪያው የክርስትና ፍሬ በመሆኑ እንደነጀሮም ያሉ የታወቁ የቤተ ክርስቲያን ሰዎች ተደንቀዋል ።

ከቅዱሳን ሐዋርያት መካከል ቅዱስ ማቴዎስ ፣ ቅዱስ ናትናኤል ፣ ቅዱስ በርተሎሜዎስ እንዲሁም ቅዱስ ቶማስ በኖብያና በኢትዮጵያ አውራጃዎች እየተዘዋወሩ ቅዱስ ወንጌልን እንደሰበኩ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊዎች እነ ሩፊኖስና እነ ሶቅራጥስ መስክረዋል ። በተለይ ሐዋርያው ቅዱስ ማቴዎስ በሕንድ በኩል አድርጎ ወደ ኖብያ ከዚያም ወደ ኢትዮጵያ ዘልቆ በመምጣት ቅዱስ ወንጌልን እንደሰበከና በዚያው አካባቢም በሰማዕትነት እንዳረፈ ጽፈዋል ።

በዘመናችን የሚገኙ አንዳንድ ዕውቅ ሰዎችም የፈተኛውን ታሪክ መሠረት እያደረጉ ሐዋርያው ቅዱስ ማቴዎስ በኢትዮጵያ ገብቶ እንዳስ ተማረ ያምናሉ ። አያይዘውም ኢትዮጵያን መንበረ ማቴዎስ (The Holy See of St. Matthew) በማለት ይጠሩአታል ።

ከዚህ በላይ እንደተገለጸው የክርስትና እምነትና ጥምቀት ክስተት በአክሱምና በአካባቢዋም በሚኖሩ የሰሜን ኢትዮጵያ ሕዝቦች በሚገባ

www.zeyeneta.com

ተቀባይነት አግኝቶ እየተሠራበትና እየተስፋፋ ፍሬምናጦስና ወንድሙ ኤዲሲዩስ ወደ አክሱም እስከመጡበት ድረስ ቆይቶአል ።

ምዕራፍ ፲፪

የኢትዮጵያን መንበረ ጵጵስና ለመመሥረት የተደረገ የውጭ ግንኙነት

የቤተ ክርስቲያን ምሥጢራት አፈጻጸም መሠረቱ ሥልጣነ ክህነት ነው ። ቀደም ብለን እንዳየነው ከመጀመሪያው ዘመነ ክርስትና ጀምሮ ፡ እስከ አራተኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ድረስ በኢትዮጵያ ሕገ አሪት ከእነ ሥርዐቱ እንዲሁም ሥርዐተ ጥምቀት ከነእምነቱ መሠረት ይዘ መቆየቱ ቢታወቅም ጳጳስ ባለመኖሩ ሥርዐተ ክህነትና ሥርዐተ ቁርባን ሳይፈጸም እስከ 330 ዓ·ም ድረስ ሊቆይ ችሎአል ።

ፍሬምናጦስ

በቤተ ክርስቲያናችን ካሉት የታሪክ መጻሕፍት በተጨማሪ ከአራተኛው መቶ ዘመን አጋማሽ እስከ አምስተኛው መቶ ዘመን መጀመሪያ ድረስ የኖረው ሩፊኖስ የተባለው የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊ ስለ ክርስትና እምነት ከእነ ሥርዐቱ በኢትዮጵያ ተሚልቶ ስለመሰጠቱ እንዲህ ሲል ጽፎአል ። በአራተኛው ክፍለ ዘመን በኢትዮጵያ በአክሱም ኢዛና እና ሳይዛና የተባሉ ሁለት ወንድማማቾች በእንድነት ነግሠው ነበር። በዚህ ጊዜ የጢሮስ ከተማ ተወላጅ የነበረው መሮፒዎስ ዘመዶቹ የሆኑትን ፍሬምናጦስንና ወንድሙን ኢዲስዩስን ወይም ሲድራኮስን አስከትሎ ሕንድን ለመጐብኘት በአዱሊስ ወደብ በኩል ሲያልፍ በወደቡ ዐረፈ ። በዚህ ጊዜ በድንገት ሽፍቶች (ወንበዴዎች) አደጋ ጣሉባቸውና ፈላስፋው መሮፒዎስ ተገደለ ፡ ፍሬምናጦስና ኤዲሲዮስ (ሲድራኮስ) ግን ከአደጋው ድነው ወደ አክሱም ቤተ መንግሥት ተወሰዱ ። በቤተ መንግሥቱ ማረፊያ እንዲሰጣቸው ተደርጎ ልዩ እንክብካቤ እየተደረገላቸው የአገሩንም ቋንቋና ባህል እያጠኑ ብዙ ጊዜ ኖሩ ። ንጉሡ ሁለቱንም በቤተ መንግሥቱ የሥራ ዘርፍ ሾማቸው ። ትንሹን ኤዲሲዮስን የቤተ መንግሥቱ አሳላፊና አዛዥ አድርጎ ሾመው ፡ ትልቁ ፍሬምናጦስ ግን

www.zeyeneta.com

በጣም ብልህና የተማረ ሰው ስለነበር የቤተ መንግሥቱ ግምጃ ቤትና ጸሐፊ አድርጎ ሾመው ፡ ከጥቂት ዓመታት በኋላ ንጉሡ ሞተ ። ነገር ግን ንጉሡ ከመሞቱ በፊት ፍሬምናጦስና ወንድሙ ኢዲሲዮስ ወደ አገራቸው ለመመለስ ከፈለጉ ሊሄዱ ይችላሉ ብሎ ቃለ ኑዛዜ ሰጥቶ ነበር ። ሆኖም የመንግሥቱን ኃላፊነት የተረከበችው ንግሥት አሕየዋ (ሶፊያ) ሕፃኑ ልጅዋ ለሥልጣነ መንግሥት እስኪደርስ ድረስ እስዋን እየረዱ እንዲቆዩ ለመነቻቸው ።

በዚህ ጊዜ ወጣት ክርስቲያን ፍሬምናጦስ ከክርስቲያን ከተሞች ወደ አዶሊስና ወደ አክሱም የሚመጡትን ክርስቲያን ነጋዴዎችን በየደረሱበት ከተማ የስብሰባ ቦታዎችንና የጸሎት ቤቶችን እንዲያበጁና እንዲሠሩ ያበረታታቸው ነበር ። ከዚህ የተነሣ የክርስትና እምነትና ዜናው በሕዝቡ መካከል ሊስፋፋ ቻለ ። በዚህ ጊዜም አባቱ ሲሞት ሕፃን የነበረው የንጉሡ ልጅ ጊዜው ሲደርስ ነግሦ ሳለ በፍሬምናጦስ አስተማሪነት የክርስትናን ትምህርት ተቀበለ ። ከዚህ ሌላም ፍሬምናጦስ በወቅቱ የአሪዩ ሊቀ ካህናት ከነበረው ከእንበረም ጋር ተገናኝቶ ስለ ክርስትና እምነትና ሥርዓት ያነጋግረው ነበር ። «እምነትና ጥምቀት እንዳላችሁ አያለሁ ሥርዓተ ቁርባን (ሥጋውን ደሙን መቀበል) ግን የላችሁም» አለው ። በዚህ ጊዜ ሊቀ ካህናት እንበረም «ጥምቀተሰ አምጽአ ለነ ሕጽዋ ለሕንደኬ ንግሥተ ኢትዮጵያ ... እምነትንና (ክርስትናን) ጥምቀትን የንግሥት ሕንደኬ ባለሥልጣን (ጃንደረባው) አምጥቶ አስተምሮናል» አለው ። በዚህ ወቅት የፍሬምናጦስ ወንድም ኢዲሲዮስ በንጉሡ ፈቃድ ወደ አገሩ (ወደጢሮስ) ተመለሰ ። ፍሬምናጦስ ግን የሥርዓተ ክህነትና ቁርባን መምጣት እጅግ አስፈላጊ መሆኑን ለንጉሡና ለቤተ መንግሥቱ ባለሥልጣኖች አጽንቶ ነገራቸው ። እነሱም ፍሬምናጦስን የእኛን ቋንቋና ባህል ፡ የእነሱንም ቋንቋና ባህል የሚያውቅ ከአንተ ሌላ የለምና አንተ ወደ እስክንድርያ ሄደኽ ክህነትንና ሥርዓተ ቁርባንን አምጣልን ብለው እሱን ወደ እስክንድርያ ሰደዱት ። ፍሬምናጦስ በቤተ መንግሥቱና በሕዝቡ ተልኮ ወደ እስክንድርያ ሄደ ። ወደ እስክንድርያ የተላከው ፍሬምናጦስ እንደ ኢትዮጵያዊ ሆኖ ነው እንጂ ትውልድ ሀገሩን ወክሎ እንዳልተላከ መገንዘብ ይገባል ።

በዚያን ጊዜ በ325 ዓ·ም· በኒቅያ ከተማ የመጀመሪያው ዓለም አቀፍ

www.zeyeneta.com

የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ተደርጎ አርዮስ ተወግዞ ከቤተ ክርስቲያን የተለየበት ፣ በ328 ዓ.ም. ደግሞ ቅዱስ አትናቴዎስ የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ሆኖ የተሾመበት ጊዜ ነበር ። ቅዱስ አትናቴዎስ ፍሬምናጦስ ከኢትዮጵያ ያመጣውን መልእክት ተቀብሎ ጉዳዩን ለማየት ጉባኤ አደረገ ። የቀረበው ጉዳይ በቅዱስ አትናቴዎስ ሊቀ መንበርነት በጉባኤ ታይቶ የአገሩን ቋንቋና የሕዝቡን ባህል የሚያውቅ ከፍሬምናጦስ በቀር ሌላ ሰው ስለሌለ ፍሬምናጦስ የአትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ሆኖ እንዲሾም ተብሎ ተወሰነ ። በውሳኔው መሠረት ቅዱስ አትናቴዎስ ፍሬምናጦስን «ኤጲስ ቆጶስ ዘአክሱም ወዘኵላ ኢትዮጵያ» ብሎ በአንብሮተ እድ ሾሞ ፣ አባ ሰላማም በማለት ሰይሞ ላከው ፍሬምናጦስ በ330 ዓ.ም የመጀመሪያ የኢትዮጵያ ጳጳስ ሆኖ ወደ ኢትዮጵያ ተመለሰ ። ወዲያውም ነገሥታቱን ኢዛናንና ሳይዛናን አስተምሮ አጠመቃቸው ፣ «አብርሐ ፣ አጽብሐ» ብሎም በክርስቲያን ስም ጠራቸው ። ከዚያም መንበረ ጵጵስናውን በአክሱም አድርጎ ሐዋርያዊ ሥራውን ማስፋፋት ጀመረ ፣ የቁርባንና የክህነትን ሕግ አስፋፋ ። በኢትዮጵያ ግዛት በሙሉ የወንጌልን ትምህርት ለማስፋፋት የሚረዱት ቀሳውስትንና ዲያቆናትን ሾመ ። ቅዱሳት መጻሕፍትን ከሱርስት ፣ ከዕብራይስጥና ከፅርዕ (ከግሪክ) ወደ ግዕዝ ቋንቋ መለሰ ። የሳባውያንን የፊደል አቀማመጥ የለወጠና ከግራ ወደ ቀኝ የመጻፍና የማንበብ ዘዴ የደነገገም እሱ ነው ።

በዚህ አኳኋን በ330 ዓ.ም ክርስትና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሃይማኖት ሆነ ይህም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በዓለም ሁሉ ታወቀ ። ቅዱስ ፍሬምናጦስ የሰላም ምንጭ የሆነውን ወንጌል ለሕዝቡ በመስበኩ «ከሣቴ ብርሃን» ተብሎ ቅጽል ተሰጠው ይኸውም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያትን «እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ» ብሎ እንደጠራቸው ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብም ቅዱስ ፍሬምናጦስን «ከሣቴ ብርሃን» (ብርሃንን የሚገልጽ) ብለው መጥራታቸው የሚገባ ነው ።

ቅዱስ አትናቴዎስ በ325 ዓ.ም. በኒቅያ ዓለም አቀፍ ጉባኤ የተወገዘውን አርዮስንና ክህደቱን በመቃወም ፣ ጉባኤው በሙሉ ጽምፅ ያጸደቀውን የኦርቶዶክስ እምነት በመጠበቅና በማስጠበቅ የመጀመሪያውን ቦታ የያዘ ታላቅ አባት ነው ። ቅዱስ ፍሬምናጦስም ከአባቱ ከቅዱስ አትናቴዎስ በተቀበለው ቃል ኪዳን መሠረት የአርዮሳውያንን የክህደት

www.zeyeneta.com

ትምህርት በመቃወም በኒቅያ የተወሰነውን እምነት ለኢትዮጵያ ሕዝብ በሚገባ ማስረዳቱ የታወቀ ነው ። ሆኖም በዚያን ዘመን የኒቅያን ዓለም አቀፍ ጉባኤ የጠራና የአርዮስንም መወገዝ በቀጥታ የደገፈው ታላቁ ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ በ337 ዓ·ም· ስላረፈ መንበረ መንግሥቱን የወረሰው ልጁ ኮንስታንቲዩስ 2ኛ አርዮስንና ትምህርቱን የሚደግፍ ስለነበረ ቅዱስ አትናቴዎስን ከእስክንድርያ መንበረ ፓትርያርክ አባርሮ የቀጰዶቅያ ሰው የነበረውን አርዮሳዊ ጊዮርጊስን በቅዱስ አትናቴዎስ መንበር ሾመው ። እንደገናም በአክሱም መንበር የተቀመጠውን ቅዱስ ፍሬምናጦስን ለማባረርና ሌላ አርዮሳዊ ጳጳስ ለመተካት በነበረው ዕቅድ መሠረት ንጉሡ ኮንስታንቲዮስ 2ኛ ለኢትዮጵያ ነገሥታት ለአብርሀና አጽብሐ (በፊት ኢዛናና ሲዛና) ደብዳቤ ጻፈ ፣ በሕንድ አገር ሶኮትራ በተባለችው ከተማ የተወለደ ቴዎፍሎስ የተባለ ሕንዳዊ ቄስ ንጉሡ የጻፈውን ደብዳቤ ለነገሥታቱ ለአብርሀና አጽብሐ እንዲያደርስ ወደ አክሱም ተላከ ።

ለነገሥታቱ የተላከው መልእክትም ሙሉ ቃል እንዲህ የሚል ነበር።

«ቪክቶሪዮስ ኮንስታንቲዮስ ማክሲሞስ አውግስጦስ ለአብርሃና አጽብሐ (ኢዛናና ሲዛና) እግዚአብሔር የሰጠን ትምህርትና ማስተዋል ለሁሉም እውነትንና ጽድቅን ለሚፈልግ ሁሉ እንዲዳረስ ስመኝ በእናንተና በሮማውያንም ቤተ ክርስቲያን መካከል አንድነት እንዲኖር ይገባል ። ከሹመቱ የተሻረው ብዙ ሺህ ክስ ቀርቦበት መመለስ ያቃተው አትናቴዎስ ፍሬምናጦስን ልኮአልና አሁን በቶሎ ፍሬምናጦስን መልሳችሁ ለተከበረው ጳጳስ ለጊዮርጊስና በዚያም ላሉት ቀሳውስት ላኩትና የእርሱን ነገር እነርሱ ይጨርሱት ። የአባ አትናቴዎስን ሥራ ግን ከእናንተ በቀር አገር ሁሉ አውቆ አላስጠጋም ስላለው በእናንተ ዘንድ መጠጊያ ይፈልጋል ። ፍሬምናጦስ ግን ከልቡ ጳጳስ መሆን ከፈለገ የሕይወቱን ታሪክ ለቀሳውስቱ ገልጦ የቤተ ክህነትን ሕግና ሥርዐት በደንብ ፈጸሚ መሆኑ በእነዚያ ዘንድ ከታወቀ ተመልሶ እንደገና ጳጳስ መሆን ይችላል ። ያለዚያ ግን እንደ ለፍላፊው እንደ አትናቴዎስ ከሕግ የሚሸሽ ሆኖ ወደ አክሱም የመጣና ሹመቱን የያዘ እንደሆነ እናንተንም ቤተ ክርስቲያናችሁንም እንዳያበላሽና ሁከት እንዳይፈጠር ያስፈልጋል ። እኔ ግን እንደሚመስለኝ ፍሬምናጦስ ወደ እስክንድርያ ተመልሶ በጣም ከተከበረው ጳጳስ (ፓፓ)

www.zeyeneta.com

ጊዮርጊስና ከፍ ካሉት ሊቃውንት ጋር ተገናኝቶ የቤተ ክህነትን ሕግና ትምህርት ከተረዳ በኋላ ወደ ጵጵስና ስፍራው ሊመለስ ይችላል» የሚል ነበር ። ነገሥታቱ አብርሀና አጽብሐ ግን ለኒቅያ ጉባኤ ውሳኔና ለቅዱስ አትናቴዎስ ትምህርት ያላቸውን ሙሉ ድጋፍ በመግለጥ የኮንስታንቲ የስን አሳብ ሳይቀበሉት ቀርተዋል ። መልእክቱን ይዞ ወደ አክሱም የመጣው ቴዎፍሎስም የተላከበት ጉዳይ ውጤት አልባ ስለሆነበት በመጣበት መንገድ ተመልሶ ሄዶአል ። በዚህ ጊዜ ቅዱስ አትናቴዎስ ከነበረበት የስደት ቦታ ሆኖ የኢትዮጵያ ነገሥታት አብርሀና አጽብሐ የወሰዱትን አስደናቂ አቋም ስለ ሰማ ካለበት ሆኖ ለአብርሀና አጽብሐ የምስጋና ደብዳቤ እንደ ጻፈ ይነገራል ።

ቅዱስ ፍሬምናጦስ ከነገሥታቱ ከአብርሀና አጽብሐ ፣ እንዲሁም ከሕዝቡ ጋር በመሆን በአክሱም ባለ 13 መቅደስ በጽዮን ማርያም ስም የሚጠራ ትልቅ ቤተ ክርስቲያን (ካቴድራል) አሠራ ። እንደዚሁም በየቦታውና በየአውራጃው ብዙ አብያተ ክርስቲያናት እንዲታነጹ አድርጎአል ። ቅዱስ ፍሬምናጦስ ያለአንዳች ችግር ሐዋርያዊ ተልእኮውን ሲያከናውን ቆይቶ በ380 ዓ·ም በሰላም ዐረፈ ዕረፍቱም ሐምሌ 26 ቀን ነው ።

ምዕራፍ ፶፫

የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የምትቀበላቸው ዓለም አቀፍ ጉባኤዎች

የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በመንበረ ጵጵስና ከታወቀችበት ከ330 ዓ·ም ጀምሮ ከጥንታውያን አብያተ ክርስቲያናት አንድዋ ሆና ሐዋርያዊ ሥራዋን እያከናወነች እስካለንበት ዘመን ደርሳለች። በእምነት በኩልም ቀደም ሲል ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ፣ ቀጥሎም ሐዋርያው ቅዱስ ማቴዎስና ሌሎችም ሐዋርያት ያስተማሩትን ትምህርት መሠረት በማድረግ በሦስቱ ጉባኤዎች ማለት በኒቅያ በ325 ዓ·ም ፣ በቁስጥንጥንያ በ381 ዓ·ም እና በኤፌሶን በ431 ዓ·ም የተወሰነውን የሃይማኖትና የቀኖና ውሳኔ ተቀብላ ስታስተምርና እግዚአብሔርን ስታገለግል ትገኛለች ።

www.zeyeneta.com

1ኛ· በኒቅያ በ325 ዓ·ም· የተደረገው ዓለም አቀፍ ጉባኤ

እንደሚታወቀው የኒቅያ ጉባኤ የተጠራው የአርዮስን ክህደት ለመቃወም ነው ። አርዮስ ለስህተቱ መነሻ ካደረጋቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ዋናው ከመጽሐፈ ምሳሌ ምዕራፍ 8·22 ላይ «ጥቤ ጥበብ እግዚአብሔር ፈጠረኒ ቀዳሜ ኩሉ ተግባሩ እምቅድመ ይሣርር ዓለመ» ማለት እግዚአብሔር አስቀድሞ ዓለማትን ሳይፈጥር ፈጠረኝ ያለውን ነጠላ ትርጉም መሠረታዊ መነሻ በማድረግ "ወልድ ፍጡር ነው" እያለ ማስተማር ጀመረ ።

የአርዮስ ትምህርት ከግኖስቲኮች ፡ ከሉቅያኖስና ከመሳሰሉት የአንጾኪያ መናፍቃን የተወረሰ መሆኑን ማስታወስ ይገባል ።

ከአርዮስ የክህደት ትምህርት መካከል እንዲህ የሚል ነበር ። ጥበብ ወልድ ያልነበረበት ጊዜ ነበር ፡ ያልነበረበት ሰዓት ነበረ ··· እያለ ወልድን ፍጡር ለማሰኘት ትክክል ያልሆነ ጥቅስ ይጠቅስ ነበር ።

በዚህ አኳኋን አርዮስ አንዳንዶችን ማሳሳት ስለጀመረ የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳሳት እለእስክንድሮስ አርዮስ ከክህደት ትምህርቱ እንዲመለስ ብዙ ጥሮ ነበር ፡ ነገር ግን አርዮስ ሊመለስ አልቻለም ። ይልቁንም ከ320 ዓ·ም ጀምሮ የክህደት ትምህርቱን በይፋ በየከተማው እየተዘዋወረ ማስፋፋት ጀመረ ። በዚህ ጊዜ ሊቀ ጳጳሳቱ እለ እስክንድሮስ አንድ መቶ የሚያህሉ ኤጲስ ቆጶሳትን ሰብስቦ የአርዮስን የክህደት ትምህርት ገለጸላቸው ፡ ከዚህም ጋር አርዮስ የክህደት ትምህርቱን እንዲተው ፡ በቤተ ክርስቲያን ብጥብጥ እንዳይነሣ ፡ ነገሩ በሰላም እንዲያልቅ ብሎ አርዮስን ብዙ ጊዜ ለማግባባት እንደሞከረ ለጉባኤው አስረድቶአል ። ጉባኤውም የአርዮስን የክህደት ትምህርት ከመረመረና ከክህደቱም የማይመለስ መሆኑን ከተረዳ በኋላ በአንድ ድምፅ አወገዘው ።

ጉዳዩ በእስክንድርያ ሀብትንና ብጥብጥን እያስከተለ በመሄዱ ንጉሡ ቆስጠንጢኖስ በጣም ያሳሰቸና ወዳጁ የነበረውን የአስፔይኑን ኤጲስ ቆጶስ ሆሴዮስን ወደ እስክንድርያ ላከው ፡ ኤጲስ ቆጶስ ሆሴዮስም በእስክንድርያ ከእለ እስክንድሮስና ከሌሎቹ ኤጲስ ቆጶሳት ጋር ሲወያይ ሰንብቶ ወደ ንጉሡ ተመለሰ ። ጉዳዩም በሽምግልና መፈታት እንደማ

www.zeyeneta.com

ይችል ለንጉሡ አስረዳው ፡ በዚህ ጊዜ ንጉሡ ቆስጠንጢኖስ ጉባኤ እንዲደረግ አዋጅ አስነገረ ። የእስክንድርያው እለ እስክንድሮስም ጉዳዩ በጉባኤ እንዲታይ ለንጉሥ ቆስጠንጢኖስ በጽሑፍ አሳውቆ ነበር ። በዚህ መሠረት ጉባኤው በኒቂያ ከተማ በግንቦት ወር 325 ዓ.ም. ተከፈተ። በጉባኤው በርከት ያሉ ኤጲስ ቆጶሳትና ረዳቶቻቸው ተገኝተዋል ። ጉባኤው ከግንቦት 20 እስከ ሰኔ 13 ቀን የመግቢያና የአጀንዳ ዝግጅት ሲያደርግ ቆይቶ በይፋ በንጉሡ ንግግር ተከፈተ ። በጉባኤው ከ2000 በላይ ተሳታፊዎች እንደነበሩ በታሪክ ተመዝግቦአል ።

ጉባኤው በመጀመሪያ የተነጋገረበት ርእስ ፡

- የአርዮስ የክህደት ትምህርት ፡
- በቅዱስ እለ እስክንድሮስ ሰብሳቢነት የእስክንድርያው ሲኖዶስ የአርዮስን ትምህርት በማስተባበልና በመቃወም የሰጠው ውሳኔ፡

ጉባኤው በእነዚህ ጉዳዮች ላይ በሰፊው ተወያይቱ አርዮስና ተከታዮቹ የወልድን የባሕርይ አምላክነት በመቃወም የጠቀሱአቸውን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች በተሳሳተ መንገድ የተጠቀሱ መሆኑን ለአርዮስ አስረድቱአል ። በዚህም መሠረት ከመጽሐፈ ምሳሌ 8፡22 የተጠቀሰው ጥቅስ ቃለ እግዚአብሔር ወልድ ዓለም ከመፈጠሩ በፊት ከአብ ባሕርይ መገኘቱን (መወለዱን) እንጂ እንደ ፍጡራን ሁሉ ያልተፈጠረ መሆኑን አርዮስ እንዲረዳው ለማድረግ የጉባኤው አባቶች ብዙ ደክመዋል ። ከቅዱሳት መጻሕፍት እየጠቀሱ ። ቃለ እግዘአብሔር ወልድ የባሕርይ አምላክ መሆኑን አስረድተውታል ። ወልድ የአብ የባሕርይ ልጅ እንጂ ያልተፈጠረ መሆኑን በማስረዳት የተጠቀሱትም (ዮሐ. 1 ፡ 1—14 ፡ 10፡30 ፡ ሮሜ. 9፡5 ፡ 1ኛ ዮሐ. 5፡20) እና እነዚህን የመሰሉትም ናቸው ።

አርዮስ ግን ከክህደት ትምህርቱ ሊመለስ ስላልፈለገ 318 ቅዱሳን አበው (ኤጲስ ቆጶሳት) በመንፈስ ቅዱስ «እንደ አንድ ልብ መካሪ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ» በመሆን አርዮስንና ትምህርቱን አውግዘው የወልድን አምላክነት የሚገልጽ አንቀጸ ሃይማኖትን በውሳኔ አጸደቁ ።

www.zeyeneta.com
ከዚህም ጋር ቤተ ክርስቲያን የምትመራበትን ሥርዐተ ቀኖና ወሰኑ ። 318 ቅዱሳን አበው በ325 ዓ·ም· በኒቅያ የወሰኑት አንቀጸ ሃይማኖት (ጸሎተ ሃይማኖት) ከዚህ የሚከተለው ነው ።

«ሁሉን በያዘ ሰማያትንና ምድርን ፣ የሚታየውንና የማይታየውን ፍጥረት ሁሉ በፈጠረ በአንድ አምላክ በእግዚአብሔር አብ እናምናለን ። ከአብ በተወለደ ተቀዳሚ ተከታይ በሌለው በአንድ ጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እናምናለን ። ዓለም ሳይፈጠር ከእርሱ ጋር በነበረ ፣ ከብርሃን የተገኘ ብርሃን ከእውነተኛ አምላክ የተገኘ እውነተኛ አምላክ ፣ የተወለደ እንጂ ያልተፈጠረ ፣ ከአብ ጋር በመለኮቱ (በባሕርይ) የተካከለ ፣ ሁሉ በእርሱ የተፈጠረ ፣ ያለ እርሱ ምንም ምን የተፈጠረ የሌለ ፣ በሰማይም በምድርም ያለው ቢሆን ፣ ስለ እኛ ስለ ሰዎች ስለ መዳናችን ከሰማይ ወረደ ፣ በመንፈስ ቅዱስ ከቅድስት ድንግል ማርያም ፈጽሞ ሰው ሆነ ፣ በጰንጤናዊው በጲላጦስ ዘመን ስለእኛ ተሰቀለ ፣ ተመመ ፣ ሞተ ፣ ተቀበረ ፣ በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ተለይቶ ተነሣ ፣ በቅዱሳት መጻሕፍት እንደተጻፈ በምስጋና ወደ ሰማይ ዐረገ ፣ በሕያዋንና በሙታን ይፈርድ ዘንድ ዳግመኛ በምስጋና ይመጣል ለመንግሥቱም ፍጻሜ የለውም» ።

2ኛ· <u>የቁስጥንጥንያው ጉባኤ ፡</u>

ቴዎዶስዮስ ቀዳማዊ ወይም ዘየዐቢ በቁስጥንጥንያ በ379 ዓ·ም በነገሠ ጊዜ ጢሞቴዎስ ዘአልዐ ጥሪት የእስክንድርያ ፓትርያርክ ሆኖ ተሾሞ ነበር ። በሮምም ዳማሶስ በተሾመበት ወቅት የቁስጥንጥንያ ሊቀ ጳጳስ የነበረው መቅዶንዮስ የመንፈስ ቅዱስን አምላክነት በመካድ መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ ጋር በባሕርይ በመለኮት አንድ አይደለም። ... መንፈስ ቅዱስ ከአብ ከሠረፀ አብና ወልድም መንፈስ ቅዱስን ከላኩትና መልእክተኛ ከሆነ ፣ ከእነርሱ ጋር ትክክል አይደለም ፣ ከእነርሱ በታች (ሕፀፅ) ነው እያለ ማስተማር ጀመረ ። ይህ የክህደት ትምህርት በምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት መዛመት ስለጀመረ አንድ መቶ ሃምሳ (150) ኤጲስ ቆጶሳት በቁስጥንጥንያ በ381 ዓ·ም· ተሰብስበው ዐቢይ ጉባኤ አደረጉ ። በዚህ ጉባኤ ከብሉያትና ከሐዲሳት እየጠቀሱ መንፈስ ቅዱስ ከአብ ቢሠርፅም ከአብና ከወልድ ጋር በባሕርይ ፡

www.zeyeneta.com

በመለኮት አንድ መሆኑን ፣ በዕሪናም ከእነሱ ጋር ትክክል መሆኑን (መዝ· 33፡6፣ ኢሳ· 6፡3 ፣ የሐዋ· ሥራ 28፡25) በሰፊው አትተው የመንፈስ ቅዱስን አምላክነት የሚያረጋግጥ ውሳኔ በማጽደቅ መቅዶንዮስንና ትምህርቱን በጥብቅ አውግዘዋል።

በኒቅያ 318 ቅዱሳን አበው የወሰኑትንም አንቀጸ ሃይማኖት በማጠናከር የመንፈስ ቅዱስን አምላክነት በሚገባ ገልጸው «ከአብ በሠረፀ ፣ ጌታ ፣ ሕይወት ሰጭ በሚሆን በመንፈስ ቅዱስ እናምናለን ፣ ከአብና ከወልድ ጋር ጋር በአንድነት እንሰግድለታለን እርሱም በነቢያት አድሮ የተናገረ…» ብለው በኒቅያ የሃይማኖት ውሳኔ ላይ ጨምረው ወሰኑ ። ይኸውም ከዚህ በታች የተመለከተው ነው ።

«ጌታ ፣ ሕይወት ሰጭ በሚሆን ከአብ በሠረፀ በመንፈስ ቅዱስ እናምናለን ፣ እንሰግድለትም እናመሰግነውም ዘንድ ከአብና ከወልድ ጋር በነቢያት የተናገረ ። ከሁሉ በላይ በምትሆን ሐዋርያት በሰበሰብዋት በአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እናምናለን ። ንጠኢት በሚሠረይባት በአንዲት ጥምቀት እናምናለን ። የሙታንን መነሣትና የሚመጣውን ዘላለማዊ ሕይወት ተስፋ እናደርጋለን» በማለት መዶ አምጣው (150) አበው በአንድ ድምፅ ተስማምተው ወሰኑ ።

ከዚያን ጊዜ ጀምሮም የኒቅያና ቁስጥንጥንያ አንቀጸ ሃይማኖት በሚል ስም ታውቆ በሁሉም አብያተ ክርስቲያናት በዘወትር ጸሎትና በጸሎተ ቅዳሴ ጊዜ በጎብረት እንዲጸለይ ተደርጓል ።

3ኛ· የኤፌሶን ጉባኤ

ቴዎዶስዮስ 2ኛ በቁስጥንጥንያ ነግሦ ሳለ ፣ በእስክንድርያ ቅዱስ ቄርሎስ በ412 ዓ/ም የእስክንድርያ ፓትርያርክ ሆኖ ተሾሞ ነበር ።

በሮም ደግሞ ሰለስቲን ቀዳማዊ የሮምን መንበር ወርሶ በነበረበት ወቅት ፣ የአንጾኪያ ተወላጅ የሆነው የጠርሴሱ ኤጲስ ቆጶስ የዲያድርስ ተማሪ የነበረው ንስጥሮስ በ427 ዓ/ም የቁስንጥንጥንያ ሊቀ ጳጳስ ሆኖ ተሾመ ። የቁስጥንጥንያ ሊቀ ጳጳስ ሆኖ በተሾመበት ዓመት በቁስጥንጥንያ የአርዮስንና የመቅዶንዮስን ፣ እንደዚሁም የአቡሊናርዮስን የክህደት ትምህርት የሚደግፉ የተለያዩ መናፍቃን በብዛት ነበሩ ፣ በንስጥሮስ ጠያቂነት መናፍቃኑን ከዋናው ከተማ ጠራርጎ የሚያስወጣ ፣ ትምህርታቸ

www.zeyeneta.com

ውንም የሚያወግዝ በንጉሡ የተፈረመ ደብዳቤ በአዋጅ እንዲሰራጭ ተደረገ ። ይህ በሆነ በዓመቱ በዚያ ሰበብ የንስጥሮስ ጸሐፊ የነበረው አንስጣስዮስ የተባለ መነኩሴ በቁስጥንጥንያ ከተማ በአንድ ትልቅ ቤተ ክርስቲያን (ካቴድራል) ቃለ ስብከት ሲያሰማ እንዲህ አለ ፡ «ድንግል ማርያም ክርስቶስን በንጽሕናና በድንግልና መውለድዋ የታመነ ነው ፡ ነገር ግን እስዋን ወላዲተ እግዚአብሔር ወይም እመ እግዚአብሔር (ቴዎቶኮስ) ብሎ መጥራት አይገባም ምክንያቱም አምላክ ከሰው ሊወለድ አይችልምና ። ነገር ግን እስዋ በእውነት ፡ ወላዲተ ክርስቶስ ወላዲተ ሰብእ፡ መሆንዋን እናምናለን ...» በማለት አስተማረ ። በዚህ ጊዜ ይህን አዲስ ትምህርት የሰማ ሁሉ ተደናገጠ ፡ ተቃውሞም ከየቦታው ተነሣ ንስጥሮስ መነኩሴው ያስተማረውን ክህደት እንዲያስተካክል ሕዝቡ ጠየቀው ፡ ንስጥሮስ ግን የራሱ ትምህርት (ከእሱ የተገኘ ትምህርት) መሆኑን ያውቃልና የሕዝቡን ጥያቄ አልተቀበለም እንዲያውም ከዚያን ሰዓት ጀምሮ ንስጥሮስ ራሱ የክርስቶስን ወልድ ዋሕድ መሆንና የባሕርይ አምላክነቱን እየነቀፈ «ከማርያም የተወለደው መለኮት ወይም ቃለ እግዚአብሔር በጸጋ የተዋሐደው ኢየሱስ ነው ፡ እሱም ክርስቶስ ተባለ ፡ ስለዚህ ድንግል ማርያምን ወላዲተ አምላክ ብሎ መጥራት ሐሰት ነው ። እስዋ በእውነት ወላዲተ ክርስቶስ ናት እንጂ ወላዲተ እግዚአብሔር ተብላ መጠራት አይገባትም ...» እያለ በቃልም በጽሑፍም ትምህርቱን ማሰራጨት ጀመረ ። ከዚህም የተነሣ የንስጥሮስ የክህደት ትምህርት በየቦታው ተሰማ ፡ በተለይም የእስክንድርያው ፓትርያርክ ቅዱስ ቄርሎስ ይህን የክህደት ትምህርት ሰምቶ በየካቲት ወር 430 ዓ/ም ለመጀመሪያ ጊዜ ምክር አዘል ደብዳቤ ለንስጥሮስ ጻፈለት ፡ በዚያውም ለሮሙ ፓፓና ለሌሎችም በምሥራቅና በምዕራብ ለሚገኙ ሊቃነ ጳጳሳት የጉዳዩን አሳሳቢነት ገልጾ ጻፈላቸው ። ለንጉሡ ለቴዎድሮስም ጉዳዩን በጽሑፍ አሳወቀ ። ንስጥሮስም በበኩሉ ቅዱስ ቄርሎስ ለጻፈላቸው ክፍሎች ሁሉ የተቃውሞ ደብዳቤ ጻፈ ። በሀገረ ስብከቱ ውስጥ ትምህርቱን የተቃወሙትን ቀሳውስትና መነኰሳት ከክህነት ከአገልግሎት አግዶ ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዳይገቡ አስከለከላቸው እነሱም ወደ ንጉሡና ወደ ቅዱስ ቄርሎስ አቤቱታቸውን ጻፉ ።

ከዚህ በኋላ ቅዱስ ቄርሎስ የንስጥሮስን ትምህርት አጥብቆ

www.zeyeneta.com

በማውገዝ ራሱን ንስጥሮስን ሳያወግዝ ጠንካራ ደብዳቤ ለንስጥሮስ ጻፈለት ፡ ግልባጩንም ለቤተ መንግሥቱና ለሚመለከታቸው ሊቃነ ጳጳሳትና ለገዳማትም ሄዶር ላከላቸው ። በዚህ ሁኔታ ቅዱስ ቄርሎስና ንስጥሮስ ደብዳቤ እየተጻጻፉ እስከ አንድ ዓመት ቆዩ ።

ንስጥሮስ የክህደት ትምህርቱን ከማስፋፋትና ከማጠናከር በቀር ከስህተት የማይመለስ ሆኖ በመገኘቱ ንጉሡ ፡ የሮም ፓፓ ሰለሰቲን አንደኛ ፡ ሌሎቹም በምሥራቅም በምዕራብም የነበሩ የታወቁ ሊቃነ ጳጳሳት የንስጥሮስን ጉዳይ ለማየት ባስቸኳይ ጉባኤ እንዲደረግ ተስማሙ ። በዚህ ምክንያት በ431 ዓ.ም. በኤፌሶን ከተማ ጉባኤ እንዲደረግ ተወሰነ ። 200 የሚያህሉ ሊቃነ ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጶሳት በኤፌሶን ተሰበሰቡ ፡ ቅዱስ ቄርሎስ የጉባኤው ሊቀ መንበር እንዲሆን ተመረጠ ። የአንጾኪያው ሊቀ ጳጳስ ዮሐንስ በሥሩ የሚገኙትን ኤጲስ ቆጶሳት ይዞ እንዲመጣ ተጠርቶ ነበር ፡ ነገር ግን የንስጥሮስ ዋና ደጋፊ ስለነበር በሰዓቱ አልመጣም ። እሱ እስኪመጣ ድረስ ሁለት ሳምንት ሙሉ ተጠበቀ ፡ ነገር ግን በመንገድ ልዩ ልዩ ችግር እንደገጠመው እውነት ባልሆነ ቃል ልዩ ልዩ ምክንያት እየፈጠረና መልእክተኛ እየላከ ብዙ ቀን ቢጠበቅም ሊመጣ አልቻለም ። በዚህ ጊዜ ጉባኤው እንዲጀመር ተወሰነ ። ንስጥሮስ በጉባኤው እንዲቀ ርብና ጉዳዩን እንዲያስረዳ ከጉባኤው ጥሪ ደረሰው ፡ ሦስት ጊዜ ተጠርቶ ለመቅረብ ፈቃደኛ ሆኖ ስላልተገኘ ጉባኤው እሱ በሌለበት ስብሰባውን ጀመረ ።

<u>በመጀመሪያ</u> ንስጥሮስ የጻፋቸው የክህደት ትምህርቱን የያዙ ደብዳቤዎች ቀርበው ተነበቡ ።

<u>ሁለተኛ</u>፡- ቅዱስ ቄርሎስ የንስጥሮስን ክህደት በማጋለጥ የጻፋቸው ደብዳቤዎችና 12 የውግዘት አንቀጾችን የያዘ መልእክት አንድ በአንድ ለጉባኤው ቀርበው ተነበቡ ። በዚህ መሠረት የንስጥሮስ ትምህርት ከቅድስት ቤተ ክርስቲያን ትምህርት ጋር የሚቃረን የክህደት ትምህርት መሆኑ በጉባኤው ተረጋገጠ ። የቅዱስ ቄርሎስ መልእክታት ግን ከቅዱሳት መጻሕፍትና ከቅዱሳን አበው ትምህርት ጋር አንድ ሆነው ስለተገኙ ጉባኤው በአንድ ድምፅ ተቀበላቸው ። ንስጥሮስ ድንግል ማርያምን ወላዲተ አምላክ ተብላ መጠራትዋን በመቃወም ያሠራጨውን የክህደት ትምህርት

www.zeyeneta.com

ጉባኤው በጽኑ በማውገዝ ከቅድስት ድንግል ማርያም የተወለደው ራሱ አምላክ መሆኑን በማረጋገጥ ድንግል ማርያም በአማን ወላዲተ አምላክ መሆንዋን በአንድ ድምፅ ተስማምቶ ወስኖአል ። ከዚህም ጋር ቅዱስ ቄርሎስ ለንስጥሮስ ከጻፈው ከሁለተኛው መልእክት፡-

1. «ንጽሕት ድንግል እግዚአብሔር ቃልን በሥጋ እንደ ወለደች እናምናለን» ሲል ያስተማረውን ፣ በተጨማሪም ፣
2. ይህ ቅዱስ አባት ለምሥራቃውያን ጳጳሳት ከጻፈው መልእክቱ «ኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክ ሲሆን እግዚአብሔርን ከወለደች ከቅድስት ድንግል ማርያም በነሣው በነፍስ በሥጋ እንደ እኛ ሰው መሆኑን ፣ እሱም በተዋሕዶ አንድ አካል አንድ ባሕርይ» መሆኑን በመግለጽ የጻፈውን ፣
3. በዚያው መልእክቱ «ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ እንደሆነች ማመን ይረባል ይጠቅማል ፣ እርስዋ ሰውን የወለደች ናት ትባል ዘንድ አይገባም ፈጽሞ በጎ አይደለም» ሲል ያስተማረውን ።
4. በዚያው መልእክቱ «ከልባችን ባነቃነው ነገር ተዋሕዶን ልንነቅፍ አይገባም ፣ ቅድስት ድንግልንም እግዚአብሔርን የወለደች አይደለችም አንበል» በማለት ያስተማረውን የጉባኤው ተሳታፊዎች ቅዱሳን ሊቃነ ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጶሳት በንባብ ሰምተው በአንድ ድምፅ አጽድቀዋል ። ሁለት አካልና ሁለት ባሕርይ የሚል ትምህርቱንም አውግዘዋል ።

ንስጥሮስንም ከምእመናን እንዲለይ አድርገዋል ። የዚህ ዐቢይ ጉባኤ ውሳኔም በንጉሡ በቴዎዶስዮስ ፊርማ በየቦታው እንዲ ሰራጭ ተደርጎአል ። ከዚህም ጋር የሦስተኛው ዓለም አቀፍ ጉባኤ አበው ሊቃውንት የቤተ ክርስቲያንን አስተዳደር በሚመ ለከት ሕገ ቀኖናን አጽድቀዋል ።

በኂቅያ ፣ በቁስጥንጥንያና በኤፌሶን የተደረጉ ዓለም አቀፍ ጉባኤዎች የጥንትዋ ቤተ ክርስቲያን በነገረ መለኮትና በቀኖና ሳትከፈል በአንድ የእምነት ትምህርትና በአንድ ዓይነት ሥርዓተ ቀኖና ሳለች የተደረጉ በመሆናቸው በእነዚህ ጉባኤዎች የተወሰነውን የእምነትና የቀኖና ውሳኔ ሁሉም አብያተ ክርስቲያናት ይቀበሉታል ። ጉባኤዎቹንም

www.zeyeneta.com

ከፍ አድርገው ያከብሩአቸዋል ። በተለይም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አራቱ አኃት አብያተ ክርስቲያናት ማለት የግብፅ ኦርቶዶክስ ፣ የሶርያ ኦርቶዶክስ ፣ የአርመን ሐዋርያዊትና የሕንድ ማላንካራ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት የሚመሩት በሐዋርያት ትምህርትና በእነዚህ ጉባኤዎች በተወሰነው እምነትና ቀኖና ስለሆነ ሦስቱንም ጉባኤዎች ሙሉ በሙሉ ይቀበሉአቸዋል ።

በነዚህ ሦስት ጉባኤዎች በኒቅያ 318 ፣ በቁስጥንጥንያ 150 ፣ በኤፌሶን 200 ቅዱሳን አበው የወሰኗቸውን ውሳኔዎች የሠሩአቸውን ሥርዓቶችና የደነገጓቸውን ቀኖናዎች ሁሉ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተቀብላ ስትመራባቸውና ስትሠራባቸው ኑራለች ፣ አሁንም ትመራባቸዋለች ፣ ትሠራባቸዋለችም ።

ያወገዙአቸውን መናፍቃንና ተከታዮቻቸውንም ሁሉ አውግዛለች። ታወግዛለችም ። እንደዚሁም በሁለተኛው ጉባኤ በቁስጥንጥንያ የተወገዘውን አቡሊናርዮስ ከኤፌሶን ጉባኤ 431 ዓ·ም· በኋላ የተወገዘውን አውጣኪንና ትምህርታቸውን አውግዛለች ታወግዛለችም ።

ከሦስተኛው ጉባኤ ማለት ከኤፌሶን ጉባኤ በኋላ ተደረጉ የሚባሉትን ጉባኤዎች የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አትቀበልም ። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳትሆን አኃት አብያተ ክርስቲያናት ማለት የግብጽ ፣ የሶርያ የሕንድና የአርማንያ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናትም አይቀበሏቸውም ።

www.zeyeneta.com

ምዕራፍ ፳፬

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የውጭ ግንኙነት ከኬልቄዶን ጉባኤ በኋላ

ተስዓቱ ቅዱሳን

ከመጀመሪያው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፯፭ኛ አባ ሰላማ በኋላ በሁለተኛው ፯፭ኛ በአባ ሚናስ ጊዜ ዘጠኙ ቅዱሳን በ480 ዓ.ም. ወደ ኢትዮጵያ መጡ ።

እነርሱም የሚከተሉት ናቸው ።

የቅዱሳኑ ስም	የመጡበት አገር
1ኛ. አባ አሌፍ	ቂሣርያ
2ኛ. ” አረጋዊ	ቁስጥንጥንያ
3ኛ. ” አፍጼ	ታናሹ እስያ
4ኛ. ” ሊቃኖስ	ቁስጥንጥንያ
5ኛ. ” ገሪማ	”
6ኛ. ” ጉባ	ኪልቅያ
7ኛ. ” ይምዓታ	ቆስያ
8ኛ. ” ጰንጠሌዎን	ቁስጥንጥንያ
9ኛ. ” ጽሕማ	አንጾኪያ

እነዚህ ቅዱሳን አበው ወደ ኢትዮጵያ የመጡበት ዐቢይ ምክንያት የተወገዘውን የኬልቄዶንን ጉባኤና ውሳኔውን አንቀበልም በማለታቸውና በቢዛንታይን ነገሥታት ስቃይ ስለጸናባቸው ነው ፣ ወደ ኢትዮጵያም መጥተው በሰሜን ክፍለ ሀገራችን ተቀመጡ ። የኢትዮጵያ መንግሥትና ሕዝበ ክርስቲያኑ ሲወርድ ሲዋረድ በመጣው ደግነቱና እንግዳ ተቀባይነቱ በፍቅር ስለተቀበላቸው ቅዱሳኑ በዓት አጽንተው እስከ ዛሬ በስማቸው የሚጠሩትን ገዳማት አቅንተው ወንጌለ መንግሥተ ሰማያትን፣ ሥርዓተ ገዳምንና ምንኩስናን እያስተማሩ ኑረዋል ። የሀገሪቱን የግዕዝ

www.zeyeneta.com

ቋንቋ ተምረውና አውቀው ከኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ጋር ሆነው አያሌ መጻሕፍትን ከሱርስትና ከዕርዕ መልሰዋል ። ተስዓቱ ቅዱሳን ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ጥንካሬ ከፍተኛ ተልእኮን ፈጽመው ስለዐረፉ ቤተ ክርስቲያናችን ቅዱሳን ብላ ታከብራቸዋለች ። በስማቸውም ቤተክርስቲያን ሠርታላቸዋለች ።

ለ) ዐፄ ካሌብ

ከዐፄ ካሌብ ዘመን በፊት ጀምሮ በደቡብ የዐረብ ግዛት ሁሉ ክርስትና ተዳርሶ ስለነበር በኢትዮጵያና በዐረብ አገሮች መካከል የጠበቀ ግንኙነት ነበር ። በ70 ዓ.ም. ጥፋስ ኢየሩሳሌምን በአጠፋበት ጊዜ ተሰደው ደቡብ ዐረብ (የመን) የገቡ አይሁድ ፊንሐስ በተባለው አይሁዳዊ ሰው እየተመሩ በ6ኛው መቶ ዘመን መጀመሪያ ላይ ከ485 – 515 ዓ.ም. በሀገረ ናግራን በነበሩ ክርስቲያኖች ላይ ከባድ ሥቃይ አደረሱባቸው ። ሥቃዩ የደረሰባቸው ምእመናንም በቁስጥንጥንያ በእስክንድርያና በአክሱም ለሚገኙ የሃይማኖት ወንድሞቻቸው አሰሙ ። ይህም የዕልቂት ዜና የክርስቲያን ኢትዮጵያን መንግሥትና ሕዝብ እጅግ በጣም አሳዘነ ።

አርቶዶክሳዊው የኢትዮጵያ ንጉሥ ዐፄ ካሌብ ከልብ አዝነው የሀገረ ናግራን ክርስቲያኖችን እንዴት እንደሚረዱ ይገልጽላቸው ዘንድ ወደ ፈጣሪያቸው ጸሎተ ምሕላ ያዙ ። የቁስጥንጥንያው ንጉሥ ዩስጢኖስም እልቂቱ ያሳዘነው መሆኑን ገልጦ ለእስክንድርያው ሊቀ ጳጳስ ለአባ ጢሞቴዎስ 3ኛ መልእክት ላከ ። አባ ጢሞቴዎስ 3ኛም ስለ ሀገረ ናግራን ክርስቲያኖች መታደግ ለዐፄ ካሌብ መልእክት ላኩ ። የአቡነ ጢሞቴዎስ 3ኛ መልእክት በደረሳቸው ጊዜ የእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑን ተረድተው ምን ንጋሪት ክተት ሠራዊት በማለት ወደ የመን ዘመቱ ።

ከዚያም ግፈኛውን ፊንሐስን ከነሠራዊቱ ደምስሰው ፡ የፈረሱ አብያተ ክርስቲያናትን ጠግነው ፡ ሌሎች አዲሶችንም ሠርተው ፡ ከፊንሐስ ሰይፍ የተረፉትን ምእመናንንም አጽናንተውና አረጋግተው ከአሥር ሺ ሠራዊት ጋር የሚጠበቃቸው አብርሀ የሚባል ብልሀ ሰው ሹመው ላቸው ወደ አክሱም ተመለሱ ።

ከዚህ በኋላ ዐፄ ካሌብ መንግሥታቸውን ለልጃቸው ለገብረ መስቀል ለቅቀው ፡ ዘውዳቸውን በነልንታ ለሚገኘው ለኢትዮጵያ ገዳም እንዲሰጥ ላቸው ወደ ኢየሩሳሌም ልከው ለ12 ዓመታት በምናኔ ቆይተውና የአበውን

www.zeyeneta.com

አሠረ ጽድቅ ፊጽመው ስለ ዐረፉ በኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቀኖና ቁጥራቸው ከጻድቃን ነው ። ዕረፍታቸውም ግንቦት 20 ቀን 537 ዓ·ም· ስለሆነ በስንክሳር ይዘከራል ።

የክርስትና ደሴት የሆነችው ኢትዮጵያ ከዐፄ ገብረ መስቀል በኋላ የእስልምና እምነት ተከታዮች ከሆኑ አጎራባች አገሮች መንግሥታት ከሚደርስባት ተጽዕኖ የተነሣ የነበራት የውጭ ግንኙነት እንደበፊቱ የተጠናከረ አልነበረም ።

ሆኖም በየጊዜው ከግብጽ እየተላኩ ከሚመጡት ጳጳሳት ሌላ የቤተ ክርስቲያኒቱን ዝና በመስማት አንዳንድ ቅዱሳን መምጣታቸው አልቀረም። በተቀዳሚነትም ከሚጠቀሱት አንዱ ግብፃዊው አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ናቸው ። አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ በ11ኛው ምእት ዓመት ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ገዳማትን አቅንተው የኖሩና በገድላቸው የታወቁ ታላቅ ጻድቅ ናቸው ።

ምዕራፍ ፲፫

ከኬልቄዶን ጉባኤ በኋላ በክርስትና እምነት የተገኘ ዓለም አቀፍ ዕውቅና

ኢትዮጵያ በክርስትና እምነት ጥንካሬዋ የታወቀች የክርስትና ደሴት እንደነበረችና እንደሆነች ይታወቃል ። ይህም ጥንካሬዋ እንደእነካሌብና ዘርዐ ያዕቆብ ወዘተ· ያሉ ክርስቲያን መሪዎቿ በክርስትና እምነት ንሻነት ዓለም አቀፍ ዕውቅናን ለማግኘት የበቁባት ሀገረ እግዚአብሔር ለመሆን አብቅቷታል ።

እ·አ·አ· በ1145 ክርስቲያን አውሮፓ «ፕሪስተር ጆን· ቂሱ ንጉሥ» ስለሚባል አንድ ንያል ንጉሥ የመኖሩን ዜና ሰማች ። ጊዜው ቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌምን ከእስልምና ተከታዮች ቅኝ ግዛት ነፃ ለማውጣት «የመስቀል ጦርነት» እየተባለ የሚጠራ ውጊያ የሚያካሂድበት ወቅት ነበር ። ንይልን በማስተባበር የጦርነቱ ድል አድራጊ መሆን የሁሉም ክርስቲያን ነገሥታት ምኞትና ፍላጎት ነበረ ፡ የዚህ ንጉሥ መኖር ዜና

www.zeyeneta.com
ሊሰማ የቻለውም ይህን ጎብረት ለማምጣት ይደረግ በነበረ ጥረት መሆኑ ግልጽ ነው ።

ይህ ንጉሥ ለጊዜው የፋርስ ወይም የሕንድ ክርስቲያኖች መሪ እንደሆነ ተገምቶ ነበር ። በኋላ ግን ይህ ንጉሥ በቀናዒነቱ ፕሪስተር ጆን (ቄስ ንጉሥ) የሚል ስያሜ የተሰጠው የክርስቲያን ኢትዮጵያ ንጉሥ መሆኑ ተረጋገጠ ። ዜናው የተሰማው ቀደም ብሎ ቢሆንም ማንነቱ የተረጋገጠው ግን በ14ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ነው ። የንጉሡን ማንነት ለማረጋገጥ የተደጋገመ ሙከራ ከአደረጉት ነገሥታት መካከል አፎንስ ዘአራጎን ዋናው ነበር ። ከዚህ ማረጋገጫ በኋላ ካቶሊካዊው የፖርቹጋል ንጉሥ ከሮማው ፓፓ ጋር በመመካከር ከዚህ ኢትዮጵያዊ ክርስቲያን መንግሥትና ሕዝብ ጋር የቅርብ ግንኙነት ለማድረግ ጥረቱን ቀጠለ ። በተለይ በአፄ ይስሐቅና (1405 1420) በአፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመን (1426–1460) ጥረቱ ከመልካም ፍጻሜ ሊደርስ ተቃርቦ ነበር ። በአስተዳደር ችሎታቸውና ብስለታቸው እጅግ ታዋቂ በነበሩት አያቱ በእቴጌ ዕሌኒ የአፄ በእደ ማርያም ባለቤት ሞግዚትነት ይታገዝ በነበረውና በ12 ዓመቱ በነገሠው ሕፃን ነጋሢ በአፄ ልብነ ድንግል ዘመን ደግሞ የሁለቱ ክርስቲያን አገሮች ግንኙነት ወደ አምባሳደር ልውውጥ ደረጃ ከፍ ስለአለ አርመናዊው ማቴዎስ የኢትዮጵያ መልእክተኛ በመሆን ወደ ሊዝቦን ፖርቱጋል ተላከ ።

አርመናዊው የኢትዮጵያ መልእክተኛ ለመሆን የበቃውም አርመንና ኢትዮጵያ የኬልቄዶንን ጉባኤ የማይቀበሉ የኦርቶዶክሳውያን ሕዝቦች አህጉር በመሆናቸው ሲሆን በተለይ ይህ ሰው በዚያ ዘመን እስከ ኢትዮጵያ ድረስ ዘልቆ በመግባት የንግድ እንቅስቃሴ የሚያደርግና በዚያም ሥራው በቤተ መንግሥት የታወቀ የውጭ ቋንቋ አዋቂ ነጋዴ መሆኑ ለዚህ ባለሚልነት አብቅቶታል ።

በካቶሊካዊት ፖርቹጋል አማካይነት ሮም ከኢትዮጵያ ጋር የበለጠ ትውውቅ ለማድረግና የቅርብ ግንኙነትም ለመፍጠር ጥረት ማድረግ ጀመረች ። ለዚህ ትውውቅ ከፍተኛ ትኩረት የሰጠችውም መላውን የክርስትና ዓለም በካቶሊክ እምነትና በሮሙ ፓፓ የበላይ አመራር ሥር ለማዋል ካላት ጉጉት የተነሣ ነበር ። ከዚህ ምኞት በመነሣት በ15ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የሮም ቤተ ክህነት የኬልቄዶንን ጉባኤ የሚቀበሉና

www.zeyeneta.com

የማይቀበሉ አብያተ ክርስቲያናት መልእክተኞች የሚገኙበት አንድ ዓለም አቀፍ ጉባኤ በፍሎሬንስ በማዘጋጀት ጥሪ አደረገ ። በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በኩል በዚህ ስብሰባ ላይ በመልእክተኝነት የተገኘው በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ገዳማት ማኅበር የተወከለ አንድ መነኩሴ ሲሆን መልእክተኛው ለዚህ ስብሰባ ምንም ዓይነት ድጋፍ ሳይሰጥ በተመልካችነት ብቻ ተገኝቶ መመለሱ ተመዝግቧል ። ይህም የሆነው የስብሰባው መንፈስ የሮሙን ፓፓ የበላይነት ለማንበላረቅ ታስቦ የተዘጋጀ ጉባኤ መሆኑን ስለተገነዘበ ነው ።

በአፄ ልብነ ድንግል ዘመን በኢትዮጵያ የፖርቱጋል አምባሳደር ሆኖ ተልኮ የነበረው ዶርቲ ገልቮ ይጫወት የነበረው የዲፕሎማቲክ ሚና ሁለት ገጽታ ያለው ነበር ።

<u>አንደኛው</u>፡ ንግሥት ዕሌኒና ወጣት ነጋሢ የሆነው ልጅዋ ልብነ ድንግል የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነታቸውን ትተው ወደ ካቶሊክ እንዲመለሱ ሲሆን ፡

<u>ሁለተኛው</u>፡ ደግሞ ፖርቹጋል ከግብፅ ጋር በምታደርገው ጦርነት ኢትዮጵያ ከጐንዋ እንድትሠለፍ ለማድረግ የሚያስችል ወዳጅነት መፍጠር ነበር ።

ኢትዮጵያ በጊዜው የግብፅና የየመን ዐረብ ክርስቲያኖች ደኅንነት ጠባቂ እንደነበረች ስለሚታወቅ በዚህ በኩል የግንኙነት መሳካት ለክርስቲያን ፖርቱጋል በእርግጥ ጠቀሜታ ያለው ነበር ። ይህ እንዲህ ሲሆን በኋላ ለታሪክ መዘክር ጉልህ ሁኖ የተገኘው ግን የመጀመሪያው አንቀጽ ነው ።

ነገሩ በዚህ ሁኔታ ላይ እንዳለ የክርስቲያን ኢትዮጵያና ክርስቲያን አውሮፓ ግንኙነት ያሰጋቸው የእስልምና እምነት ተከታይ አገሮች "ሳይቀድመኝ ልቅደም" በሚል አስተሳሰብ በግራኝ መሐመድ ፊታውራሪነት ኢትዮጵያን መውረር ጽኑዕ ዓላማቸው አድርገው ተነሡ ። ከዚያም ኢትዮጵያውያን የእስልምና እምነት ተከታዮች በክርስቲያኖች ላይ ለጦርነት እንዲነሡ በመገፋፋት የፊለጉትን የወረራ ጦርነት አስጀመሩ ። በዚህ ምክንያት ለርዳታ ትፈለግ የነበረችው ኢትዮጵያ እንደገና የፖርቹጋል ርዳታን ጠያቂ ሆነች ። ካቶሊካዊት ፖርቹጋል ይህን አጋጣሚ

www.zeyeneta.com

በመጠቀም ለኦርቶዶክሳዊት ኢትዮጵያ በሮም ቤተክህነት የታለመ ሁለት ዓይነት ምርጫ አቀረበች ።

በካቶሊካዊ እምነት የሮሙን ፓፓ የበላይነት ማወቅና በለውጡም ወይም ያደራዊ ርዳታ ማግኘት ወይም ይህን ምርጫ በመቃወም ለውጭ ወራሪ መጋለጥ ጊዜው ፈታኝ ወቅት ስለነበረ የኢትዮጵያ ቤተክህነትና መንግሥት ለዚህ ጥያቄ የእምቢታም ሆነ የእሺታ ምልክት መሆኑ የማይለይ መልስ በመስጠት የርዳታ ጥያቄውን በዲፕሎማቲክ መንገድ ቀጠሉ ።

በፖርቱጋልና በሮሙ ፓፓ በኩል ሁነው ይህን ሁሉ የፖለቲካ ሚና ይጫወቱ የነበሩትም ጆን ቢርሙዲዝና በጸሎት ቤት ንላፊነት ስም የተላከው ፍራንሲስኮ አልበርት ነበሩ ።

አልበርት ይህን ተልእኮ ይፈጽም የነበረው በአንድ በኩል የኦርቶዶክስ ኢትዮጵያን ሥነ ጽሕፈትና የአምልኮ ሥርዓት አፈጻጸም በጻጻሱ በአቡነ ማርቆስና በእጨጌ ያዕቆብ ፊት በማድነቅ ለስውር ዓላማው ሽፋን በመስጠት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ኢትዮጵያ የምትፈልገውን ርዳታ ለማግኘት ለሮሙ ፓፓ ጥያቄ ብታቀርብ ጥያቄው አስቸኳይ መልስ ሊያገኝ እንደሚችል በማጓጓት ኦርቶዶክሳዊት ቤተክርስቲያንን ካቶሊካዊት የማድረግ ተልእኮውን ለመፈጸም የሚያደርገው ጥረት ቀላል አልነበረም ። «አፋ ቅቤ ልቡ ጩቤ» የነበረው አልበርት የሚናገራቸው አስመሳይ ቃላት ለጊዜው ያስደንቃቸው ከነበረው የቤተክርስቲያኒቱ ንላፊዎች አንዱ የሆነው እጨጌ ያዕቆብ የአልበርት የቋንቋ ተማሪ በመሆንም የፖርቱጋል ቋንቋ እስከማወቅ ደርሶ ነበር ።

በኢትዮጵያ በኩል የሚሰጠው መልስ ገና ያላረካቸው ሮምና ፖርቱጋል ለኢትዮጵያ መሪዎች የርዳታ ጥያቄ አፋጣኝ መልስ ባለመስጠታቸው በግራኝ መሐመድ ፈታውራሪነት በኢትዮጵያ ላይ የታሰበው የውጭ ንይሎች ወራሪ ተጀምሮ ጦርነቱ በጠላት የበላይነት መካሄድ ጀመረ ። ይህም ሆኖ ልብነ ድንግልም ሆነ ከልብነ ድንግል በኋላ የተተኩት መሪዎች ለሮም ጥያቄ የአዎንታ መልስ የሰጡ መስለው በመታየት የርዳታ ጥያቄያቸውን በዲፕሎማቲክ መንገድ መቀጠላቸው አልቀረም ።

ጉዳዩን ከረጅሙ በአጭሩ ለመግለጽ ይህኑ ለማጠናከር ኢትዮጵያና

www.zeyeneta.com

ፖርቱጋል በርከት ያሉ አምባሳደሮችንና ደብዳቤዎችን ተለዋውጠዋል ።

ከብዙ ድርድር በኋላ በጥያቄው መሠረት በ1539 ዓ·ም· የፖርቱጋል ንጉሥ ዮሐንስ 3ኛ በሊዝቦን የኢትዮጵያ መልዕክተኛ በነበረው ጸጋ ዘአብና በራሱ መልዕክተኛ በጆን ቤርሙዲዝ ንላፊነት ልዩ ልዩ ገጸ በረከትና የጦር መሣሪያ ርዳታ ከበቂ እግረኛ ወታደር ጋር ለኢትዮጵያዊው ንጉሥ ገላውዴዎስ ላከ ።

ከፖርቱጋል በተገኘው ወታደራዊ ርዳታ በመታገዝ በተደረገው የመልሶ ማጥቃት ውጊያ በ1543 ዓ·ም· በየካቲት 21 እ·አ·አ አሕመድ ግራኝ ከነሠራዊቱ ተደመሰሰ ። ቀደም ሲል ስለተደረገው ርዳታ ገላውዴዎስ ለንጉሥ ጆን የምስጋና መልእክት ላከ ። ሁኖም ከዚህ ድል በኋላ በሁለቱ ተባባሪ ወገኖች መካከል የተካሄደው የሃይማኖት ጦርነት ካለፈው ያነሰ አልነበረም ። ለዚህ ጦርነት መንሥኤ የሆነውም ያው ከርዳታው በስተጀርባ የነበረው የሃይማኖት ቅሰጣ እቅድ ነው ።

ከግራኝ ውድቀት በኋላ ሮም አርቶዶክሳዊት ኢትዮጵያን ካቶሊ ካዊት ለማድረግ የነበራት እቅድ ተግባራዊ የሚሆንበት ጊዜ እንደደረሰ ማሰባ አልቀረም ። ሁኖም ግብፃዊው አቡን አባ ዮሳብ በ1548 ዓ·ም· ኢትዮጵያ ስለገባ ውጤቱ እንደተጠበቀው አልሆነም ። በዚህ ሁኔታ ያልተደሰተው የፖርቱጋሉ ንጉሥ ዮሐንስ ኢትዮጵያ በሮም ፓፓ በተጻፈሰ አቡን የበላይነት እንድትመራ ምኞቱ መሆኑን በይፋ ገለጠ ።

የቀድሞው ጠንሮ አስተካካይና ዲፕሎማት ጆን በርሙዲዝ የካቶሊክ ጳጳስ ሁኖ እንደተሾመ አድርጎ ራሱን በማስተዋወቅ አፄ ገላውዴዎስን ወደ ካቶሊክ እምነት ለመለወጥ የሚያደርገውን ዘመቻ ቀጠለ ። አፄ ገላውዴዎስ ግን ከአርቶዶክስ እምነት ውጭ ምንም ዓይነት አዲስ ሃይማኖት እንደማይቀበልና ከእስክንድርያ ጋር ያለውንም ግንኙነት እንደማያቋርጥ ከማረጋገጡም በላይ ጆን በርሙዲዝን በዲፕሎማቲክ መልዕክተኛነቱ እንጂ በጵጵስና እንደማያውቅ ገለጸ ።

በቤርሙዲዝ ምትክ የተላከው የካቶሊክ ጳጳስ ባሪቶአቢዲዮ በገላውዴዎስ ላይ ያን የተሰለቸ ስብከት ስለቀጠለ ገላውዴዎስ በአርቶዶክሳ ውያን ሊቃውንትና በካቶሊክ ሚሲዮናውያን መካከል ራሱ በሚገኝበት አደባባይ ክርክር እንዲደረግ አዘዘ ። ክርክሩም ተጀመረ ። ሁኖም አቪየዶ በኃይል እንጂ በክርክር ለማሳመን የተላከ ሐዋርያ ባለመሆኑ የውይይቱን

www.zeveneta.com

መድረክ ረግሞ ወጣ ። ይህ ሰው ከገላውዴዎስ ቀጥሎ በነገሠው በአፄ ሚናስ ፊት እጅግ የተጠላና የተናቀ ሰው ስለሆነ አንዳንድ ከዳተኞች መኳንንትን በአፄ ሚናስ ላይ በማነሳሳትና የርስ በርስ ጦርነትም እንዲፈጠር በማድረግ ስውር ተልእኮውን ይፋ አደረገ ።

እንደገና በአፄ ዘድንግል ዘመን ንጉሡ ራሱ ወደ ካቶሊካዊነት የዘመመ አቋም ስላሳየ ከግብፃዊው የኢትዮጵያ ጳጳስ ከአቡነ ጴጥሮስ ጋር ትብብር ያደረጉ መሳፍንት ባስነሡት ጦርነት ድል ሆነ ። ተገደለም ። በአፄ ሱስንዮስ ዘመን የሚሲዮናውያኑ ጩኸት እንደገደል ማሚቶ በንጉሡ ጭንቅላት ስላስተጋባ የኦርቶዶክስን እምነት የሚነቅፍና የካቶሊክ እምነት የአገሪቱ እምነት እንዲሆን የሚደነግግ አዋጅ በድፍረት ዐወጀ ። ይህን ዐዋጅ የሚጥስም መቀጫው ሞት እንደሚሆን ተገለጸ ።

እስከዚያ ዘመን ድረስ የተጻፉ የኦርቶዶክስ መጻሕፍት እንደገና በካቶሊካውያን ሳንሱር እየተደረጉ እንዲስተካከሉ ፣ ሥርዐተ ግዝረት እንዳይፈጸም ፣ የአጽዋማትና በዐላት ቀናት በካቶሊክ ካላንደር መሠረት እንዲስተካከሉ በካቶሊኩ ሊቀጳጳስ ያልተካነና ያልተፈቀደለትም ካህን ቅዳሴ እንዳይቀድስ ወዘተ· የሚል ዐዋጅ ስለተላለፈ በአገሪቱ ደርሶ የማያውቅ ቀውስ ተፈጠረ ።

ለጊዜው የነበሩት ጳጳስ አቡነ ስምዖን ሱስንዮስን ከነተከታዮቹ አወገዙ ፣ መነኮሳትና ቀናዕያን ካህናት በአደባባይ ጩኸው እያለቀሱ በመታየት የኦርቶዶክስ እምነትን በሚኮንነው ዐዋጅ ላይ ያላቸውን ተቃውሞ ገለጹ ። ተቃውሞው ዐዋጁን እጅግ አጠነከረው ። ለእምነታቸው ቀናዕያን በመሆን በንጉሡ ፊት አዋጁን በተቃወሙ መነኮሳትና ቀሳውስት ላይ የሚፈጸም የአደባባይ ግርፋት ርምጃ የበለጠ እየከፋ ሄደ ። ሆኖም ይብሱኑ መነኮሳቱ ፣ ሕዝቡና ካህናቱ በአንድነት ከዳር እስከዳር ተንቀሳቅሰው በሱስንዮስ ላይ ተነሡ ። የሃይማኖት ጦርነት ስለሆነ ሴት ወንድ ፣ ወጣት ሽማግሌው ሳይቀር የተሣተፈበት አሰቃቂ ውጊያ ተካሄደ ። በዚህም የሃይማኖት ጦርነት ብፁዕ አቡነ ስምዖንና አያሌ ካህናት የሰማዕትነትን ሞት በመቀበል ለተከታዮቻቸው ሕዝበ ክርስቲያን መልካም አርአያ ሆኑ ፣ ሕዝቡም የእነርሱን አርአያ በመከተል የገድላቸው ተሣታፊ ሆነ ።

www.zeyeneta.com

ሱስንዮስ ይህን ስለሚያውቅ ዐዋጁን በድፍረት ያወጀው ለዚህ ጉዳይ ከፖርቹጋል ጦር እንደሚላክለት በመተማመን ነበር ። ሆኖም ጦሩ ሳይላክ እሱ ራሱ ባስነሣው ጦርነት ክፉኛ ተመትቶ ድል ሆነ ። ቀደም ብሎ በግራኝ ጊዜ ለርዳታ የተላከው የፖርቹጋል ጦር ቅሪቶችም ከሱስንዮስ ጋር ስለወገኑ ከአገር እንዲባረሩ ተደረገ ። ነገሩ እንዳልሆነ ሲያውቅ ሱስንዮስ በስህተቱ እጅግ አዘነ ፣ ተጸጸተ ። መንግሥቱን ለልጁ ለፋሲል በመተውም ከሥልጣን ተሰናበተ ።

አፄ ፋሲል ዐዋጁን በዐዋጅ በመለወጥ የኦርቶዶክስ ሃይማኖትን እንደነበረ እንዲቀጥል ስላደረገ ሕዝቡ ተረጋጋ ። ከዚያም በሁለቱ ወገኖች መካከል የሃይማኖት ክርክር እንዲደረግ ስለፈቀደ ክርክሩ ቀጠለ ። በክርክሩ አደባባይ የኦርቶዶክሳውያኑ አፈ ጉባኤ ሁነው የቀረቡት እጨጌ በትረ ጊዮርጊስ ሲሆኑ የካቶሊካውያኑ ደግሞ ዶም አፎንሶ መንዲዝ ነበር ። አፎንሶ መንዲዝ «የእግዚአብሔር ልጅ በሞቱ ዓለምን አዳነ» የሚል መጽሐፍ እንደሌለ በመግለጽ ክርክሩን ቀጠለ ። ተከራካሪው እጨጌ በትረ ጊዮርጊስም «እኛ ለእግዚአብሔር ጠላቶቹ ስንሆን በልጁ ሞት ይቅር አለን።» (ሮሜ· 5፣10) የሚለውን ጥቅስ በመጥቀስ የማያዳግም መልስ ሰጠ፣ አፎንሶ መንዲዝ በመልሱ መረታቱን ስላወቀ ራሱን ከክርክሩ ውጭ አደረገ ።

እጨጌ በትረ ጊዮርጊስ ይህን የማያዳግም መልስ በመስጠት የተከራካሪያቸውን አፍ ስለአስያዙ አንድ የቅኔ ሊቅ «ወረከብናሁ ለበትር ዘያደክማ ለሮሜ ፣ ጽሩበ በንባብ ወቅሩፀ በትርጓሜ» ሲል ለእጨጌው ያለውን አድናቆት ገልጿል ። ከዚህ በኋላ ለዚያ ሁሉ እልቂት ምክንያት የሆኑ ሚስዮናውያን ሁሉ ተጠርገው ከአገር እንዲወጡ ተደረገ ፣ ይህም የሆነው ደግሞ ሌላ የሃይማኖት ጦርነት እንዳይቀሰቀስ ለማድረግ ነበር ።

በዘመኑ የነበሩ የአገሪቱ መሪዎችና ሕዝቦች የነበራቸው የእምነት ጥንካሬ የቤተክርስቲያኒቱ ጠንካራ ኦርቶዶክሳዊ ትምህርት ውጤት መሆኑ ግልጽ ነው ። ያም ጥንካሬ ዓለም አቀፍ እውቅናንና ታላቅ ዝናን በማትረፉ የአውሮፓን ትኩረት ሳበ ፣ ከዚያም ከክርስቲያን ፖርቹጋል ጋር አዲስ ግንኙነት እንዲፈጠር አደረገ ። በካቶሊካዊት ፖርቹጋል ስህተት ምክንያት የግንኙነቱ ውጤት አኩሪ ባይሆንም ኦርቶዶክሳዊት ኢትዮጵያ በምንም ዓይነት ኃይል ከእምነቱ የማይናወጥና ለውጭ ወራሪም የማይ

www.zeyeneta.com
በገር ሕዝበ ክርስቲያን አገር መሆንዋን ያረጋገጠችበት ሰልፍ ስለነበር ግንኙነቱ የሚያስደስት ታሪክ ኖረውም ጀልኖረውም ኦርቶዶክሳዊት ኢትዮጵያ በትዝታው አታፍርበትም ። ታሪኩን የምታዘክረው ግን ከትምህርት ሰጭነቱ እንጅ ከቂም በቀል መጋቢነቱ አንጻር አይደለም ።

ምዕራፍ ሸ፯

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የውጭ ግንኙነት በአሁኑ ጊዜ ፣

ሀ) የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያንና የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ፡

የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ እንደቅዱሳት መጻሕፍት ቃል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አዳኝ መሆኑን ማመንና በዚያም እምነት አንድ አምላክ ለሚሆን ለአብ ፣ ለወልድና ለመንፈስ ቅዱስ የሚገባውን የክብርና የምስጋና አቅርቦት ተልእኮ በጎብረት መፈጸም መልካም ፈቃዳቸው የሆነ አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ነው። ድርጅቱ የተመሠረተው እ.አ.አ በ1948 ዓ.ም በአምስተርዳም ሲሆን የራሱ የሆነ ዓላማና ተግባር ያለው ተቋም ነው ። ከዚያም ዋናው ዓላማ ምሥጢረ ቁርባንን በአንድነት ለመፈጸም ከሚቻልበት ሁኔታ ላይ ለመድረስ እስከሚቻል ድረስ አባል አብያተ ክርስቲያናት ስለ እምነት አንድነት የሚያደርጉትን ጥረት ማበረታታትና የክርስቶ ናውን ዓለም አንድነት በተግባር ለማስመስከር መብቃት ነው ።

በአባል አብያተ ክርስቲያናት መካከል ሊኖር የሚገባውን የእርስ በርስ ተራድኦ ማጠናከርም ሌላው የድርጅቱ ዐቢይ ተግባር ነው ። በዚህ የእርስ በእርስ ተራድኦ ተጠቃሚ ከሆኑት አብያተ ክርስቲያናት አንድዋ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ናት ።

በሕጉ መሠረት የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ዓላማውን ተግባራዊ የሚያደርገው በጠቅላላ ስብሰባ ፣ በማዕከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ፣

www.zeyeneta.com

በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ስብሰባና በሌላም እንደአስፈላጊነቱ ሊመደብ በሚችል የሰው ኃይል ነው ። ሕጉ ለአባል ቤተክርስቲያን ምእመናን ብዛት ከፍተኛ ግምት ስለሚሰጥ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን እንደምእመናኖቿ ብዛት በሰባት ዓመት አንድ ጊዜ በሚያካሂደው ጠቅላላ ስብሰባ አሥራ ሁለት፣ በዓመት አንድ ጊዜ በሚደረገው የማዕከላዊ ኮሚቴው ስብሰባ ደግሞ ሁለት መቀመጫ ዎችን በመያዝ በምታደርገው ተሳትፎ የበኩሏን አስተዋጽኦ ታደር ጋለች ።

ድርጅቱ ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ከፍተኛ መንፈሳዊና ማኅበራዊ ጉዳዮች ውሳኔ ሊያገኙ የቻሉባቸው ሰባት አጠቃላይ ስብሰባዎች ተካሂደዋል ። በተደረገው ስብሰባና ውይይት ውጤት፣

ሀ) በእርስ በርስ ጥላቻ ፈንታ በአባል አብያተ ክርስቲያናት መካከል የተቀራረበ ግንኙነትን በመፍጠር በኩል ከፍተኛ ርምጃ ተደርጓል፣

ለ) አባል አብያተ ክርስቲያናት የሐዋርያትን ትምህርትና እምነት ለመከተልና ያንንም እምነት በኅብረት ለመመስከር ፣ እንዲሁም ከዚያ ደረጃ ለመድረስ የተጀመረውን የኅብረት ጉዞ እስከ መጨረሻው ድረስ ለመቀጠል ያላቸውን ሙሉ ፈቃደኝነት አሳይ ተዋል ፣

ሐ) በአብያተ ክርስቲያናት መካከል ሊኖር የሚገባውን የእርስ በርስ ተራድኦ መርሐ ግብር ተግባራዊ በማድረግ በኩል መልካም ውጤት ታይቷል ።

በዚህ በኩል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ቅድሚያ በሚሰጣቸው የዕለት ደራሽ ርዳታ ፣ የመልሶ ማቋቋምና የልማት ነክ መርሐ ግብር አፈጻጸም በኩል ከድርጅቱ የተደረገላትና የሚደረግላት እገዛ ከፍተኛ መሆኑን በምስጋና ታረጋግጣለች ። ስለድርጅቱ የተራድኦ ሥራ መቃናት ልታበረክተው የሚገባትን አስተዋጽኦ ለመቀጠል ያላትን በጎ ፈቃድም በደስታ ትገልጻለች ።

አንድነት ተፈላጊ ነገር እስከሆነ ድረስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን የዚህ ድርጅት መሥራች አባል ናት ።

www.zeyeneta.com

ለ) <u>የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያንና የመላው አፍሪካ አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ</u>

የመላው አፍሪካ አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ በ1963 ዓ.ም እ.ኤ.አ. አሁን ዋና መሥሪያ ቤቱ በሚገኝበት በናይሮቢ የተመሠረተ የአብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ነው ። ማኅበሩ የተመሠረተውም እንደ ቅዱሳት መጻሕፍት ቃል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አዳኝ መሆኑን በማመን አንድ አምላክ ለሆነው ለአብ፣ ለወልድ ፣ ለመንፈስ ቅዱስ የሚገባውን የክብርና ምስጋና አቅርቦት ተልእኮ በሕብረት ለመፈጸም መብቃት ነው ።

<u>የጉባኤው ዋና ተግባርና ዓላማም የሚከተለው ነው።</u>

1. በአብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ወንጌል ስለአብያተ ክርስቲያናት ሕይወት፣ አገልግሎት ፣ ምስክርነትና አንድነት የሚያዘውን ቃል ለመጠበቅና ለማስጠበቅ የሚያስችል ተልእኮ መፈጸም ፣
2. የጋራ ጥናትና ምርምር ማካሄድ፣
3. የጉባኝነት ፣ የኢንፎርሜሽን (የመረጃ) ልውውጥ በማድረግ በአብያተ ክርስቲያናት መካከል የቅርብ ግንኙነትና የልምድ ልውውጥ እንዲኖር ማደፋፈር፣
4. በአብያተ ክርስቲያናት መካከል የባለሙያ ወይም የሰው ኃይል ተራድኦ እንዲኖር ማበረታታት ፣
5. አብያተ ክርስቲያናት የሠለጠነ የሰው ኃይል ለማግኘት የሚያደር ጉትን ጥረት ማገዝ፣
6. ከዚህ በላይ በተገለጸው መንገድ የሚፈለገውን ግዴታ ለመፈጸም በሚያስችልና የድርጅቱንም ነፃ አሠራር መብት በማይነካ ሁኔታ ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ጋር በመተባበር የሚፈለ ገውን ተልእኮ ማከናወን ።

ጉባኤው በየአምስት ዓመት አንድ ጊዜ አጠቃላይ ጉባኤ፣ በየዓመቱ ደግሞ የማእከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ በማድረግ የጋራ ውይይት ያደርጋል ። ውሳኔዎችንም ያሳልፋል ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የዚህ ጉባኤ መሥራች አባል ናት ።

www.zeyeneta.com

በመሆንዋም በየአምስት ዓመቱ በሚያረገው አጠቃላይ ጉባኤ አምስት፡ በየዓመቱ በሚያረገው የማእከላዊ ኮሚቴ ጉባኤ አንድ መቀመ ሓጌዎች አሏት ።

ጉባኤው በናይሮቢ ኬንያ ባለው የማሠልጠኛ ማእከል የሙያ ማሻሻያ ሥልጠና በመስጠትና ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ጋር በመተባበር ለስደተኞች የሚፈለገውን አገልግሎት በማቅረብ ተልእኮውን ለመፈጸም ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል ።

የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጉባኤው የተቋቋመበትን ዓላማ በብቃት እንዲወጣ የበኩሏን አስተዋጽኦ ለማድረግ ያልተቆጠበ ጥረት ታደርጋለች ።

ምዕራፍ ፲፯

በኦሪየንታል ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናትና በምሥራቅ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት መካከል ምሥጢረ ሥጋዌን በተመለከተ የተደረገ ውይይት ፡

የኬልቄዶን ጉባኤ እስከተደረገበት እስከ 451 ዓ·ም ድረስ ቤተክርስቲያን በእምነትና በሥርዐተ አምልኮት አንዲት እንደነበረችና አሁንም ክርስቶስ አንድ በመሆኑ ቤተ ክርስቲያንም ምንጊዜም አንድ እንደሆነች መላው የክርስትና ዓለም ያምናል ። ከኬልቄዶን ጉባኤ በኋላ ግን በጉባኤው ላይ በምሥጢረ ሥጋዌ ምክንያት ቤተክርስቲያን ለሁለት ተከፍላ ቆይታለች ። ለመለያየትም ምክንያት የነበረው ዐቢይ ነጥብ፡ የምሥራቅ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ወገኖች ስለክርስቶስ ምሥጢረ ሥጋዌ ያላቸውን እምነት "በአንድ አካል ሁለት ባሕርይ፡ ሁለት ፈቃድ፡ ሁለት ግብር" በሚል ቃል ሲገልጹ የኦሪየንታል ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ደግሞ፡ "አሐዱ ባሕርይ ዘእግዚአብሔር ቃል ሥጋው" የሚለውን የቅዱስ ቂርሎስን የእምነት አገላለጽ መሠረት በማድረግ "ቃለ እግዚአብሔር ወልድ ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋን ፡ ከነፍስዋ ነፍስን ነሥቶ ሰው በሆነ ጊዜ ፡

www.zeyeneta.com

ያለመከፈል፡
የለመነጣጠል ፣
ያለመጠፋፋት፣

ያለመለወጥ ከሁለት አካል አንድ አካል ፣ ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ በተዋሕዶ ነው" ብለው እምነታቸውን ስለሚያረጋግጡ ነው።

ይህ የእምነት አገላለጽ ልዩነት ከኬልቄዶን ጉባኤ ከ451 ዓ.ም እስከ አለንበት ዘመን ድረስ ለረጅም ጊዜ ለያይቶን ቆይቷል ።

ይሁን እንጂ በኦሪየንታል ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት በኩል ለልዩነቱ ምክንያት ሆኖ የቆየው ይህ የምሥጢረ ሥጋዌ ትምህርት ሆኖ እያለ በምሥራቅ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት በኩል ቤተክርስቲያን ለሁለት እንድትከፈል ምክንያት የሆነው በቃላት የአገላለጥ ልዩነት እንጂ በሁለቱም በኩል የተዋሕዶው መሠረተ እምነት አንድ መሆኑ ተጠቅሶ ወደፊት ወደ አንድነት ሊያመጣ የሚችል የጋራ ውይይት መድረክ እንዲከፈት ስለተጠየቀ ይፋ ያልሆኑና የሆኑ ሰባት የጋራ ጉባኤያት በተለያዩ ጊዜያትና ቦታዎች ተካሂደዋል ።

ጉባኤያቱም ፣

1· በአርሁስ ዴንማርክ እ·ኤ·አ ነሐሴ 11–15 ቀን 1964 ዓ·ም.
2· በብሪስትል ኢንግላንድ እ·ኤ·አ ነሐሴ 25–29 ቀን 1967 ዓ·ም.
3· በጄኔቫ ስዊዘርላንድ እ·ኤ·አ ነሐሴ 16–21 ቀን 1970 ዓ·ም.
4· በአዲስ አበባ ኢትዮጵያ እ·አ·አ ጥር 22–23 ቀን 1971 ዓ·ም.
5· በአባ ቢሾይ ገዳም ግብፅ እ·ኤ·አ 1989 ዓ·ም.
6· በቻምቤዚ ስዊዘርላንድ እ·ኤ·አ 1990 ዓ·ም.
7· በቻምቤዚ ስዊዘርላንድ እ·ኤ·አ ጎዳር 1–6 ቀን 1993 ዓ·ም. የተካሄዱት ነበሩ ።

በእነዚህ ጉባኤያት ሁሉ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በመልእክተኞችዋ አማካይነት ተሳትፋለች ።

በጉባኤያቱ ሁሉ የኬልቄዶኑ ውግዘት መነሻ ምክንያቶች በጥልቅ ተመርምረዋል ። በመጨረሻም በቻምቤዚ ከጎዳር 1–6 ቀን 1993 ዓ·ም. እ·ኤ·አ በተደረገው ጉባኤ በምሥጢረ ሥጋዌ ስለ ክርስቶስ ተዋሕዶ የሚሰጠው ትምህርት ልዩነት የቃላት አገላለጥ እንጂ የእምነት አለመ

www.zeyeneta.com

ሆኑን ጉባኤው ተገንዝቦአል ። ንስጥሮስንና አውጣኬን ግን የሁለቱም ወገን አብያተ ክርስቲያናት የሚያወግዙአቸው መሆኑ ተገልጧል ።

በመጨረሻዎቹ 3 ጉባኤያት ላይ በሁለቱም ወገን ያሉትን ውግዘቶች ማንሣት ስለሚቻልበት ሁኔታ ሰፊ ውይይት ተካሂዷል ። በተካሄደውም ውይይት ውግዘቶችን ስለማንሣት የሚከተሉት የውሳኔ አሳቦች ቀርበዋል ። እነዚህም ፦

1· የሁለቱም አብያተ ክርስቲያናት ቤተሰቦች ውግዘቶችን እንዲያነሱ፣
2· የውግዘቶች መነሣት በሁሉም ወገን በአንድ ጊዜ እንዲፈጸም፣
3· የውግዘቱ መነሣት፣

ሀ) የሁለቱ ወገኖች ሙሉ አንድነት እንደገና መመለሱን ወዲያውኑ የሚያረጋግጥ መሆኑን ፣

ለ) ያለፈው ሰፋኖሳዊ ወይም የግል ውግዘት ከዚያ በኋላ በሁለቱም ወገኖች እንደማይቀጥል ፣

ሐ) የሁለቱም አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ስም በቅዳሴ ጊዜ እንዲጠራ ስምምነት መኖሩን የሚያመለክት እንዲሆን የሚሉ ነበሩ። ከዚህም ጋር ከሦስተኛው ጉባኤ በኋላ ያሉትን የኬልቄዶኑንና ተከታዮቹን ጉባኤያት ኢኩሚኒካል ጉባኤያት አድርገው እንዲቀበሉ የኦሪየንታል ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ተጠይቀው አልተቀበሉትም ።

<u>ከዚህም በመነሳት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ያላትና የሚኖራት አቋም ፣</u>

1· <u>ያለፈውን ውግዘት በተመለከተ፣</u>

ሀ) በምሥጢረ ሥጋዌ አንድ አካል ሁለት ባሕርይ በተዋሕዶ የሚለው የኤልቄዶናውያኑ የእምነት አገላለጥ አንድ አካል ፣ አንድ ባሕርይ በተዋሕዶ ከሚለው የኦሪየንታል ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት

www.zeyeneta.com

ከሚሰጡት የእምነት አገላለጥ ፈጽሞ የተለየና ውግዘቱም በዚያ ምክንያት ስለተላለፈ፡

ለ) አንድ ሺህ አምስት መቶ ዓመታት መሉ ውግዘቱን በተመለከተ ከአባቶቻችን የተቀበልናቸው መጻሕፍት ሁሉ በትክክል የተጻፉና በቤተክርስቲያናችንም ስትገለገልባቸው የቆዩና ያሉ ስለሆኑ፡

ሐ) በዮንያውያኑ ኬልቂዶናውያን ላይ የተላለፈውን ውግዘት ለማንሣት ቀናዊ ሥልጣን ስለሌለ፡

መ) ውግዘቱን በዮንያውያኑ ኬልቂዶናውያን ላይ ያስተላለፉትን የአባቶቻችንንም ክብርና ሥልጣን ስለሚያቃልል ፡ በዮንያውያኑ ኬልቂዶናውያን ላይ የተላለፈውን ውግዘት ማንሣትና የተወገዙትን ቅዱሳን ብሎ መጥራት በቤተክርስቲያናችን አይደገፍም ።

2· <u>ምሥጢረ ሥጋዌን በተመለከተ ፡</u>

በሁለቱም ወገኖች መካከል ያለውን ልዩነት ለማስወገድ ከአርሁስ እስከ ቻምበዚ በተካሄዱት ጉባኤያት በተደረገው ውይይቶች በአሪየንያል አርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት በኩል፡

"ያለመከፈል ፡

ያለመነጣጠል ፡

ያለመጠፋፋት·

ያለመለወጥ ከሁለት አካል አንድ አካል ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ በተዋሕዶ" የሚለው የምሥጢረ ሥጋዌ እምነትና ትምህርት በኬልቂዶናውያኑ በኩል ተቀባይነትን አግኝቷል ።

ይህንም ለመቀበል የቻሉበት ምክንያት ልዩነቱ የአገላለጥ እንጂ የእምነት አለመሆኑን ስላረጋገጡ ነው።

ስለዚህም አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ በአሁኑ ጊዜ ከመራራቅ ይልቅ መቀራረብ ፡ ከመለያየትም ይልቅ በአንድነት መተሳሰብና መረዳዳት ጊዜው የሚጠይቀው መንፈሳዊና ማኅበራዊ ግዴታ ከመሆኑም በላይ በሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት መካከል የነበረው የምሥጢረ ሥጋዌ ትምህርት ልዩነት ከሚወገድበት ደረጃ ላይ እንዲህ ከተደረሰ ፡ በእምነትና በሥርዓት ከሚመስሉዋት አንዱት

www.zeyeneta.com
አብያተ ክርስቲያናት ጋር በአንድነት መክራ ወደፊት በሚያረገው ጉባኤ "አንድ አካል ሁለት ባሕርይ በተዋሕዶ" ከማለት ይልቅ ፡

"ያለመከፈል ፡

ያለመነጣጠል ፡

ያለመጠፋፋት ፡

ያለመለወጥ (በተዐቅቦ)

ከሁለት አካል አንድ አካል ፡ ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ በተዋሕዶ" (አሐዱ ባሕርይ ዘእግዚአብሔር ቃል ሥግው) በሚለው እምነት ከአንድነት ደረጃ ላይ ቢደረስ ቤተክርስቲያናችን በመንፈስ ቅዱስ መሪነት የመቀራረቡን አሳብ የማትቃወም መሆኗን ታረጋግጣለች ።